የዘማች ሹመት የመጨረሻውን እርከን በመቀዳጀት በ1948 ዓ.ም ራስ ተብለዋል።

በየአካባቢው መሬት መያዝ ይወዱ ስለነበረ የመሬት ከበርቴ ምሳሌ ከመሆናቸውም በላይ ሁኔታው ከብዙ ሰው ጋር አጋጭቷቸዋል። ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ የቀድሞ ባለሥልጣኖችን እጃቸውን የሚሰጡበትን ሰዓት ወስኖ በነበረበት ጊዜ ራስ መስፍን ከከተማ ውጭ ስለነበሩ ሰዓቱ ያለፈ እንደሆን ርስታቸው እንዳይወረስ ስግተው ስልክ ደውለው መጣሁ በማለታቸውና ሁኔታው በወቅቱ በሬዲዮ ይተላለፍ ስለነበረ ብዙ ሰው በሁኔታው ተገርሟል። በመጨረሻ ርስታቸውም ተወረሰ፤ እሳቸውም ከተረሸኑት ከስልሣ አንዱ ውስጥ ነበሩ።





# ምዕራፍ ፴፫

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ባህርይና ትክለ ሰውነት

## ትክለ ሰውነት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተፈጥሮአቸው አጭር ሲሆኑ ቁመታቸው አንድ ሜትር ከስልሳ ሴንቲ ሜትር (1.60 ሳሜ)፣ ክብደታቸውም ሃምሳ ኪሎ ግራም (50 ኪግ)፣ የእግራቸው መጫሚያ ትልቅና የቀኙ ወደጎን የሚረግጥ ነበር። ጃንሆይ መልከ ቀና፣ ቀይ፣ ጥርሰ ፍንጭት፣ ትላልቅ ጆሮና አፍንጫ ያላቸው፣ ጠጉራቸው ከግንባራቸው ገባ ያለ፣ ጎፈሬያማ፣ ባለ ሙሉ ጢምና ትልቅ የቅንድብ ጠጉር ያሏቸው ነበሩ። ምንም አጭር ቢሆኑም በ20ኛው ክፍለ ዘመን ካሉት ንጉሦች ሁሉ ንጉሥ ሲኖረው የሚገባው ግርማ ሞገስ ነበራቸው።

አማርኛ ተናጋሪ ቢሆኑም በተጨማሪ አደርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ በመጠኑ ደግሞ ጀርመንኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ያውቁ ነበር። ሲናገሩ አንዳንድ የሚጫኑዋቸው ቃላቶች የነበሩና የምታስቸግራቸውም ድምጽ "ረ" ስትሆን ድምጻቸው ጎርናና ነበር።

ከማጠራቸው የተነሣና ለክብራቸውም ሲባል ወንበር ላይ ሲቀመጡ ብዙ ጊዜ እግራቸው ሥር ትራስ ይደረግ ነበር።

## ባህርይ

በጠባይ በኩል የሁለት ተፈሪዎችን ስብዕና የተላበሱ ነበሩ ለማለት ይቻላል። አንደኛው ተፈሪ ትሁት፣ ሩህሩህ፣ ለጋስ፣ ሲሆን ሁለተኛው ተፈሪ ደግሞ ቁጡ፣ ጨቋኝ፣ ቂመኛና አናካሽ ነበሩ። በጠቅላላው ግን ተፈሪ በኅብረት ኩሩ፣ ጨዋ፣ ደፋር፣ ራስ ወዳድ፣ የማስታወስ ችሎታ

ያላቸውና ሞትን ያልተቀበሉ ሰው ነበሩ። እንደ ቀድሞ ነገሥታት ግን ጠረኛ አልነበሩም።

ምግብ የሚበሉት መርጠው ሲሆን ቁርሳቸው ቅንጬና ዱለት ነበር። ምንም እንኳን አግ መብላት ቢያዘወትሩም ለምሳና እራት የተለየ ምግብ አይዘጋጅላቸውም። በግብር ሰዓት እፊታቸው ጥሬ ሥጋ ለደንቡ ይቀመጣል እንጂ አይበሉትም ነበር። ሆኖም ለሚወዱትና ጥሬ ሥጋ አበላሉ ለሚያምር ሰው የራሳቸውን ፋንታ ይሰጡ ነበር። ምክንያት ሲኖር ጥቂት ወይን ጠጅና ሻምፓኝ ይቀምሳሉ እንጂ የአልኮል መጠጥ በፍጹም አይነኩም። ለጥም ማርኪያ ግን የፈረንሳይን ኤቪያን የሚባለውን ውሃ ይመርጡ ነበር።

ጃንሆይ ሽክ ያለ አለባበስ በጣም ይወዱ ነበር። ሽቶም እንደሚወዱ አጠገባቸው የደረሰ ሰው ሁሉ ስለሚያውደው ይታወቃል። በ1923 ዓ.ም ለዘውድ በዓላቸው የፈረንጅ ቅድ አሰፍተው መኳንንቱ እንዲለብስ ፈልገው ከንቲባ ገብሩን ቢያማክሯቸው "ምን ያደርግልናል የእኛኑ እንልበስ፣ አለበለዚያ የገና ዛፍ እንመስላለን" ብለዋቸዋል። የወታደሩን የየክፍለ ጦር ልብስ መልበስ ያዘወትሩ ነበር። ይህም የክብር ዘበኛ፣ የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይል፣ የጦር ሠራዊት የደንብ ልብስ ነበር። ኢንሳይድ አፍሪካ (Inside Africa) የሚል መጽሐፍ ላይ ጃንሆይን ሲገልጻቸው የክብር ዘበኛ ባርኔጣ ሲያደርጉ ሰውነታቸው ረቀቅ ያለ ስለኾነ እንጉዳይ ይመስላሉ ብሏቸዋል። አገር ውስጥ በብዛት ካባ መልበስ ቢወዱም አውሮፓና አሜሪካ ሲሄዱ ግን ካፖርት ይለብሱ ነበር። የማይታበል ሃቅ ግን ምንም ይልበሱ ያምርባቸዋል።

ብዙ ሰው እንደታዘበው ቀይ ሰው ይወዱ ነበር። በተለያዩ አጋጣሚዎች ተማሪዎች ንጉሡ ነገሥቱ ዘንድ ሲቀርቡ የሚያነጋግሩት ቀያዩቹን እየመረጡ ነበር። ለማነጋገር ሲፈልጉ የሚያስቀድሙት የማነህ ልጅ? በሚል ጥያቄ ነበር። የማስታወስ ችሎታቸው ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ የእከሌ ልጅ ነኝ ሲል ብዙውን ጊዜ አባትየውን የሚያውቁ ሆነው ይገኛሉ። የሚገርመው ነገር ሊያነጋግሩት የሚገባ ተሸላሚ ተማሪ ጠይም ወይም ጥቁር ከኾነ ሳያነጋግሩ ማለፋቸው የተደጋገመ ክስተት ነው። ቁመቱም ዘለግ ያለ ከኾነ አልፈው አልፈው ያነጋግሩ ነበር። ኢንጂኔር ኃይሉ ሻውል የምኒልክ ተማሪ በነበሩበት ወቅት "አንተ የማነህ ልጅ?" ተብለው ሲጠየቁ "እኔ የገበሬ ልጅ ነኝ" በማለት ተገቢውን ንጉሣዊ ክበሬታ



ሳይለግሱ በመቅረታቸው ችግር ላይ ወድቀው በትምሕርት ቤቱ ዳይሬክተር በሚስተር ስሚዝ አማካይነት ከትምሕርት ገበታ ሳይባረሩ ቀርተዋል። ቀኃሥ በነጭ የበላይነት የሚያምኑ ከመሆናቸው በላይ የውጭ አገር ሰው ካልኾነ በስተቀር ኢትዮጵያዊ አይጨብጡም ነበር። ምናልባት ኢትዮጵያዊው ከውጭ አገር ሰዎች ጋር ሆኖ ቢጨብጡም ፎቶግራፍ ከተነሳ በምንም መልኩ ይፋ እንዳይሆን ፎቶግራፍ አንሺዎችን ፕሮቶኮል ይከለክላቸዋል። ጃንሆይም ሳይጠነቀቁና ሳይፈቅዱ ፎቶግራፍ ከተነሱ ፍቶግራፍ አንሺው ተይዞ ፊልሙ ይሰረዛል።


አልጋ ወራሽ ተፈሪ

የቀን ፕሮግራማቸው ለየት ያለ ነበረ። ጧት በሦስት ሰዓት ወደ ቢሮ ሄደው ሲሠሩ ይቆዩና ወደ አምስት ሰዓት ላይ ችሎት ያስችላሉ። ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ቆመው ነው። ወደ መጨረሻው ገደማ ግን መቀመጥ ጀምረው ነበር። ከችሎት በኋላ ወደ ቤተ መንግሥት ተመልሰው ምሳ ይበሉና ትንሽ ጋደም ብለው ይነሳሉ። ከሰዓት በኋላ የሥራ ፕሮግራማቸው እየዞሩ የሥራ ጉብኝት ማድረግ ወይም የሚጎበኝ ከሌለ ሽርሽር መሄድ ነበር። ማታ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እራት ከበሉ በኋላ ሲኒማ ካለ አብረው ይመለከታሉ። አለበለዚያ ከትንሽ ጭውውት በኋላ ቤተሰቡ ሲተኛ እሳቸው ቢሯቸው ገብተው የመጣላቸውን የዕለት ሪፖርት ይመለከታሉ። የሚያነቡትም ነገር ካለ ያነብባሉ። ብዙ እንቅልፍ ስለሌላቸው የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ዕኩለ ሌሊት ድረስ ሲሠሩ ቆይተው ይተኙና በአሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ይነሳሉ። አምሽተው በሚሠሩበት ወቅት አስቸኳይ ነገር ካለ ሚኒስቴሮቻቸውን ደውለውም ቢሆን ይጠይቃሉ። የሚያድር ጉዳይ ከኾነ በማግሥቱ ያጣራሉ።



ንግሥት ኤልሳቤጥና ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ጠባያቸው እንዳረማመዳቸው ደፋርና በሕዝብ መካከል በእግር የሚሄዱ፣ በቤተ ክርስቲያን ለንግሥ በዓል የሚገኙ፣ መሥሪያ ቤቶችን፣ አዳሪ ትምሕርት ቤቶችን፣ ፋብሪካዎችንና ሆስፒታል የተኙ ህመመተኞችን ሳይታሰብ ከተፍ ብለው መጎብኘት የሚያዘወትሩ መሪ ነበሩ። ማንም ተበድያለሁ የሚል ሰው ነጠላውን አንጥፎ አቤት! ሲል፣ መኪናቸውን አስቁመው ጉዳዩን ይሰሙና ባልደረባ ሰጥተው ያልፋሉ እንጂ የሕዝብን አቤቱታ አይንቁም ነበር። የማስታወስ ችሎታቸው ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ አንድን ሰው በአንድ ጉዳይ ካወቁት ከአሥር ዓመት በኋላም ቢያገኙት ያስታውሱታል። ቂምም ከያዙ ስለማይረሱ ለተቈመበት ሰው ችግር ነበር።

የቋንቋ ችሎታቸው ከፍተኛ ስለ ኾነ አንድ ሰው ሲናገር የንግግሩን ውስጠ ምስጢር በቶሎ የመረዳት ችሎታ አላቸው። እሳቸውም ብዙ ጊዜ ነገር ጣል ያደርጉ ነበር። ሲናደዱ አደገኛ ከመሆናቸውም በላይ ከመኳንንቶቻቸው መካከል የተገረፉም፣ በጥፊ የተመቱም ነበሩ። ማንም የመንግሥታቸው ተቀናቃኝ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት ወደ እስር



ይሰውጣሉ እንጂ እንዲገደል አይወዱም ነበር። በፖለቲካ ጉዳይ በፍርድ የተገደሉት በላይ ዘለቀና መንግሥቱ ንዋይ ብቻ ሲሆኑ፣ በእስር ግን በፍርድም ያለፍርድም ብዙ ሰው በዘመናቸው ተጉላልቷል። በተረፈ የሞት ፍርድ ሲፈረድ ውሳኔውን ካላጸደቁት በስተቀር ማንኛውም ወንጀለኛ በሞት አይቀጣም። በዘመናቸው በስቅላት የተቀጣች አንድ ሴት እንደነበረች ይታወሳል። የተሰቀለችውም መስፍን ሐረር መንገድ ሾላ ይባል በነበረው ቦታ ላይ ነው። የተሰቀለችበትም ምክንያት በወቅቱ ስለሴት እኩልነት በስፋት ይወራ ስለነበረ ከወንዶች እኩል ሴቷንም በመቅጣት እኩልነትን ለማረጋገጥ የተደረገ እርምጃ ይመስላል።

ጃንሆይ ከሚቋቋመው ድርጅት አብዛኛው በእሳቸው ወይም በቤተሰባቸው ስም እንዲጠራ ይፈቅዱ ነበር። አዲስ አበባ ውስጥ ካሉ ድርጅቶች ብቻ በራሳቸው ስም የሚጠሩት እንደሚከተለው ይሆናል።

| | |
|---|---|
| 1 | ተፈሪ መኮንን ትምሕርት ቤት |
| 2 | ተፈሪ መኮንን ሆስፒታል (ኢንስቲትዩት ፓስተር) |
| 3 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አንደኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት |
| 4 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት |
| 5 | ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ |
| 6 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል |
| 7 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ቲያትር |
| 8 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስታድየም |
| 9 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አየር ማረፊያ |
| 10 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የበጎ አድራጎት ድርጅት |
| 11 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት |
| 12 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጎዳና |
| 13 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ |
| 14 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የአካለ ስንኩላን ት/ ቤት |
| 15 | የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መርሃ ዕውራን ት/ ቤት |

በሁሉም ቦታ ከፍ ያለ ነገር ከተሠራ የሚጠራው በንጉሡ ነገሥቱ ስም ነው። ለምሳሌ ያህል የዓባይ ድልድይ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ድልድይ ይባላል። የንጉሡን ድክመት የተገነዘቡ አድር ባዮች ለሚመረቀው ድርጅት ሁሉ የሚያቀርቡት ስም የተለመደ ቢሆንም ንጉሡም አይቃወሙም። ጀኔራል ደ ጎል አዲስ አበባን በሚጎበኙበት

ወትት አራዳ መካከል ይገኝ የነበረው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ በሱ ስም ሲለየም ጃንሆይ በመከላከያ ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መካከል ያለውን የአድዋ አደባባይ የነበረውን በስማቸው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አደባባይ ተብሎ ተጻፈበት። የአደባባዩ ስያሜ በይፋ ያልተመረቀ ስለነበረ ብዙ ሰው ግንዛቤው እስካሁን አይኑረው እንጂ የአዲስ አበባ የመንገድ ካርታ ላይ ይገኛል።

ቂመኛነታቸው ጎልቶ የታየው በራስ አደፍርሰው ልጅ በሻለቃ ክፍሌ አደፍርሰው ላይ የደረሰውን በመገንዘብ ነው። በስደት ዘመን ባዝ ከነበረው መኖሪያ ቤታቸው አጠገብ ክፍሌ አደፍርሰውና ልዑል መኮንን ልጆች ስለነበሩ ሲጫወቱ ተደባድበው ክፍሌ ልዑል መኮንንን አፍንጫቸው ላይ ስላደማቸው አቤት እያለቀሱ ሲመለሱ ደሙን ጃንሆይ ተመልክተው በጣም ተቆጡ። "አንተ የጌታህን ልጅ እንዴት ደፍረህ ትመታለህ?" ብለው ተቀቆጡ። በዚህ ቂም ይዘው ሻለቃ ክፍሌ አደፍርሰውን ሲያንገዋልሏቸው ኖረዋል። የራስ ልጅም ሆነው ከሻለቃ በላይ ማዕረግ ሊበልጡ አልቻሉም።

ራስ አደፍርሰው የሚታወሱበት ነገር ቢኖር አንድ የመንግሥት ሂሳብ ሠራተኛ ሲደምር "አንድ አለኝ! ሁለት አለኝ!" ሲል ሰምተው "አንተ ሌባ! አንተ እዚህ ውስጥ ምንም የለህም! ሁሉም የመንግሥት ነው!" ብለው በመቆጣታቸው ነው።

ጃንሆይ ወደ ውጪ አገር አሽሽተዋል ስለተባለው ገንዘብ በይፋ ሁኔታው እልባት ባይሰጠውም የተነገረው የገንዘብ ልክ ግን ከአገሪቷ አቅም በላይ ስለኾነ የማይታመን ነው። የኾነው ሆኖ ገንዘብ አያስቀምጡም ለማለት ደግሞ ሁኔታዎችን ለተመለከተ ምናልባት ትንሽ ገንዘብ አስቀምጠው ይሆናል። ከማይጨው ጦርነት በፊት አንዳንድ መኳንንቶች ውጭ አገር ገንዘብ እንደነበራቸው በተለይ ራስ ኃይሉ ተክለ ሃይማኖት አንድ ሚሊዮን ፓውንድ ስተርሊንግ እንዳስቀመጡ አቢሲኒያ ኦን ዘ ኢቭ በላዲስላስ ፋራጎ (ABYSSINIA ON THE EVE by Ladislas Farago) በሚለው መጽሐፉ ጠቅሶታል። ጃንሆይ በስደት እሥራኤል አገር እንደገቡ ሰባት ቡችላ ወርቅ ባርክሌይስ ባንክ እንዳስቀመጡ በላይ ግደይ በጻፉት መጽሐፍ ላይ ተጠቅሷል። እንደነገ በስደት ሲሄዱ እንደዛሬ የኢትዮጵያ ባንክ የነበረውም ገንዘብ እንደተወሰደ ይታወቃል። ይኽ እንኳን ጠላት ከሚወስደው ለስደት ዘመን እንዲሆን የተወሰደ



እርምጃ ስለሆነ ትክክል ሊሆን ይችላል። ንጉሠ ነገሥቱ በስደት ወደ እንግሊዝ አገር ሲሄዱ አፄ ምኒልክ ኢትዮጵያ ላይ ክፉ ቀን የመጣ እንደሆን አገሪቷ እንዳትቸገር በማለት በልዩ ውል ኢየሩሣሌም በክሬዲሊዮኔ ባንክ ውስጥ ያስቀመጡትን 200,000 ማርያ ትሬዛ ብር አውጥተው ተጠቅመውበታል። በየጊዜው ገንዘብ ወደ ኢየሩሣሌም መላኩ አስቸጋሪ ስለሚሆን ዋናው ገንዘብ ተቀማጭ ኾኖ ወለዱን በኢየሩሣሌም ገዳማት ውስጥ ለሚኖሩ ለኢትዮጵያዊ መነኮሳትን መተዳደሪያ እንዲሆን የተቀመጠ ገንዘብ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ በስደት እያሉ ወደ መጨረሻ ላይ የገንዘብ ችግር ላይ እየወደቁ መሄዳቸው ታውቋል። በዚህም የተነሳ ከሃኪም ወርቅነህ ጋር ተጣልተው ነበር። የተጣሉትም የኤምባሲውን ገንዘብ ስጠኝ አልሰጥም በመባባል ነበር። የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ነርስ ሲስተር ምሕረት ጳውሎስ በስደት ዘመን በአስተርጓሚነት ንጉሠ ነገሥቱን ሲያገለግሉ "ትንሽ ገንዘብ ይስጡኝ" ብለው ጃንሆይን ቢጠይቁ "ገንዘብ የለም" ሲባሉ ተናደው "ገንዘቡ እኮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት ነው እንጂ የግል ገንዘብዎ አይደለም" ብለው ስለተናገሩ ዳግመኛ መግባባት ላይ ሊደረስ ስላልተቻለ ወደ ሱዳን ሄደው እዚያው ሱዳናዊ አገቡ።

ጃንሆይ ከስደት እንደተመለሱ የነበረባቸው ትልቁ ችግር ለደሞዝተኛ የሚከፈል ገንዘብ ስላልነበረ መንግሥታቸውን ለማቋቋም ተቸግረው ነበር። ከስደት መልስ የገንዘብን ነገር በቀላሉ የሚመለከቱት ጉዳይ አለመሆኑን በመረዳት ተመሳሳይ ችግር ቢፈጠር ትንሽ ዘስሚ ላስቀምጥ ብለው ወስነው ሊሆን ይችላል። ሆኖም ብዙ ሰው ውጭ አገር ገንዘብ አስቀምጠዋል እያለ ቢያወራም የአገሪቱን ሃብት በመመልከት እጅግ በርካታ ገንዘብ ሊያስቀምጡ ችለው ነበር ማለቱ በፖለቲከኞች የተጋነነ አነጋገር ይመስላል።

ጆን ማን 'ዘ ላዮንስ ሼር' በሚለው መጽሐፉ ላይ ጃንሆይ ሲሞቱ በለንደን፣ በዙሪክና በኒውዮርክ ተቀማጭ ወርቅ እያላቸው ሳይናዘዙ በማለፋቸው የተከሰተውን ችግር ያትታል። አስከትሎም ወርቁ መከበት የጀመረው በአልጋ ወራሽነት ዘመናቸው ለንደን በመጡ ጊዜ ካስቀመጡት ወርቅ ላይ በየዓመቱ የሚላከው ወርቅ እየታከለበት መሆኑን ይገልጻል። በየዓመቱ ይላክ ነበር ያለው የወርቅ ብዛት ከ100,000 ወቄት እስከ 200,000 ወቄት እንደነበረም አትቷል። ይህ

በገንዘብ ሲተመን ከዘጠኝ ሚሊዮን እስከ አሥራ ስምንት ሚሊዮን የአሜሪካ ብር መሆኑ ነው። በመጨረሻ ሳያወርሱ የሞቱት የወርቅ ብዛት ሁለት ሽህ አምስት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ይገመታል ብሏል። የጆን ማን ጽሑፍ ግን ተአማኒነት ያለው አይመስልም።

ወርቅ በአይሮፕላን ወደ ለንደን በየወቅቱ እንደሚሄድ ብዙ ሰው ያውቅ ነበር። ምናልባት ለኢትዮጵያ ብር ዋስትና ይሆናል ብሎ ያስብ ነበር እንጂ ጃንሆይ ገንዘብ በግል ያስቀምጣሉ ብሎ ለመደምደም በእሳቸው ዘመንና ሁኔታ ይከብድ ነበር። ምክንያቱም ኢትዮጵያ ማለት እሳቸው፣ እሳቸው ማለት ኢትዮጵያ ስለነበሩ ነው። ወደ መጨረሻ ላይ ግን ይኸው የገንዘብ ጉዳይ በሰፊው ይወራባቸው ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ መጠርጠራቸው እንኳን ለብዙ ሰው አሁን ድረስ አይዋጥለትም። ከዚህች የድሃ አገር ይህን ያህል ኃብት ተወስዶ ከሆነና ከተረጋገጠ የጃንሆይ ታሪክ መልኩን ይቀይራል፣ ደጋፊዎቻቸውንም የሚያሳፍር ይሆናል። በሌላ መልኩ ያስቀመጡት ገንዘብ ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው ተጣርቶ ዕውነቱ ታውቆ ስማቸው የሚጸዳበት ሁኔታ ቢመቻች ምንኛ ጥሩ ነበር። ስለሆነም በተቻለ የህንን ጉዳይ ከፖለቲካ የጸዳ አካል ተፈጥሮ ሊከታተለውና ሊያጣራው የሚገባ ጉዳይ ነው።

የደርግ መንግሥት ከጃንሆይ መንግሥት ቀጥሎ ሥልጣን የተረከበ ስለነበረ ይህን መሰሉን ጉዳይ በሥርዓት እንደማጣራት ለፖለቲካ መጠቀሚያ ሲል ጥሩውንም አቆሽሾ ማቅረቡ ፍትሐዊ አልነበረም። ለምሳሌ የልዑል አሥራተ ካሣ ሴት ልጅ ለሠርጓ የትምህርት ቤት ጓደኞችዋ ከእንግሊዝ አገር የላኩላት ኬክ ተሰብሮ ለጥገና ሒልተን ሆቴል ስላመጣችው ደርግ ነገሩን ሳያጣራ ብዙ ካወራ በኋላ ሃሰት መሆኑ ተረጋግጦ ነበር። ልጅቱም የተሰራጨውን ዜና አስተባብሉልኝ ብትል ይሂማ አይሆንም ፖለቲካ ያበላሻል መባሉዋን በቦታው ስለነበርኩ አስታውሳለሁ። ስለሆነም አንድን ነገር ለማጣራት ከፖለቲካ የጸዳ ወገንካልኾነ ማመኑ ያስቸግራል።

ታለፉት ይሻላል ተብሎ ነው እንጂ
ተፈሪ መኮንን ለሊላም አይበጅ
እኩሉን ቲያስለቅስ እኩሉን ሊያበጅ
ሃምሳ ዓመት ይገዛል ሰው የለውም እንጂ
እንቁላሉ ገምቶ ጠፋ በሰው እጅ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል





# ምዕራፍ ፴፯

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ልጆች

## ከጋብቻ የተወለዱ ልጆች

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከእቴጌ መነን ጋር ከተጋቡ በኋላ ስድስት ልጆች ወልደዋል። እነሱም

| | |
|---|---|
| 1 | ልዕልት ተናኘ ወርቅ |
| 2 | ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን |
| 3 | ልዕልት ሀነበ ወርቅ |
| 4 | ልዕልት ፀሐይ |
| 5 | ልዑል መኮንን |
| 6 | ልዑል ሣህለ ሥላሴ ናቸው |

## ልዕልት ተናኘ ወርቅ

ልዕልት ተናኘ ወርቅ ጥር 22 ቀን 1905 ዓ.ም ተወለዱ። ልዕልት ተናኘ ወርቅ ራስ ደስታ ዳምጠውን አግበተው ስድስት ልጆች አፍርተዋል። ልጆቹም

| | |
|---|---|
| 1 | ልዕልት ዓይዳ ደስታ |
| 2 | ልዑል አምኃ ደስታ |
| 3 | እመቤት ሆይ ሂሩት ደስታ |
| 4 | ሬር አድሚራል እስክንድር ደስታ |
| 5 | እመቤት ሆይ ሰብለ ደስታ |
| 6 | እመቤት ሆይ ሶፍያ ደስታ |

እንዲሁም እንግሊዝ አገር በስደት በነበሩበት ወቅት ከክቡር አቶ አበበ ረታ እመቤት ሆይ ኢሳማዝን ወልደዋል።



ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከልጆቻቸውና ከልጅ ልጆቻቸው ጋር

ራስ ደስታ ዳምጠው ከተማ በማይጨው ጦርነት ወቅት በሲዳሞ በኩል ዘምተው ጦራቸው ሲፈታ ወደ እናታቸው አገር ቡታጅራ ተሸሽገው ካሉበት ተይዘው ከራስ ካሣ ሁለት ልጆች ጋር የካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ተገደሉ። ንጉሠ ነገሥቱ ከማይጨው መልስ ሲሰደዱ አብረዋቸው ከተሰደዱት አምስት ልጆቻቸው መካከል አንዷ ልዕልት ተናኘ ወርቅ ነበሩ። የራስ ደስታ አያት ከተማ አንተን ይስጠኝ ይባላሉ። እሳቸውም ከጎንደር የመጡ የአስኳል ዘር ናቸው። ቅድመ አያታቸው አቶ አንተን ይስጠኝ አፄ ቴዎድሮስ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ ጦርነት ላይ ጦር ሰብቀው አፄ ቴዎድሮስን ሲሸማቀቁ አይተው ሽምቃቃ! ብለው ተዋቸው። አፄ ቴዎድሮስም ጀግንነታቸውን ተመልክተው መጨረሻ ላይ ይዘዋቸው ወደ ጎንደር ሄዱ[20]። የራስ ደስታ ወንድም ጀኔራል አበበ ዳምጠው የልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አባት ናቸው። ደጃዝማች ዳምጠው የአፄ ምኒልክ መልዕክተኛ ሆነው ወደ ሩሲያ ንጉሥ ዳግማዊ ኒኮላስ ዘንድ ተልከው በሄዱ ጊዜ

[20] ከአስኳል መጽሐፍ የተገኘ



የእርሳቸውን መልክና ቁመና በመመልከት ሩሲያኖች ኢትዮጵያውያንን በተለየ ዓይን መመልከት ጀመሩ። አፄ ምኒልክ የጠየቁትን የጦር መሣሪያና የጦር መኮንኖች ከሩሲያ ይዘውም ተመልሰዋል።

የልዕልት ተናኘ ወርቅ የመጨረሻ ሴት ልጅ እመቤት ሆይ አልማዝ (ሜሪ) አበበ ዶክተር ሥዩም ሃረጎት ባለቤት ነበሩ። በዚህ ትዳር ሁለት ልጆች ወልደው በዘመነ ደርግ አባታቸው ክቡር አቶ አበበ ረታ፣ ወንድማቸው ሬር አድሚራል እስክንድር ደስታ፣ አማቻቸው ደጃዝማች ሃረጎት አባይ፣ አያታቸው ቀኃሥ ተገደሉ። እናታቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅ፣ ባለቤታቸው ዶክተር ሥዩም ሃረጎት ከሌሎች ብዙ የሥጋ ዘመዶቻቸው ጋር ታስረውባቸው ነበር። ይኸን ሁሉ ስቃይ በመመልከት ተማርረው የራሳቸውን ሕይወት አጥፍተዋል።

ልዕልት ተናኘ ወርቅ ከስደት መልስም ራስ አንዳርጋቸው መሳይን አግብተው ይኖሩ ነበር። የባሕር ኃይል አዛዥ የነበሩት ልጃቸው ሬር አድሚራል እስክንድር ደስታ እንዲነግሡላቸው እንደሚፈልጉ ይወራ ነበር። ልዕልት ተናኘ ወርቅ በ90 ዓመታቸው አርፈው ሚዝያ 7 ቀን 1995 ዓ.ም በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።

ሬር አድሚራል እስክንድር ደስታ የአቶ አማኑኤል አብርሃምን የመጀመሪያ ልጅ ወይዘሮ ሣራን አግብተው ቢፋቱም በአሁኑ ሰዓት በአሜሪካን አገር የምትኖረውን ወይዘሪት ናዕሚ እስክንድርን ወልደዋል። ደርግ ከገደላቸው 61 ባለሥልጣኖች መካከልም አንዱ ነበሩ።

ልዕልት ዓይዳ ደስታ ራስ መንገሻ ሥዩምን አግብተው ብዙ ልጆች ወልደው አሁንም በሕይወት ይገኛሉ።



የሬር አድሚራል እስክንድር ደስታ ጋብቻ

# ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን

ልዑል አልጋ ወራሽ አሰፋ ወሰን ሐምሌ 20 ቀን 1908 ዓ.ም ተወለዱ።



ልዑል አልጋ ወራሽ አሰፋ ወሰንና ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ

እሳቸውም የራስ ሥዩም መንገሻን ልጅ ልዕልት ወለተ እሥራኤልን አግብተው ልዕልት እጅጋየሁን ወልደዋል። ልዕልት ወለተ እሥራኤል ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ከመጋባታቸው በፊት ከአድዋው ተወላጅ ከደጃች ገብረ ሥላሴ ደጃዝማች ዶክተር ዘውዴ ገብረ ሥላሴን ወልደዋል። ልዕልት እጅጋየሁም እንግሊዝ አገር እንዳሉ የተዋወቁትን የወለጋውን ባላባት የደጃች ሃብተ ማርያምን ልጅ ፍቅረ ሥላሴን አግብተው ሲኖሩ መጨረሻ እስር ቤት እንዳሉ ታመው ሞቱ።

ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ከልዕልት ወለተ እሥራኤል ጋር ከተፋቱ በኋላ ከልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ጋር ተጋብተው

| | |
|---|---|
| 1 | ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ |
| 2 | ልዕልት ማርያምሥና |
| 3 | ልዕልት ስሂን |
| 4 | ልዕልት ሥፍራሽ ወልደዋል። |



ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ በ1966 ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት አልጋ በተነቃነቀበት ወቅትና ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰንም ታመው እንግሊዝ አገር በነበሩበት ጊዜ ተጠባባቂ አልጋ ወራሽ ተብለው ሐምሌ 16 ቀን ተሾሙ።

ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን በስደት እያሉ አምኃ ሥላሴ ተብለው መንገሣቸውን ይፋ ቢያደርጉም ኮሎኔል መንግሥቱን በግል ከማስደንገጡ በስተቀር ምንም ለውጥ አላመጣም። ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ልጃቸው ተጠባባቂ አልጋ ወራሽ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብ በጤና ጉድለት ምክንያት ሊተኳቸው አልቻሉም።

ልዕልት ማርያምሥና የአርበኛውን የደጃዝማች ዘውዴ ጥላሁንን ልጅ አቶ ሰይፉ ዘውዴን አግብተው ብዙ ልጆች ወልደዋል።

ጃንሆይ ልዑል አልጋ ወራሽን እንደ ልዑል መኮንን አያስጠጉም ነበር። እንዲያውም አይወዱዋቸውም እየተባለ በሕዝብ ዘንድ ይወራ ነበር። የማይወዱበትም ምክንያት በሰዉ ዘንድ የሚወራው የልጅ ኢያሱ ልጅ ናቸው ብለው ስለሚጠረጥሩ ነው። ነገር ግን ልዑል አልጋ ወራሽ ጃንሆይን በቁመት፣ በእርጋታ፣ በአረማመድና በድምጽ ይመስሏቸዋል። እነመንግሥቱ ንዋይ አስገድደው ያስነበቧቸውን አዋጅ ለሰማ ሰው ከጃንሆይ ጋር የድምጻቸውን ተመሳሳይነት በማዳመጥ ልጃቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ ይቻላል።

ምንም እንኳን ልዑል አስፋ ወሰንን አልጋ ወራሻቸው አድርገው አፄ ኃይለ ሥላሴ ቢሾሙዋቸውም እምብዛም ስለማያፈቅሯቸው በመካከላቸው አለመግባባት ነበር። ሕዝቡ በሙሉ 'አልጋ ወራሽ አይነግሡም' እያለ እንደዘበት ይናገራል። ይሁንና ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ የወሎ ገዥ ከመሆናቸውም በላይ ንጉሠ ነገሥቱ በአገር ውስጥ በማይኖሩበት ወቅት የመንግሥቱን ኃላፊነት ይዘው ይጠብቁ ነበር። ጃንሆይ አልጋ ወራሻቸውን ወደ ኋላ ላይ ንጉሥ ብለው ለመሾም ቀርቶ እስከመጨረሻው ድረስ በካቢኔያቸውም እንኳን አላሳተፏቸውም። በዚህም ምክንያት ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ደስተኛ አልሆኑም።

ይህንን ሁኔታ የተረዱ ባለሥልጣኖች በጃንሆይና በአልጋ ወራሹ መካከል የነበረውን ክፍተት ለማስፋት ሞክረዋል። አንድ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ለሁለት ወር ጉብኝት ላይ በነበሩ ጊዜ ልዑል አልጋ ወራሹ

የተወዘፉ ሥራዎችን አጠናቅቀው ሚኒስትሮችን በደንብ ተቆጣጥረው መልካም ሥራ ሠሩ። ይህንን ሁኔታ ያልወደዱት በተለይ ክቡር አቶ መኮንን ሃብተ ወልድ የአገር ፍቅር የበላይ ስለነበሩ "ጠቅል ቶሎ ና. ጠቅል ቶሎ ና" የሚል ዘፈን ያዘፈኑት በዚያን ጊዜ ነበር።

ልዑል አልጋ ወራሽ ፍርድ አዋቂና ቁጥብ ሰው ነበሩ። የወሎ አገረ ገዥ ሆነው ሁሉም ሰው 'አስፋው ወሰን ይሙት!' እያለ ሲምል ለሕዝቡ ግን ያደረጉት ነገር አልነበረም። እንዲያውም ብዙ ንብረት እንደገፈፉ ተደርጎ ይታሙ ነበር። የወሎ ረሃብ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ወቅት ንጉሡ ነገሥቱ ሰምተው ወሎን ሲጎበኙ የረሃቡን ዕናት ሲመለከቱ ልዑል አልጋ ወራሽን በኃይል ተቆጡ። በዚህም ቁጣ አልጋ ወራሽ ተከፍተው ስለነበረ ከጉብኙቱ በኋላ ደብረ ዘይት ለዕረፍት ሄደው የደም ግፊቱ ስለባሰባቸውና በበሽታቸውም አስጊነት የተነሳ ለህክምና ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው እዚያው እንዳሉ መንግሥት ተገለበጠ።

ባለቤታቸው ልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ ጎበዝና ሥነ ሥርዓት ያላቸው ልዕልት ከመሆናቸውም ባሻገር ልጆቻቸውን በሥርዓት ያሳደጉ እናትም ናቸው።

ተፈሪ መኮንን ትልቁ ልጃቸው
አልጋውን ለመውረስ ያስባል ልባቸው
የኋለ የኋላ ሐቲማም የላቸው
ሸዋ ክፉ ሰው ነው ተሥር ነቀላቸው
ዳግሚያ እንዳይነሱ ተነልጅ ልጃቸው
ሼህ ሁሴን ጅብሪል

## ልዕልት ዘነበ ወርቅ

ልዕልት ዘነበ ወርቅ ሐምሌ 18 ቀን 1909 ዓ.ም. ተወለዱ። ልዕልት ዘነበ ወርቅ ከአፄ ዮሐንስ የልጅ ልጅ ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ጋር ተጋብተው ሲኖሩ ቆይተው በወሊድ ሞቱ። ልዕልት ዘነበ ወርቅ ከሞቱ በኋላ 'የልጃችንን የወግ ዕቃ አምጥተህ አስረክበን' በመባሉ ደጃች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ቅሬታ አቁሮ ይኖር ነበር። ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ቅምጥል የነበረ በጠላት ወረራም ወቅት ጣሊያኖች ትግራይን በሙሉ



ለእኔ ይሰጡኛል ብሎ ለጣሊያን ያደረ ሲሆን ከጣሊያን ድል በኋላ በግዞት ኢሉባቦር ከዚያም በቁም እስር አምቦ ላይ ቆየ። በደርግ ጊዜ ከተፈታ በኋላ የተፈጥሮ ሞት ሞተ።

## ልዕልት ፀሐይ

ልዕልት ፀሐይ ጥቅምት 2 ቀን 1912 ዓ.ም. ተወለዱ። ልዕልት ፀሐይ ጥሩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ስለነበራቸው ከጣሊያን ወረራ በፊት በአስተርጓሚነት አባታቸውን አገልግለዋል። በጣሊያን ጊዜ ከአባታቸው ጋር በስደት እንግሊዝ አገር ሄደው የነርስነት ሙያ ተምረዋል። ከስደት መልስ በዚሁ ሙያ ሲያገለግሉ ቆይተው ነቀምት ሆስፒታል ውስጥ በወሊድ ሞቱ። ባለቤታቸው ጀኔራል ዓብይ አበበ በደርግ ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች አንዱ ናቸው።

ለልዕልቲቷ መታሰቢያ ተሰይሞላቸው የነበረውን የልዕልት ፀሐይ ሆስፒታልን ደርግ የጦር ኃይሎች ሆስፒታል ብሎ መጠሪያውን ለውጦታል።



ልዕልት ፀሐይ ከወንድማቸው ከልዑል መኮንን

## ልዑል መኮንን

ልዑል መኮንን ጥቅምት 5 ቀን 1916 ዓ.ም ተወለዱ። ልዑል መኮንን ኃይለ ሥላሴን አባታቸው ከእንጀት የሚወዷቸውና ከልጆቻቸውም መካከል የሚያቀርቧቸው ስለነበር የሚደፍሯቸውና አንተ የሚሏቸው ልጃቸው ነበሩ። የሐረር ገዥ አድርገው ሾመዋቸው እንደ እንግሊዞች አጠራር 'የሐረር ዱክ' እያሉ ይጠሯቸው ነበር። ሐረር ከተማን ከሚከበው አጥር ላይ ካሉት አምስት በሮች መካከል አንዱ በእሳቸው ማዕረግ ዱክ በር በመባል እሁንም ይታወቃል።

ከልዕልት ማራ ግዛው ጋር ተጋብተው
አምስት ወንዶች ልጆች ወልደዋል። ልጆቹም

ልዑል ወሰን ሰገድ
ልዑል ሚካኤል
ልዑል ተፈሪ
ልዑል ዳዊት (መኮንን መኮንን)
ልዑል በዕደ ማርያም ናቸው


ወይዘሮ ምሕረት መኮንን

ልዕልት ማራ ግዛው የጥላሁን ግዛው ታላቅ እህት ናቸው። ጥላሁን የዩንቨርስቲ ተማሪዎች ፕሬዚዳንት ሆኖ በአንድ የከብር ዘበኛና በአንድ የፖሊስ መኮንን ቅንብር በጥይት በ1962 ዓ.ም ተገደለ።

ልዑል መኮንን ከጋብቻ ውጭ ወይዘሮ ምሕረትንና አቶ እስክንድርን ወልደዋል። ምንም እንኳን ስለ ወይዘሮ ምሕረት የራሳቸው የጃንሆይ ልጅ ናቸው የሚል ሃሜት ቢኖርም ባለቤታቸው ጄኔራል ግርማ መንግሥቱን አነጋግሬ አስተባብለውልኛል። አቶ እስክንድር ሕመምተኛ ስለነበሩ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ልዑል መኮንን ቸርና በጣም ደግ ሰው እንደነበሩ ተጋንኖ ይወራላቸዋል።


ልዑል ወሰን ሰገድ መኮንን

በ1949 ዓ.ም ጃንሆይ ሲዳሞ ለጉብኝት በሄዱበት ወቅት ልዑል መኮንንም ወደ ሲዳሞ በመኪና ከራስ መስፍን ጋር ሲሄዱ ሞጆ ላይ አደጋ ደርሶባቸው ሞተው ታላቅ ሃዘን በኢትዮጵያ ውስጥ ተደረገ። በዚህም ሃዘን ሳቢያ ወንዱ ጥቁር ጨርቅ ሴቶች ከል እንዲለብሱ ፖሊስ አልፎ አልፎ ያሳስብ ነበር። በሃዘኑ ምክንያት የመንግሥት የጽሕፈት ወረቀቶች በሙሉ በጥቁር የተከበቡ እንዲሆኑ ተደርጓል። በዘፈንና በመዝናኛ ሙያ የተሰማሩ ሁሉ ለስድስት ወራት ሥራቸውን ማቋረጥ ግድሆኖባቸው ነበር።



ስለ ልዑል መኮንን አሟሟት ብዙ ቢወራም በመኪና አደጋ ለመሞታቸው እርግጠኛ መሆኑን በማጣራት ለማወቅ ችያለሁ።


ከልዑልነታቸው ሞት በኋላ ለስማቸው መታሰቢያ ሆስፒታል ማሠሪያ አዋጡ ተብሎ ብዙ ገንዘብ ተሰበሰበ። በተለይ ደሞዝተኛ የኾነ ሁሉ የአንድ ወር ደሞዙን በአሥራ ሁለት ወር እንዲከፍል ስለተወሰነ 10% ከከፈሉት ከአየር ኃይል ሠራዊት በስተቀር ሁሉ ደሞዝተኛ ከፍሏል። በተጨማሪም ገበሬውም፣ ነጋዴውም ሳይቀር የተቻለውን ያህል በውዴታ እንዲከፍል ተደርጓል። በተሰበሰበው ገንዘብ ቀድሞ የራስ ቢትወደድ ተሰማ ናደው ወይም ስኳር ሜዳ ይባልየነበረው በኋላ ለዩኒቨርስቲ በተከለለው ቦታ ላይ በልዑል መኮንን ስም ሆስፒታል ተሠራ። መጨረሻ ላይ ግን በዩጎዝላቪያና በስዊስ (በስዊትዘርላንድ) መንግሥቶች ከፍተኛ ዕርዳታ ጭምር ሆስፒታሉ አልቆ ተከፈተ።

ደርግ ሥልጣን እንደጨበጠ የንጉሡ ነገሥቱንና የቤተሰቦቻቸውን ስም ለማስወገድ ባደረገው ዘመቻ ሆስፒታሉን የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብሎ ሰየመው። ሆስፒታሉ በሕዝብ መዋጮ የተሠራ ሲሆን መንግሥት ወርሶ ባለቤት መሆኑና ስሙን ያለሕዝቡ ፈቃድ መቀየሩ ለብዙ ሰዎች እስከ አሁን ድረስ ቅሬታ እንዳሳደረባቸው ነው። ሌሎችም በልዑሉ ስም ተሰይመው የነበሩትን ትምሕርት ቤቶች ደርግ ስማቸውን ለውጦታል። አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን የልዑል መኮንን ት/ቤት 'አዲስ ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤት' ብሎታል። በሐረርና እንዲሁም በሌላ ቦታ በልዑሉ ስም የተሰየሙትን ትምሕርት ቤቶችም ደርግ ስማቸውን ቀይሮታል።

ጃንሆይ ልዑል መኮንንን እንደሚወዱ ሁሉ አምስቱን የልዑል መኮንንን ወንዶች ልጆች በአባታቸው ዓይን እየተመለከቷቸው በጣም ይወዷቸው ነበር። ልጆቹም ጃንሆይን በእንግሊዝኛ ትልቁ አባባ (Grand Pa) ይሏቸው ነበር። መንግሥት በተለወጠበት ወቅት ያለጥፋታቸው በመወሰድ ብቻ እስከ አሥራ አምስት ዓመት ድረስ ታስረዋል። ከአምስቱ ልጆች መካከል የመቶ አለቃ መኮንን መኮንን በስደት ላይ ሞቷል። ሌሎቹም በአገር ውስጥና በውጭ አገር በትምሕርትና በሥራ ላይ ይገኛሉ። ከልዑል መኮንን ልጆችም ኾነ ከንጉሣውያን ቤተሰብ ልጆች መካከል ልዑል በዕደ ማርያም በአስተዋይነቱ ሞዓ አንበሳ ለንጉሥነት ከሚመርጣቸው አንዱ ተወዳዳሪ እንደ ኾነ ይወራል።

በውልደትም ከልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን ልጆች በመቀጠል ለዙፋኑ የሚቀርቡት የልዑል መኮንን ልጆች ናቸው።

## ልዑል ሣህለ ሥላሴ



ልዑል ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ

*ልዑል ሣህለ ሥላሴ የካቲት 20 ቀን 1923 ዓ.ም ተወለዱ። ዘመኑ ጃንሆይ የንግሥ በዓላቸውን የፈጸሙበት ወቅት ነበር። ወንድ ልጅ ሲወለድ መተኮስ የአገሩ ልምድ ስለ ኾነ ልዑል ሣህለ ሥላሴ የተወለዱ ዕለት ማታ የጥይት እሩምታ ከቤተ መንግሥት ተሰማ። አንዳንድ ሰዎች ሽጉጥና ጠመንጃቸውን ለመሞከር ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ስላገኙት ከተማው በሙሉ ሲናወጥ አደረ። በማግስቱ ምክንያቱ ሲጠየቅ ወንድ ልጅ በቤተ መንግሥት ስለተወለደ ነው ተባለ። የዚህን ጊዜ ሰው ለአዲሱ ልጅ "አሸብር" ብሎ ስም አወጣለት። ልዑል ሣህለ ሥላሴ በቤተዘመድ ደረጃ አሸብር እየተባሉ ለአጭር ጊዜ ተጠርተውበታል።

ለጃንሆይ ትንሹና መሳይ ልጃቸው ሣህለ ሥላሴ ሲሆኑ ጃንሆይ ግን ትንሹንና መሳይ ልጃቸውን እንደ ልዑል መኮንን አላስጠጓቸውም።

ልዑል ሣህለ ሥላሴ እንግሊዝ አገር እንደ ራስ መንገሻ ሥዩምና እንደ አቶ ዓለማየሁ ወልደ ሥላሴ (የጃንሆይ አኅት ልጅ) የካርታ ሥራ ቅየሳ (SURVEYING) ተምረው ተመረቁ። በዚያን ወቅት ብልህና ጎበዝ መሆናቸውን የሚገልጽ ሪፖርት ሲመጣ ብዙ ገንዘብ ተላከላቸውና የቀረውን ጊዜ እንግሊዝ አገር በመዝናናት አሳለፉ። እንደተመለሱም የኢትዮጵያ አየር ኃይል ትምሕርት ቤት ገብተው



የአብራሪ ክንፍ አገኙ። ሆኖም እያደር የባሕርይ ለውጥ ማሳየት ጀመሩና በከባድ ሥራ ላይ ሊሠማሩ አልቻሉም። ለማንኛውም የጋሞ ጎፋ አገረ ገዥ ሆነው ቢሾሙም በወኪል አገሩ ሲተዳደር እሳቸው እዚሁ አዲስ አበባ በመዝናናት ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር።

የሬዲዮ አማተር ስለነበሩ የመንግሥቱ ንዋይን መንግሥት ግልበጣ መልዕክት ለጃንሆይ ያስተላለፉ እሳቸው ነበሩ። ባልታወቀ ምክንያት ደስታ ያልነበራቸው ስለነበሩ የሚኖሩት ከመንግሥት በሚያገኙት ገንዘብ እንጂ ምንም ሥራ ውስጥ አይሳተፉም ነበር። ሆኖም በልጅነት ዕድሜያቸው ታመው በ1954 ዓ.ም አረፈዋል።

የወለጋ ባላባት የኩምሣ ሞረዳ (ደጃዝማች ሃብተማርያም) ተወላጅ የሆኑትን ልዕልት ማሕጸንተን አግብተው ልዑል ኤርምያስን ወልደዋል። ልጃቸው ልዑል ኤርምያስ አሁን በአሜሪካና በእንግሊዝ አገር ነዋሪ ሲሆን የይሁዳ አንበሳ ፓርቲ የወቅቱ ሊቀመንበር ነው። ንግሥና እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ ቢመለስ ለመንገሥ ከተሰለፉት አንዱ ልዑል ኤርምያስ ነው።



ልዑል ኤርሚያስ ሣህለ ሥላሴ

ልዑል ኤርምያስ ቁመናውም አረማመዱም እንደ አያቱ ዓይነት ነው። ወደ ውጭ ከመሄዱ በፊት ጀርመን ትምሕርት ቤት ይማር ስለነበረ ከአማርኛ ሌላ ጀርመንኛና እንግሊዝኛ የሚናገርና የሚጽፉ መሆኑ ግልጽ ነው።

ልዑል ኤርምያስ ቢነግሥ ምናልባት በሁለቱ ግዙፍ የአማራና የኦሮሞ ብሔሮች መካከል የበለጠ መግባባት ይፈጥር ይሆናል ተብሎ ይገመታል። በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው የሁለት ጎሣዎች ልጆች በመጋባታቸው ሰው እንደሚያስበው የሚከሰተው መግባባት በቻ ሳይሆን አንዳንዴም በተቃራኒው ሊሆን ይችላል። በንጉሥ በካፋ የልጅ ልጅ በኢዩአስ ዘመነ መንግሥት በቋራና በየጁ መካከል የተነሳው አለመግባባት መንግሥቱን አዳክሞ ኢዩአስንም በሻሽ

አሳንቆ አስገድሎታል። የልዑል ኤርምያስ ታሪክ ከንጉሥ ኢዩአስ ጋር ተመሳሳይነት ይኖረዋል።

መቼም ከእንግዲህ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ንጉሥ ለማንገሥ ቢያስቸግርም ሊሆን የሚችለው በአራት ምክንያቶች ብቻ ነው።

1ኛ አገሪቱ የተወሳሰበ ችግር ውስጥ ገብታ ከችግሩ ለመውጣት የሚረዳበት ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ።

2ኛ ነጻ መግባባት ተደርሶ ከፕሬዚዳንት ይልቅ ባህልን የተከተለ የብሔራዊ አምበል የኾነ ንጉሥ ያስፈልጋል ተብሎ በውይይት ሲታመንበት።

3ኛ የንጉሥ አገዛዝ ደጋፊዎች በምርጫ ወይም በሌላ ዘዴ የፖለቲካውን ሥልጣን እጃቸው ማስገባት ከቻሉ።

4ኛ የንጉሥ አገዛዝ የሚደግፍ ፓርቲ ወይም ማኅበር ፍልስፍናውን ለሌሎች ፓርቲዎች ለማሳመንና ሕገ መንግሥቱ ውስጥ ንግሥና እንዲጠቃለል ለማድረግ ከቻለ ብቻ ነው።

ይህም ሆኖ ከእንግዲህ ወዲህ ንጉሥም ተብሎ አንድ ሰው ቢሾም ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ እንጂ ፈላጭ ቆራጭ ሊሆን በምንም ዓይነት አይችልም። በኃይል ተጠቅሜ ፈላጭ ቆራጭ ልሁን ብሎ ቢነሳም እንደ ፈረንሳዩ ንጉሥ ሉዊስ 17ኛ በአሳፋሪ ሁኔታ ሊወገድ ይችላል።

## ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ

አቶ ነብየ ልዑል ክፍሌ በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት በረዳት ሚኒስትር ማዕረግ የሕዝብ ደህንነት ባለሥልጣን ነበሩ። አንድ ጊዜ "ሳይወለድ የሚመስል፣ ተወልዶ የማይመስል አለ" ብለው መናገራቸው ይታወሳል። በተለይ አንድ ትልቅ ጀግና ወይም ታዋቂ ከበርቴ ሰው ሲሞት ብዙ ጊዜ ልጅ ነን ባዮች ከየቦታው ብቅ ብቅ ማለት ይጀምሩና ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። በዚህ መካከል ዕውነተኛ የሆነም ያልሆነም ሊኖር ስለሚችል ትመልካች መፍረድ ያስቸግረዋል። በትግራይ ባህል አንዲት ሴት እያወቀች ልጁ ያልሆነውን ልጅህ ነው ተቀበል ብላ የወለደችውን ልጅ አባትነት ለትልቅ ሰው ስትሰጥ ዞር ብላ ለጓደኞችዋ "ልጁ ጠጅ ይጠጣ ብዬ ነው" ትል ነበር። ምክንያቱም ድሃ አባት ብትሰጠው ሲያድግ ጠጅ



ሊጠጣ ስለማይችል ነበር። ብዙውን ጊዜ እንዲህ ዓይነት ነገር የሚከሰተው ወላጅ እናቶች ሲሞቱ በሚተውት ኑዛዜ ይሆናል። ዛሬ የህክምና ሙያ ሳይንስ በመራቀቁ የወላጅና የተወላጅ ዲ ኤን ኤ ሊመሳከር ስለሚችል የማጣራቱ ሁኔታ እየቀለለ መጥቷል።

አንድም ስለሃቅ አንድም ለንብረት ክፍያ አንድም ለዝና ከጃንሆይ መወለድ እንደ ትልቅ ነገር ስለሚታይ ሰዎች ልጅ ነን ቢሉ አያስገርምም። በሌላ በኩል ጃንሆይ በዘመናቸው ስለሚፈሩና እንደልዩ ፍጡር ስለሚታዩ ዕውነትም ልጅ ቢሆን ስለሚያስፈራ ከሞታቸው በኋላ ቢመጣ ላያስደንቅ ይችላል። የሁንና አንድ ልጅ ከጋብቻ ውጭ ከተወለደ ለአባቱ ክብር ሲባል ብቻ ልጁን አባት አልባ ማድረግ ፍትሓዊ ስለማይሆን መዝርዘሩ ተገቢ እንደመሆኑ መጠን እኔም የጃንሆይ ልጅ ናቸው የሚባሉትን ሁሉ መርምሬ የደረስኩበትን እንደሚከተለው ዘርዝሬያለሁ።

## ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይለ ሥላሴ


ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከጋብቻ በፊት ከወሎዬዋ ወ/ሮ ወይኒቱ አመዴ ልዕልት ሮማን ወርቅን ወልደዋል። ልዕልት ሮማን ወርቅ ደጃዝማች በየነ መርዕድን አግብተው ደጃዝማች መርዕድ በየነንና ልጅ ሳምሶን በየነን ይወልዳሉ።

ባለቤታቸው ደጃዝማች በየነ መርዕድ በጣሊያን ወረራ በደቡብ በኩል ሲዋጉ ተገደሉ። ልዕልት ሮማን ወርቅም ተማርከው ወደ ጣልያን አገር ቶሪኖ ከተወሰዱ በኋላ በሕመም ምክንያት ጥቅምት 4 ቀን 1933 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

የልዕልት ሮማን ወርቅን አስከሬን ለማስመጣት በቫቲካን የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር የነበሩት አቶ ማርቆስ ኢጋጅየለው ጃንሆይን ቢያሳስቧቸው "ወይድ! አያገባህም" ብለው ተቆጡና አስከሬኑ ሳይመጣ ቀረ።

# አቶ ኪዳኔ ተፈሪ

ከንጉሡ ነገሥቱ ህልፈተ ሕይወት በኋላ ከጋብቻ ውጭ የተወለድሁ ለጃቸው ነኝ የሚሉት አቶ ኪዳኔ ተፈሪ ብቅ ብለው ስለአወላለዳቸው የሚከተለውን ገልጸዋል። አቶ ኪዳኔ ተፈሪ የተወለዱት ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚሠሩት ከወይዘሮ ይመኙሻል ክብረት መሆኑ ባይካድም ጃንሆይ ክብራቸውን የሚጠብቁ ስለሆኑ ከሴትየዋ ጋር የመገናኘታቸው ዕድል አይኖርም በማለት ነገሩን የሚያጣጥሉት ብዙ ናቸው። ነገር ግን አንድ አጋጣሚ ይጠፋል ብሎ መደምደም የዋህነት ነው። ነገሩን ችላ ለማለት ደግሞ አንድ በመሃሉ የተወለደ ልጅ ስላለ ለአባቱ ክብር ተብሎ የሱን ያላባት መቅረት ችላ ማለት በደል ስለሚሆን ነገሩ መነሳትአለበት።



አቶ ኪዳኔ ተፈሪ

ፎቶግራፋቸውን የተመለከተ ሰው "ይህ ሰው ዕውነትም ይመስላቸዋል" የማይል የለም። ያደጉትም እስከ ሰባት ዓመታቸው ቤተ መንግሥት ውስጥ ሲሆን ከሰባት ዓመት በኋላ ራስ እምሩ ቤት እንደነበርና ባለመስማማት ምክንያት እናታቸው እህት ዘንድ ሄደው ማደጋቸውን አስረድተዋል። አንድ ልጅ ያላቸውና ደርግ በጠራው ዘመቻ ላይ ተሳትፎ ሁለት እግሩን ተመቶ እሳቸው ዘንድ በፊት በቀለም ቀቢነት በሚያገኙት በኋላ ግን በአርጅና ዘመን ደግሞ በልመና የሚያገኙትን እየተካፈለ እንደሚኖር አስረድተዋል። ግንቦት 27 ቀን 1994 ዓ.ም በሰባ ዓመታቸው ሞተው በቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስከሬናቸው አርፏል።



# መንግሥቱ ግርማ



አቶ መንግሥቱ ግርማ

አቶ መንግሥቱ ግርማ ግንቦት 13 ቀን 1936 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። አባቱ አቶ ግርማ ልዑል አልጋ ወራሽ መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ግቢ ይሠሩ የነበሩ ናቸው። እናቱ ከአርመናዊ አባትና ከኢትዮጵያዊት እናት የተወለዱ ሲሆኑ መልከ መልካም ነበሩ። እንደሚባለው አቶ መንግሥቱ ግርማ የተወለደው ከጃንሆይ ሲሆን እንዲያውም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት አሁን የውል ክፍል የሚባለውን ቤት ጃንሆይ ለልጅሽ ማሳደጊያ ይሁንሽ ብለው ለእናቱ የለጧቸው ነው ይባላል። ሕዝቡ ግን የአልጋ ወራሽ ልጅ ነው እያለ ይንሾካሾክ ነበር። መንግሡቱ ግርማ መልከ መልካምና ቀይ ሲሆን ያደገው በራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ስለነበረ በመሃል አራዳ የታወቀ ልጅ ነበር። በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ሲሠራ ኖሮ መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ መሥሪያ ቤት የፔርሶኔል መምሪያ ኃላፊ በመሆን አገልግሏል።

አቶ መንግሥቱ ግርማ በድንገት ጥቅምት 13 ቀን 1987 ዓ.ም አርፎ በቅዱስ ዮሴፍ መካነ መቃብር አስከሬኑ አርፏል። በአሁኑ ወቅት ባለቤቱ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ግረማና ሦስት ወንዶች ልጆቹ የሚኖሩት አሜሪካን አገር ነው።

# ትዕግሥት ካሣና ቴዎድሮስ ካሣ

ወይዘሮ አስገደች አበራ የሚባሉ ሊሞቱ ሲሉ ንስሓ ልግባ ብለው ዘመድ ሰብስበው ልጆቼ ትዕግሥት ካሣና ቴዎድሮስ ካሣ የተወለዱት ከጃንሆይ ስለኾነ እስከ ዛሬ በመፍራት ሳልናገር ቆይቻለሁ። አሁን ግን ትክክሉን ይወቁት ብለው ተናገሩ። ወይዘሮ አስገደች የሚሠሩት በቤተ መንግሥት የቤት ዝግጅት ከመሆኑም በላይ ጃንሆይ ወደ ውጭ አገር ለጉብኝት በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ አብረው ይመላለሱ ነበር። ባለቤታቸው አቶ ካሣ ገበየሁ በዩጋንዳ ኤምባሲ የሚሠሩ ከወይዘሮ

አስገደች አራት ልጆች ሲኖሩዋቸው ትዕግሥትንና ቴዎድሮስንም አባት ሆነው አሳድገዋል። ሰውየው እንደተብከነከኑ ኖረው መጨረሻ ላይ በጥርስ ኢንፌክሽን መዘዝ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የስድስት ልጆቻቸውን ገጽታ ለተመለከተ እነዚህ ሁለት ልጆች አጠርና ለየት ይላሉ።

## ወይዘሮ ትዕግሥት ካሣ

በአስተዳደርና በሕዝብ ግንኙነት የቢኤ ዲግሪ ያላቸውና አሁን ደግሞ ስዊድን አገር ለማስትሬት ዲግሪ የሚያደርስ ውጤት እንዳላቸው ተናግረዋል። ቀደም ብሎ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ከስድስት ዓመት በላይ የሠሩ ናቸው። አሁን ሚስተር ስቬን ማግኑሰን የሚባሉ ስዊድናዊ አግብተው ስዊድን አገር ውስጥ በትዳር ይኖራሉ። በአውሮፓውያኖች ባህል መሠረት የሚጠሩትም ሚስስ ማግኑሰን እየተባሉ ነው።



ወ/ሮ ትዕግሥት ካሣ

በትርፍ ጊዜያቸው ስፖርተኛ ስለነበሩ የእቴ መላ ምቺ የሴቶች የእግር ኳስ ቡድንን በ1967 ዓ.ም ከመሠረቱት አንዷ ከመሆናቸውም በላይ የቡድኑ 8 ቁጥርና አምበል ነበሩ።

ወይዘሮ ትዕግሥት በመኪና አደጋ ከተለዩዋቸው የቀድሞ ባላቸው አቶ ምስክር ወልዴ የወለዷት የወይዘሪት ብሌን ምስክር እናት ሲሆኑ ልጅቷ በአሁኑ ወቅት ፈረንሳይ አገር በትምሕርት ገበታ ላይ ትገኛለች። ከሚስተር ማግኑሰን ልጅ እንደሌላቸው ተናግረዋል።

ትዕግሥት ልጅ በነበሩበት ጊዜ ጃንሆይ በጣም የሚያቀርቧቸው እንደነበሩና በዘጠኝ ዓመት ዕድሜያቸው እንግሊዝ አገር እንዲሄዱ ፓስፖርት ከወጣ በኋላ እናትየዋ ስላለቀሱ ጉዞው ቀረ። የልጅነታቸውን ሁኔታ ብርጋዲዬር ጄኔራል ዳንኤል መንግሥቱ እንደሚያውቁ ተደርሶበታል።



## አቶ ቴዎድሮስ ካሣ -

አቶ ቴዎድሮስ የተወለዱት በ1958 ዓ.ም ነው። ከሁለተኛ ደረጃ ትምሕርትበኋላ ለሁለት ዓመት ያሬድ የሙዚቃ ትምሕርት ቤት ተምረው በአ.አ. ዩንቨርሲቲ የባህል ማዕከል ለሰባት ዓመት ሠርተዋል። አንድ ዓመት ኬንያ ውስጥ በኮንትራት ሥራ ቆይተው ተመልሰዋል። ሴቫንስ ከሚባል ባንድ ጋር በከበሮ መችነት በሚጫወቱበት ጊዜ ድምጻቸውም በካሴት ያስቀረጹ መሆኑን ነገረውኝ ነበር። ፀጉራቸው ገባ ከማለቱ በስተቀር የወላጅ አባታቸውን መልክና አካል የያዙ ናቸው።



አቶ ቴዎድሮስ ካሣ




ቢዛ ቴዎድሮስ

አቶ ቴዎድሮስ የአንጀት ቁስለት (አልሰር) በሽታ ያሰቃያቸው እንደነበረና ሲታከሙ ቆይተው ሚያዝያ 7 ቀን 1995 ዓ.ም በመሞታቸው አስከሬናቸው በቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አርፏል። ቤዛ ቴዎድሮስ የምትባል የአራት ዓመት ዕድሜ ያላት ሴት ልጅ አለቻቸው።

## አቶ መክብብ አበበ

አቶ መክብብ አበበ በ1965 ዓ.ም የተወለደ ሲሆን አሁን የሚተዳደረው አዲስ አበባ ውስጥ በታክሲ ነጅነት ነው። እናቱ ወይዘሮ ንጋቷ ቤተ መንግሥት ውስጥ የሚሠሩና የሻለቃ ታደሰ ጎሹ የቤተ መንግሥት አንጋች ልጅ የነበሩ ናቸው።



አቶ መክብብ አበበ

አቶ መክብብን ያሳደጉት ጄኔራል ወርቁ ዘውዴ ናቸው። የሚጠራው ግን በወይዘሮ ንጋቷ ታደሰ ባለቤት ወይም በእንጀራ አባቱ በአቶ አበበ ወልዴ ሲሆን እሳቸውም ዳኛ ነበሩ። በዚሁ ልጅ መወለድ ምክንያት በነበረው አለመግባባት ባልና ሚስቶቹ ተፋቱ። ከተፋቱም በኋላ አቶ አበበ ቂም ቋጥረው በደርግ መንግሥት ጊዜ ሴትየዋን ወንጅለው ነበር።

መክብብ የጃንሆይ ልጅ መሆኑን ቢያውቅም አንዳንዶች ገና እሳቸውን ትመስላለህ እንደሚሉት ይናገራል። መጨረሻ ላይ ግን በደንብ የጃንሆይ ልጅ መሆኑን የተረዳው ወይዘሮ ትዕግሥት ቢሆነኝ በግልጽ ስለነገሩትና ወንድሞቹም ከአቶ ተሰፋዬ ወልደ ሥላሴ ከሚባሉ የቤተ መንግሥት ሠራተኛ ሰምተው ስላረጋገጡለት ነበር።



በግራ በኩል የቆሙት ወ/ሮ ንጋቷ ታደሰ ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር

ይህንን ሁኔታ እንደተረዳ አንድ ቀን "ልዕልት አይዳን ይሁን ልዕልት ሰብለን አላውቅም እንደኛቸው ቤት ድንገት ዘው ብዬ ገብቼ ማነጋገሬን አስታውሳለሁ" ብሏል። ሁኔታውን ሲገልጽ ደነገጡና "ግን እኛ የምናውቀው ነገር የለም ምን እናድርግ" ብለው መልሰውለታል።



"ለልዑል ኤርሚያስ ደብዳቤ ጽፌ መልስ አላገኘሁም" ብሎም ተናግሯል።

## ሁለት ልጆች

በሰበታ መንገድ ቤተ ሳሊሆም የምትባል የሴቶች ገዳምን ለመጎብኘት እቴጌ መነን ሲሄዱ አንዲት ቅጠል በመልቀም ላይ ያለች ልጅ እጇን እያውለበለበች ሠላምታ ስትሰጣቸው ጊዜ ወደዋት ወሰዷትና እቴጌ መነን ትምህርት ቤት አስገቧት። እዚያ በመማር ላይ እያለች ለልዑል መኮንን ልጆች ሞግዚት እንድትሆን ወደ ቤተ መንግሥት ተወሰደች። ይህች ልጅ ስሟ ፀሐይ መገርሣ ይባላል። ቤተ መንግሥት ውስጥ እያገለገለች ስትኖር በመካከሉ ሁለት ልጆች ወለደች። በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ለነበሩት ለአቶ ሐጎስ ባህታ ተዳረች። ሠርጉም የተካሄደው በጊዮን ሆቴል ሲሆን በዓይነቱ የተለየ ስለነበረ ልዕልት ተናኘ ወርቅ በጉዳዩ ያልተደሰቱበትም ምክንያት በተለይ አባታቸው ጃንሆይ ሙሽሮቹን እስከ ሰበታ ድረስ በመሸኘታቸው ነበር። በመጨረሻም ወይዘሮ ፀሐይ ከነባለቤታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ በሥራ ተዛውረው ሄደዋል። ሃሜቱ ሁለቱ ቤተ መንግሥት የተወለዱትን ልጆች የጃንሆይ ናቸው የሚል ነው። በንብረት በኩል ወይዘሮ ፀሐይ በአሮጌ አይሮፕላን ማቢያ አካባቢ መሬት ተሰጥቷቸው ቤት እንደሠሩበት ይታወቃል።

## ሰሎሞን ሠርፀ ወልድ



ሰሎሞን ሠርፀ ወልድ

ወይዘሮ የውብዳር ድፋባቸው የሚባሉ የአቶ ሠርፀ ወልድ ባለቤት የቤተ መንግሥት ሠራተኛ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ዕድሚያቸው 82 ዓመት ነው ተብሏል። ከበርካታ ልጆቻቸው መካከል ትንሹ ወንድ ልጃቸው ሰሎሞን የጃንሆይ ልጅ ነው ይባላል። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ በህመም ምክንያት ንግሥት ዘውዲቱ ሆስፒታል ገብቶ እያለ የጃንሆይ ልጅነቱ በሆስፒታሉ ውስጥ በሰፊው ስለተወራ

እንዲት ነርስ ስጋት ገብቷት ቤተሰቦቹን በማሳሰብዋ ልጁ ሳይድን ከሆስፒታል ወጥቶ በድብቅ ታክሞ ለመዳን በቅቷል።

እያደር ሰሎሞን ሠርፀ ወልድ የጃንሆይ ልጅ መሆኑ በሰፊው ስለታወቀ እንደምንም ብሎ ወደ አሜሪካን አገር ሄዶ እሁን ድረስ እዚያው ይኖራል።

ከቤተሰቦቹ ለማረጋገጥ እህቱንና ወንድሞቹን ብናነጋግራቸውም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ እንዲሉ የጃንሆይ ልጅነቱን ለማረጋገጥ አልፈለጉም። እንደተረዳነው ዘመዶቹ ጥቅም ለሌለው ነገር ሰሎሞንን ከአብሮ አደግ ወንድሞቹና እህቶቹ ላለመነጠልና ለደህንነቱ በማሰብ የጃንሆይ ልጅነቱን ላለመቀበል የወሰኑ ይመስላል። ይሁንና ሰሎሞን በልጅነቱ በቤተ መንግሥት ማደጉና መልኩም እንደሚታማው ጃንሆይን መምሰሉን ደርሰንበታል። እናቱም ለልጁ ማሳደጊያ ወርሃዊ የገንዘብ ድጎማ ያገኙ ነበር ተብሏል።

በአጠቃላይ ስለተለያዩ ሌሎች ልጆች ብዙ ቢባልም በከፊል እንኳን ተአማኒነት የሚያሳድር ፍንጭ የሌለው ስለሆን አልፈዌለሁ።



# ምዕራፍ ፴፯

# የውዳሴ ከንቱ አስተዳደር

## በጎ አድራጎት

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከ1913 ዓ.ም ጀምሮ በየወቅቱ የዕርዳታ ድርጅቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ የጡረታና የነዳያን መርጃና መማሪያ ድርጅቶችን ሲያቋቋሙ ኖረው መጨረሻ ላይ በ1945 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት በሚል ስም ተጠቃለው አንድ ተቋም ተመሠረተ። ለነዚህም ድርጅቶች የገንዘብ ምንጭ የሆኑት የግል ርስት፣ የግል ገንዘብ፣ ግለሰቦች የሚያበረክቱት ዕርዳታ፣ የውጭ አገር ሰዎችና ድርጅቶች ስጦታ፣ ከብሔራዊ ሎተሪ፣ ከመንግሥት ወጪ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ የልደት ስጦታ ወዘተ.. ናቸው።

አንድ ንጉሥ ወይም ንጉሠ ነገሥት የመንግሥት ቋሚ ሠራተኛ እንጂ ነጋዴ ወይም ሃብታም ገበሬ ወይም ከብት አርቢ አይደለም። ከ13 ዓመት ዕድሜ ጀምሮ የአስተዳደር ሥራ እየሠራ የኖረ መሬት ካልነጠቀ፣ ወይም የመንግሥቱን ገቢ ወደ ግል ሃብትነት ካላዞረ፣ የጠላት ንብረትን ለግሉ ካልወሰደ፣ ወይም ከመንግሥት ካዝና እያዘዘ ካልሰጠ፣ እንዴት ከበርቴ ሊሆን ይቻላል ብሎ ስለሚያስብ፣ ጃንሆይ በየወቅቱ ከግል ሃብታችን ይኸን ሰጠን ቢሉም ለተማረው ክፍል አልተዋጠለትም። እንዲያውም እንዴት ዘርፈውን ኖሯል የሚያሰኝ አስተሳሰብ ላይ ጥሎታል።

ሰው ሁሉ በአንድ ዓይነት ሊያስብ አይችልም። አንዳንዶች በንጉሡ ችሮታ ሲረኩ አንዳንዶች እንዴት ይቀለድብናል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። ስለሆነም ይሻል የነበረው ድርጅቱን በንጉሠ ነገሥቱ ስም ሰይሞ፣ አንድ የመንግሥት አካል አድርጎ፣ በበጀትና በዕርዳታ አሰባሰብ ቢተዳደር የተሻለ ነበር። በየልደት በዓላቸውም ውስጡን ግዴታ ላዩን በፈቃድ ስጦታ

እየተባለ የሚሰበሰበውን ባይቀበሉ ጥሩ ነበር። እንዲህ ዓይነት ስጦታ የሚቀነባበረው በልወደድ ባዮች መሆኑ አያጠራጥርም።

ይህ የበጎ አድራጎት ድርጅት ገና ሲቋቋም ለሠራተኞች ደመወዝ ይከፈል የነበረው ከገንዘብ ሚኒስቴር እየታዘዘ ነበር። አስከትሎም የዚህን ድርጅት የሃብት ምንጭ ስንመለከት እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን።

1ኛ የቀዳሚ የግል ርስት(ቤተ ርስት)
2ኛ የቀዳሚ የገንዘብ ችሮታ
3ኛ ግለሰቦች ያበረከቱት ንብረት
4ኛ የውጭ ድርጅቶች ያበረከቱት ንብረት
5ኛ የጠላት ንብረት
6ኛ የብሔራዊ ሎቶሪ
7ኛ ከመንግሥት የተፈቀደ ገንዘብ
8ኛ ሕዝብ ያዋጣው ገንዘብ
9ኛ ለንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠ የልደት ስጦታ ተሸጦ የተገኘ ገንዘብ
10ኛ ከካዚኖ ገቢ (ራስ እንዳርጋቸው ቤት ውስጥ በኋላ ሆራ ራስ ሆቴል)
11ኛ ከጦር መሣሪያ ሽያጭ (ጋሻ ፒያሳ ብሉቢልዲንግ)
12ኛ በድርጅቱ የሚተዳደሩ ተቋሞች የሚያስከፍሉት ገንዘብ

በመጀመሪያ ደረጃ የግል ርስት እያሉ ንጉሠ ነገሥቱ ለድርጅቱ ተቋሞች ይሰጧቸው የነበሩት ቦታዎች መጀመሪያውኑ እንዴት የግላቸው ሆኑ ተብሎ ቢጠየቅ ምናልባት ብዙዎቹ የመንግሥት ሆነው ይገኛሉ። የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ በአንድ ባሊያናዊ ተጀምሮ አፄ ምኒልክ ለመንግሥት እንዲሆን ካደረጉት በኋላ ሥራ አቋርጦ ነበር። በ1915 እንደገና ተቋቁሞ በጠላት ወረራ ወቅት ተስፋፍቶ ነበር። ከወረራው በኋላ መንግሥት ሊወስደው ሲገባ የጃንሆይ የግል ንብረት ሆነ።የአንበሳ አውቶብስም ጉዳይ ከዚህ አይለይም። ኮኤል የሚባል የመብራት ኃይል ማመንጫ ሙሉ በሙሉ የባሊያን ዜጋ ሃብት የነበረ ሲሆን በኋላ ከልዑል መኮንን ጋር አክሲዮን እንዲገባ ተደርጎ ነበር። ባሊያኑ ሲባረር መንግሥት በጉዳዩ ስላልገባበት ገቢው ከገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ውጭ እንደሆነ ቆይቶ ነበር። የመብራት ኃይል ማመንጨቱን ሥራ የሚያከናውነው ይኸው ኮኤል የሚባለው ድርጅት ስለነበረ በጦር ኃይሎች የተሠራው ቆቃ የሚያመነጨውም የመብራት ኃይል በዚሁ ኩባንያ ሥር ዋለ። ስለሆነም ኩባንያው የሚያገኘው ገቢ የራሱ የነበረና ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር መግባት የጀመረውም ቆይቶ በደርግ ዘመን መሆኑ ይነገራል።



ብዙውን ጊዜ ከግል ገንዘባቸው ተቸረ የሚባለውን ስንመረምር እንዴት ይኼን ያህል ገንዘብ ሊኖራቸው ቻለ ብሎ እንዲጠየቅ ይጋብዛል። ከደመወዛቸውም ከኾነ ደመወዙ ከልክ በላይ ነበረ ማለት ነው። በፊት በአገረ ገዥነት በነበሩ ጊዜ የተሾሙባቸው ግዛቶች ጥቅም የሚሰጡ ስለነበሩ ገንዘብ እንደሚኖራቸው ቢገመትም ከሌሎቹ አገረ ገዥዎች ይበልጥ እንደ ኾነ እንጂ እንዲህ የናረ ይሆናል ማለቱ ያስቸግራል።

ሌሎች ድርጅቶችም ሆኑ የውጭ ተቋሞች ለመርዳት የሚቀላቸውና የሚመርጡት ቀጥታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለኾነ በትክክል ያለንቅዘት ሥራው ቢሠራ የበለጠ ይረዱ ነበር። የብሔራዊ ሎተሪ ገቢም ኾነ የጠላት ንብረት የኢትዮጵያ መንግሥት ሀብት ስለኾነ ባጀት ተዘጋጅቶ ፓርላማውን አሳምኖ ለኢትዮጵያውያን የሚበጅ ሥራ ለመሥራት ቢጠየቅ ይፈቅድና ይስማማል እንጂ አይቃወምም ነበር።

የሀብት ነገር ከተነሳ ባሊያን ሠርቶት የሄደውንና ከሌሎች ሰዎች የሚወርሱትን ቦታዎችና ቤቶች ወደ ራሳቸውና ወደ ልጆቻቸው ባለቤትነት ይዛወሩ ነበር። ከልጆቻቸው በጣም ከበርቴ የነበሩት ልዕልት ተናኘ ወርቅ ነበሩ። ባሊያን ሠርቷቸው የሄደውን ቤቶች በመውረስ የመከላከያ ሚኒስቴር ሕንፃ፣ የቀድሞው የሳባ መጽሐፍት ቤት የነበረበት መደዳ ቤት አሁን ሼህ አላሙዲን የያዙት ቦታ፣ የኢትዮጵያ ሲኒማና ትሪያኖን ቡና ቤት፣ የራስ ተሰማ ቤትና አካባቢው፣ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ከእናታቸው የወረሱትን ቦታ የቀድሞ አይሮፕላን ማቢያና አካባቢውን ወርሰዋል። ልዑል መኮንን ደግሞ በአፄ ምኒልክ ዘመን የአቢሲኒያ ባንክ የነበረውንና አሁን ጠቅላይ ስታትስቲክስ ጽሕፈት ቤት የሚባለውን በባለቤትነት ይኖሩበት ነበር። ልዑል ኀይለ ሥላሴ ግዮን ሆቴል መኖሪያ ቤታቸው ሲሆን ኢትዮጵያ ሆቴል ጎን ያለው አንበሳ ባር ያለበት ባሊያን የሠራው ሕንፃ ለትምህርት ቤታቸው ወጭ መሸፈኛ ተሰጧቸው ነበር። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ከብዙ በጥቂቱ ለማሳየት ያህል እንጂ ቢዘረዘሩ እጅግ በጣም በርካታ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀብቱን የተወረሰው ቀደም ብሎ ያለአዋጅ ነበር ቢባል ስህተት አይሆንም።

## የሽልማት ድርጅት

የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሽልማት ድርጅት ከተቋቋመ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ በቀለጠፈና ባልተዛባ መስፈርት ሽልማቶችን በዓላማው መሠረት ይሰጥ ነበር። የድርጅቱ አሠራር ምንም የማይወጣለት ሆኖ እያለ ብዙ ሰዎች የውዳሴ ከንቱ ሥራ ነው እያሉ ማናናቃቸው አልቀረም። ለዚህ አባባል የነበረው ምክንያት ሦስት ነው። አንደኛው አገሪቱ ድሃ መሆንዋ እየታወቀ ለስጦታ ገንዘብና የሰው ጉልበት ለምን በሽልማት ይባክናል። ሁለተኛው አስተሳሰብ ልክ የራሳቸውን ሐውልት እንደሚያሠሩ ዲክታተሮች በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ለምን የሽልማት ድርጅቱ በስማቸው ተሰየመ የሚል ነው። ሦስተኛው የድርጅቱ የገንዘብ ምንጭ ልክ እንደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካና ከንጉሠ ነገሥቱ የግል ርስት ላይ የሚገኘው ሰብል ተሸጦ ስለኾነ በገንዘቡ ምንጭ ላይ ብዙ ሰዎች ነቀፌታ ስላላቸው ነው።

ጃንሆይ በ58 ዓመት ለሠሩት ማስታወሻ የሽልማት ድርጅቱ በስማቸው መሆኑ ያንሳቸው እንደ ኾነ ነው እንጂ አይበዛባቸውም ነበር። ግን የሽልማት ድርጅቱ መሰየም የነበረበት ከሕይወት ዘመናቸው በኋላ በተከታዩ ትውልድ ውሳኔ በኾነ ኖሮ ጥሩ ነበር።

## የዘፈቀደ አስተዳደር

ጃንሆይ ምንም እንኳን ሕገ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰጡ ቢሉም ራሳቸው ከሕግ በላይ የሆኑ አስተዳዳሪ ነበሩ። አሠራራቸው ከደንብና ከሥርዓት ውጭ እንደፈለጋቸውና እንዳሰኛቸው ነበር።

ከጣሊያን አገር የ150 ሚሊዮን ዶላር ብድር እንዳይቀበሉና በተደረገላቸው የጉብኝት ጥሪ መሠረት ጣሊያን ኢትዮጵያን ይቅርታ ሳትጠይቅ ለጉብኝት እንዳይሄዱ ተብለው ቢከለከሉም የግል ውሳኔ አድርገው ጥቅምት 27 ቀን 1963 ዓ.ም የጣሊያንን አገር በይፋ ጎበኙ። በዚህም ጉብኝት የቫቲካንን ጳጳስ ሄደው ዓይተዋል። የቫቲካን ጳጳስ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ሲወርር ሲመጣ መድፉን ሳይቀር የባረከ ሲሆን በመንበሩ የተተካው የዘመኑ ጳጳስ እስከ አሁን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ አልጠየቀም።



እንደዚሁ ሁሉ የአገራችን የጀግኖችና የባለውለታዎች የክብር ማዕረጎችን በማቅለል ወግና ልማዱን ሽረዋል። በዘመናዊ የወታደር ደንብ ውስጥ የሹመት ማዕረግ እስከ ሻለቃ ድረስ በሥርዓት ሲሠራበት ከዚያ በላይ ያሉት እንደ ኮሎኔልና ጄኔራል ያሉ በእንግሊዝ ቃላቶች በመተካት እንደ ፊታውራሪና ደጃዝማች ያሉትን ለነጋዴና ለገበሬ እየሰጡ አቀለሏቸው። አልሆን ብሏቸው እንጂ ዱክ የሚባለውን የእንግሊዝ ሹመት ለልጃቸው ለልዑል መኮንን ሰጥቶ ለማስለመድ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። አንዳንድ ሰዎች ዓለማቀፋዊ የማዕረግ ስም ነው ይሉ ከሆነ ለምን ሌፍትናንት የሚለው የመቶ አለቃ ተባለ ለምንስ ኪንግ እያለ ንጉሥ ይባላል እንደማለት ነው። ማዕረጎቹ በመቃለላቸው ምክንያት የጃንሆይ መንግሥት ሲለወጥ ሹመት የተሰጣቸው ሰዎች መቀለጃ መሆን ጀምረው ነበር። ሌሎች ደግሞ የአድር ባይነት ጠባይ የነበራቸው በፊት ለምነው ያገኙትን ማዕረግ አንፈልግም በማለት በይፋ አቶ በሉን ብለው አስታውቀዋል።

በጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አንድ ሰው ለኢትዮጵያ ምን ጠቀመ ሳይሆን ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ነው የሚለው ጥያቄ የበለጠ ሚዛን የሚደፋ ነበር። ስለሆነም በመጀመሪያ አንድ ግለሰብ መታወቅ ሲጀምር እጅ እንዲነሳ ይጠየቃል። ይህንን ሁኔታ በሥርዓት ካልተከታተለ የግለሰቡ ለአገር ጠቃሚ መሆኑና መታወቁ ጭራሽ ያስጠቃዋል እንጂ አይጠቅመውም።

## ውዳሴ ከንቱ

ጠቅላላውን ስንመለከተው ንጉሠ ነገሥቱ ሁለት ዓይነት አስተዳደር ይመሩ እንደነበረ ነው የምንረዳው።

1ኛ መደበኛው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት
2ኛ የቀ.ኃ.ሥ የውዳሴ ከንቱ አስተዳደር

ሰው ደካማ ፍጡር ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ሰው እንደ መሆናቸው ሁሉ ብዙ ደካማ ጎኖች ነበሯቸው። ከነዚሁም አንዱ ውዳሴ ከንቱ ያበዛሉ። እወደድ ባዮችም ይኸንን ድክመት ነገዱበት። እነዚህም የአንድን አገር መሪ ታሪክ የሚያበላሹ ስግብግብና አስተሳሰባቸው ሁሉ የዕለቱን

ጥቅማቸውን ብቻ የሚመለከት ነው። ጠንካራ መሪ ከደካማው የሚለይበት ብርታት አንዱም እበላባዮችን መቋቋም ሲችል ነው።

የጃንሆይ ልዩ ረዳት (ኤዲሲ) የነበሩት ጄኔራል መኮንን ደነቀ እንዴ ንጉሠ ነገሥቱ 'ምስጋናውን ሁሉ ለራሳቸው ያደርጉታል' ብለው ስለተናገሩ ሰው ሁሉ ገሸሽ አደረጋቸው። ያማ ባይሆን ኖሮ ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድ ስለ ኤርትራ ውህደት ለደከሙት ድካም ጃንሆይ ኤርትራ ሲሄዱ ባደረጉት የይፋ ንግግራቸው ላይ ስማቸውን ጠቅሰው ባመስገኑዋቸው ነበር። ራስ አበበ በብዙ ምክንያቶች ወደ አውሮፓ እንዲሄዱ ሲታቀድ ጃንሆይ ያስቀሩዋቸው እንደነበረ ይታወቃል። ጄኔራል መኮንን የተናገሩት ውሸት ሆኖ ሳይሆን ሁሉም ልቡ እያወቀ የንጉሠ ነገሥቱ ተቆርቋሪ መስሎ ለመታየት ሲል ነው።

ለዚህ ምስኪን ሕዝብ የተቻላቸውን ያህል ቋሚና ኑሮውን የሚያሻሽልበት ሁኔታ ትተውለት ማለፍ ሲችሉ የነበረውን ረጅም የሠላም ወቅት በውዳሴ ከንቱ ዝናና ራስ ወዳድነት ላይ በማተኮር አባክነውታል። በመሠረቱ ቀኃሥ አገሩን ይገዙ የነበሩት ለራሳቸው ተድላና ደስታ እንጂ ለሕዝቡ ብለው እንዳልነበር የሚያስረዱ ድርጊቶች አሉ። አንደኛ ትተውለት የሄዱት ጠቃሚ ነገር ካለመኖሩም ሌላ ሥልጣናቸውን በሠላም ለራሳቸው ልጆች እንኳን ማስተላለፍ አልፈቀዱም። እንዲያውም ከሳቸው በፊት ዝነኛ መሪ እንዳልነበርና ወደፊትም እንዳይፈጠር አበላሽተው በማለፋቸው ከዘመናቸው በኋላ ያለው ትውልድ ደምቶበታል። በሕይወት ዘመናቸው 101 ኒሻኖችና ሜዳሊያዎች፣ 20 የክብር ዲግሪ በፍልስፍና፣ በግብርና፣ በሕግና በሥነ ጽሑፍ ተለግሰዋል። እንዲሁም ከእንግሊዝ መንግሥት የፊልድ ማርሻል ማዕረግ አግኝተዋል። ከአገር ውስጥና ከውጭ አገሮች 100 የተለያዩ ሽልማቶች ተበርክቶላቸዋል። 167 አገሮች ሲጎበኙ በዘመናቸው የ63 አገር መሪዎች ኢትዮጵያን ጎብኝተዋል። የአገሪቱን ምጣኔ ኃብት ሲመለከቱት ከላይ የተጠቀሰው ግርግር ያበረከተው ጠቀሜታ ኢምንት ነበር። እንዲያውም ለዚህ ግርግር ወጭ የሆነው ገንዘብ ጠቃሚ ሥራ ላይ ውሎ በሆነ መልካም ነበር ያሰኛል።

ሊያደርጉ የሚፈልጉትን ሁሉ በመንግሥት በኩል በቀለጠፈና በተስተካከለ መልኩ መሥራት ሲቻል በተወሳሰበ አኳኋን ሲሠሩ ብዙ ባለሥልጣኖችን ለንቅዘት አስተዳደር ጋበዙ። አንዱ የድህነት ዋና



ምክንያት የባለሥልጣኖች ንቅዘት እንደሆነ አይካድም። ስለሆነም በዚህ አይነት አሠራር ለሕዝቡ ድህነትንም አውርሰዋል ማለት ነው።

ጃንሆይን እንወዳቸዋለን እናከብራቸዋለን ግን እንተቻቸዋለን። እሳቸውን ያዋረዱ ራሳቸው ወራዳ ስለነበሩ ይሄው አሁን ተዋርደዋል። አንዳንድ የተሠሩም ነገሮች ላይ የሚደነቁባቸውና የሚመስገኑባቸው እንዳሉ ዕሙን ነው። ምንም እንኩዋን ብዙ ዓመት በሠላም የማስተዳደር ዕድልና በዘመናቸው የምዕራባውያን ስልጣኔ ተጋፍቶ የመጣበት ጊዜ ቢሆኑም ያስገቡት ስልጣኔ ሰዎችን በከፊል ሲያረካ ከፊሎችን ደግሞ አላረካም። የረኩት ያላዩትን ስላዩ ተደስተዋል ያልረኩት ግን ከሌሎች ተመሳሳይ አገሮች ሁኔታ ጋር በማስተያየት አገራችን ሊገባ የሚችለው ስልጣኔ አልገባም ነው የሚሉት። ሁለቱም ልክ ናቸው። የሚያሳዝነው ግን የሚያግባባውም ራሱ ስልጣኔ ስለሆነና ይሄኛው ስልጣኔ ደግሞ በለመግባቱ ሀለቱ ወገኖች ሊግባቡ አልቻሉም። የንግግር ነፃነት ኖሮ ሕዝብ ስለራሱ መንግሥት አስተዳደር በይፋና ሳይፈራ መወያየት ቢችል ኖሮ የማይግባባበት ምክንያት በጠፋ ነበር። የንጉሠ ነገሥቱን ስልጣን መጠበቅ ብቻ ተቀዳሚ ጉዳይ ስለነበረ ችግር ውስጥ ተገብቶ ብዙ ጥፋት ተፈጸመ። ከዚህ ሁሉ በኃላ አስተዳደሩ ግሩም ስለነበረ ራሳቸው እያደነቁ ያንኑ አሠራር አድንቁ ብለው የሚታገሉ ተላላ የሆኑ ሰዎች አሁንም አሉ።

ከላይ ያሉትን መዘርዘር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ለወደፊቱ በኃላፊነት ላይ የሚቀመጡ ሁሉ ተቀዳሚ ተግባራቸው ለአገራቸው ሕዝብ ሠላምን፣ ዕድገትን፣ መግባባትን፣ ብልጽግናና ጨዋነትን አውርሰው ማለፍ እንጂ ለጊዜያዊ ተድላና ደስታ በብልጣ ብልጥነት ኃብትንና ጊዜን እንዳያባክኑና ምን ትቼ ልለፍ ብለው ኃላፊነት እንዲሰማቸው ለማስገንዘብ ነው።

## የአንድነት ስሜት

ንጉሠ ነገሥቱ ለዓላማቸው ጎበዝ፣ ብልህ፣ ዘዴኛ፣ የነበሩ መሆናቸው አይካድም። በዛው ልክ ደግሞ ውዳሴ ከንቱ የሚያበዙና በዚህ በረጅም የሥልጣን ዘመናቸው ሊሠሩዋቸው የሚችሉትን ብዙ ሥራዎች ሳይሠሩ ማለፋቸው ይታወቃል። ጃንሆይ ራስ ወዳድ እንጂ የጎሣ ወይም ወገናዊነት አይታይባቸውም ነበር። ስለሆነም አስተዳደራቸው ውስጥ ኢትዮጵያን በአንድነት አስተሳስብ ለማስተዳደር አልተቸገሩም።

በሚመሩት የመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ሥልጣን አሰጣጥ ላይ የግለሰቡን ሁኔታ እንጂ የጎሣው ምንነት ስፍራ አይሰጠውም ነበር። ስለሆነም በዘመናቸው የጎሣ ልዩነት እየመነመነ ሄዶ ኢትዮጵያ አንድነቷ የጎለበተበት ወቅት ሆኖ ነበር። የጃንሆይ አስተዳደር አንዱ ውርስ ኢትዮጵያን መገንባት መፍትሄው አማራነት፣ ትግሬነት፣ ጉራጌነት፣ ወላይታነት፣ ሶማሊነት፣ አፋርነት፣ ወዘተ.. ብሎ ማሰብ ሳይሆን ጎሣው ምንም ይሁን በቅድሚያ ኢትዮጵያዊነቱ ብቻ መታየት ያለበት መሆኑን ነው። እንዲያውም ጃንሆይ ኤርትራውያኖች ምንም እንኳን አገራቸው በውጭ ኃይል ተይዞ ለብቻው የሚተዳደር የነበረ ቢሆንም ኢትዮጵያን ብለው የመጡትን ኤርትራውያኖች በማስተማርና ሥልጣን በመስጠት እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ እኩል መብታቸውን በማክበር በሲቪልም እስከ ሚኒስቴርነት በወታደርም እስከ ጄኔራልነት ስፍራ ይሰጧቸው ነበር።

ያም ሆኖ ግን አንዳንድ ያለፉ የአስተዳደር ስህተቶችን በአማራው ላይ ለመጣል አንዳንድ ሰዎች ይሞክራሉ። ለነገሩ የሚሠራ ሁሉ ይሳሳታል፣ ይወቀሳልም። የማይሠራ ብቻ ነው ሊወቀስ የማይችለው። ስለሆነም አስተዳደሩ በወቅቱ ያለውን ሥልጣኔ፣ አስተሳሰብና ችግር ያገናዘበ ስለሚሆን ከመውቀስ በፊት ሁኔታዎችን በሥርዓት ማስተዋል ያስፈልጋል። ይሁንና የአማራው አንጻራዊ የተሻለ የአስተዳደር ችሎታ ላለፉት 700 መቶ ዓመታት ተሳትፎ ባገኘው ልምድ የተመረኮዘ ስለኾነ አሁን ሌሎች ጎሣዎች አልፈው አልፈው በሚከሰቱ ምክንያቶች የአማራውን የአስተዳደር ችሎታ የመሰከሩበትም ሁኔታ አለ። ሌሎች ጎሣዎችም በአስተዳደሩ መግባታቸው ወቅታዊና መሆንም ያለበት ሲሆን፣ እነሱም አልፈው አልፈው ስህተት ቢሠሩም ማጉላቱ አይበጅም።

አንድ ትልቅ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመገንባት አንድ ጎሣ ብቻ እንዲያስተዳድር መፍቀድ በመሠረቱ ስህተት ነው። ለዚህች አገር እያንዳንዱ ጎሣ እኩል መስዋዕትነት እንዲከፍል ስለሚጠበቅ በሠላሙ ጊዜ እኩል ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል። የራሱን ጎሣ ጥቅም ብቻ የሚጠብቅ ሌላውን ጎሣ አስተባብሮ ማስተዳደር ይቸግረዋል። ጀርመኖች ኃይል እያላቸው አውሮፓን እንኳን አሸንፎ ይዞ ማስተዳደር አልቻሉም። ምክንያቱም አስተሳሰባቸው ከጀርመን ዝርያ የበላይነት ዕምነት ባሻገር ሊሄድ ስላልቻለ ነው። በመሠረቱ በየትም ዓለም ሕዝብ ጥሩና የዋህ ነው። ከመካከሉ ግን በየዋህነቱ ለመጠቀም



የሚሯሯጡ ጥቂቶች ውሳኔውን በማሳት ችግር ውስጥ ሲከቱት በተደጋጋሚ ታሪክ አሳይቷል። በሌላ በኩል ለእኩልነት የሚደረግ ትግል ሁሉ መደገፍ ሲኖርበት በእኩልነት ስም ለበላይነት መታገል ግን በፊት በበላይነት ለተሠሩት ስህተቶች ትክክለኝነት ማረጋገጫ ይሆናል።

እውነት ለመናገር ከሆነ አማራውና ትግሬው ወደ ኋላ የቀሩት በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ነው። ኤርትራ ውስጥ በየመንደሩ ትምሕርት ቤት ሲከፍቱ፣ በሌላው አካባቢ ፋብሪካዎች ሲያቋቁሙ፣ በትግራይና በአማራው አገር ላይ ጦር ሲያዘምቱ በአይሮፕላን ሲያስደበድቡ ኖሩ እንጂ በተለየ የሠሩለት ነገር አለ ለማለት አያስደፍርም። አንድ ሕዝብ የሚገነባው በተለያዩ ጎሣዎች ሲሆን ሁሉንም በእኩልነት ማስተዳደር ሲገባ በተለያዩ መክንያቶች ማበላለጥ ግን ቀጣዩን ተውልድ የተዛባ አመለካከት ውስጥ ይከተዋል። በመሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተደበላልቆ አንድ ኢትዮጵያዊ ብሔር ይሆናል ተብሎ ይገመታል እንጂ በየጎሣው እየተከፋፈለ ለረጅም ዘመን አይኖርም። ምክንያቱም የሕዝቡ መደባለቅ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ ስለኾነ ነው። በየሠርግ ወረቀቱ ላይ ያውም በስም መለየት የተቻለውን ብቻ በመመልከት በጋብቻ የመደባለቁ ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን ማጤን ይቻላል።



# ምዕራፍ ፴፰

## ሁለት ሉሉዎች በቤተ መንግሥት

ጄኔራል ሉሉ እንግሪዳ የሚባሉ የአፋር ተወላጅ ከወፍራሙ ግራዝማች ቡመር ዲንጎ ቀጥሎ የጃንሆይ ሾፌር የነበሩት በቤተ መንግሥት የታወቁና የተከበሩ ሰው ነበሩ። ጃንሆይን በሾፌርነት ሲያገለግሉ ኖረው በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

ጃንሆይ በእስር ሲወሰዱ ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ቆማ የነበረችው የጄኔራል ሉሉ የግል ቮልክስዋገን ቢትልስ መኪና ጃንሆይ እንዲሳፈሩባት ተደርጎ ከሄዱባት በኋላ መኪናዋም ታስራ ለረጅም ዓመት ቆይታ ለቤተሰቡ ተመልሳ በአሁኑ ወቅት ይገለገሉባታል።

ሌላዋ ሉሉ የታወቀችው የጃንሆይ ድንክ ውሻ ነበረች። ይህች ድንክ ውሻ አቶ ጃማነህ አላዛለው ተማሪ በነበሩበት ጊዜ በ1942 ዓ.ም ለጃንሆይ ያበረከቷት ነች። በተበረከተችበት ጊዜ ጃንሆይ "ስሟ ማነው" ብለው ቢጠይቁ ግለሰቡ ያልተዘጋጁበት ጉዳይ ስለነበረ አፋቸው ላይ እንደመጣ "ሉሉ ነው" ብለው መለሱላቸው። ከዚህ ወቅት አንስቶ የውሻዋ ስም ሉሉ ሆኖ ቀረ።

ይህች ድንክ ውሻ የተለየችና አቶ ጀማነህ ከየት አምጥተው እንዳሳደግዋት በእርግጥ የሚያውቅ ሰው አልተገኘም። ይሁንና የነቃችና ብልህ ውሻ ስለነበረች ለብዙ ጊዜ ሉሉን በውጭ አገር ጉብኝታቸው ጭምር ሳያስቀድሙ ንጉሠ ነገሥቱ አይሄዱም ነበር። ጃንሆይ ሉሉን ሳያስከትሉ የሚሄዱበት ቦታ ወደ ቤተ ክርስትያን ብቻ ነበር። ጃንሆይ አውስትራሊያን ለመጎብኘት ሲሄዱ የአገሩ ሕግ እንስሳ እንዲገባ ስለማይፈቅድ ሉሉ ልትገባ ባለመቻልዋ አንድ የቤተ መንግሥት



ባለሥልጣን ሉሉን ይዞ ወደ ሚቀጥለው የጎበኙት አገር ደቡብ ኮርያ ሄዶ ጃንሆይ እዚያ ሲደርሱ አስረክቧል።

ጃንሆይ ከአይሮፕላን ከመውረዳቸው በፊት ሉሉ ትወርድና የራሷን ጉብኝት ታደርጋለች። ውድድር ለመመልከት ወደ ስታዲየም ሲመጡ ቀጥ ብላ ኳሱ ሜዳ መካከሉ ድረስ ትሄድና ተመልሳ እስራቸው ትተኛለች። በተለይ በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል በ1954 ዓ.ም በተደረገው የሦስተኛ የአፍሪካ ዋንጫ የመጨረሻ ግጥሚያ ዕለት ሜዳው ውስጥ ገብታ እንዲያውም ጎል ማግቢያው ድረስ ሄዳ መመለሷን እንደ ትልቅ ነገር የሚያወሱ ሰዎች አሉ። ይኽን ሁሉ የሚመለከት ሰው ይህች ውሻ ነገር ያላት ናት እያለ ይናገራል።

ሉሉን የሚወዷት ሰዎች የመኖራቸውን ያህል የሚጠሏትም ብዙዎች ነበሩ። በተለይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጃንሆይ ለምርቃት በዓል ሲመጡ የእሷ አብሮ መምጣት አይጥማቸውም ነበር። እሷም መካከላቸው እየገባች ታነፈንፍ ስለነበረ አንድ ዓመት ላይ አንድ ምሩቅ ሰው ሳያየው ረገጣትና ሙኸች። በዚህን ጊዜ አጃቢዎች ረጋጩን ተማሪ ለመለየት ብዙ ቢሞክሩም ሌሎቹ ተማሪዎች ስለሸፈኑት ተማሪው ሳይለይ ነገሩ እንዲሁ በቅሬታ ታለፈ።

"ባለቤቱን ካልናቁ ውሻዋን አይነኩም" እንደሚባለው ጃንሆይን ካልናቁ ወይም ካልጠሉ ውሻዋን አይነኩም በሚል ውሻዋን ሁሉ ሰው ያከብር ነበር። አንድ ጊዜ ኮሎኔል ተክሉ ገብሩ ሻምብል በነበሩበት ወቅት ተግባረ ዕድ ትምሕርት ቤት የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን ትምሕርት ሲማሩ ጃንሆይ ትምሕርት ቤቱን ለመጎብኘት ሲመጡ መኮንኑ እግር ስር ሉሉ መጥታ ስላስቸገረቻቸውና ጃንሆይም በቅርብ ስለነበሩ ውሻዋን 'ወይጅ!' ማለት ስለፈሩ 'ወይዱ!' ስላሉ ጓደኞቻቸው ወይዱ! የሚል የቅጽል ስም ሰጥተዋቸው ነበር።

ሉሉ የወር ደሞዝ ተቆርጦላት በወር የአንድ ሻምበል ደመወዝ ብር 175.00 ታገኝ እንደነበረ የታወቀው ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ለግዛር በሚገኘው የጦር ካምፕ እስር ላይ በነበሩበት ወቅት ለአንድ ሻንበል 'እኔ እዚህ ችግር ውስጥ የገባሁት ያንተን ደሞዝ ከአንድ ውሻ ደሞዝ እንዲሻል ለማድረግ ብዬ ነበር' ብለው በመናገራቸው ነው።

ሞት አይቀርምና ሉሉ ስትሞት ቤተ መንግሥት ውስጥ ተቀብራ መቃብሯም በዕብነ በረድ ስለተሠራ ጃንሆይ ከተወቀሱበት ነገር አንዱ ሆኗል። በአገራችን ለእንስሳት ክብር ሐውልት መሥራት ያልተለመደ ሆኖ ነው እንጅ አገልግሎት ለሰጠ እንስሳ ማስታወሻ ማድረጉ አይከፋም ነበር። በኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥትም በትግል ዘመን ታሪክ ለሠራች አንድ የሃምሳ አለቃ ደሳለኝ ለምትባል አህያ ሐውልት ተሠርቷል። ስለሆነም ሉሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ሐውልት ከተሠራላቸው እንስሶች በታሪክ የመጀመሪያዋ መሆንዋ ነው።



# ምዕራፍ ፴፱

# ንጉሠ ነገሥቱ በአጠቃላይ ዕይታ

ንጉሠ ነገሥቱ በተፈጥሮ ብልህ፣ የውጭ አገር ትምሕርት የቀሰሙና ተራማጅ እንደ ነበሩ ይወሳላቸዋል። ሆኖም ከ 58 ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው በኋላ የአመራራቸው ውጤት እንደሚከተለው ሆኖ ተገኝቷል።

## መልካም ሥራዎቻቸው

1 ኢትዮጵያን የዓለምና የአፍሪካ መንግሥታት ማኅበሮች አባል አደረጉ
2 ዘመናዊ ትምሕርትን አስፋፉ
3 ቋሚና ዘመናዊ የመንግሥት ወታደር ገነቡ
4 ምክር ቤት አቋቋሙ፣ ሕግና ደንብ እንዲወጣና ሥራ ላይ እንዲውል አደረጉ
5 ማዕከላዊ መንግሥትን አጠናከሩ
6 ኤርትራን ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ጋር አዋሃዱ
7 አነስተኛ ተቋሞችን በሁሉም መስክ አቋቋሙ
8 ከግብጽ ጋር የነበረውን የሃይማኖት ችግር መፍትሄ ሰጡ።

## የተወቀሱባቸው ሥራዎች

1 በዘመናቸው ኢትዮጵያ በጦርነት ተሸንፋ ጠላት አገርን ወረረ
2 አመርቂ የኤኮኖሚ ዕድገት ሳያመጡና የመሬት ይዞታን ችግር በወቅቱ መፍትሄ ሳይሰጡ ቀሩ
3 ፍቅረ ንዋይ፣ የግል ድሎትና ውዳሴ ከንቱ አበዙ
4 የሚተኳቸውን ሳያዘጋጁ አለፉ።

በመሠረቱ ኢትዮጵያን ከጥንታዊ ሥርዓት አሸጋግረው ዘመናዊነትን ያስፋፉ ስለሆኑ በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሥፍራ ይኖራቸዋል።

በሌላ መልኩ የኢትዮጵያን ንጉሣዊ ሥርዓትም እንዲገረሰስ ያመቻቹ ራሳቸው ናቸው ማለት ይቻላል። ብዙ ዘመን አገሪቱን በማስተዳደራቸው ምክንያት በሕዝብ ተቀባይነትና ክበሬታ ስለነበራቸው ከጣሊያን ወረራ በፊት የጀመሩትን አሠራር ከወረራውም በኋላ ቀጥለው ሥልጣናቸውን በወቅቱ አስረክበው ቢሆን ኖሮ አገሪቱም እሳቸውም ተጎጂ ባልሆኑ ነበር። በተለይ ከ1953 ዓ.ም የታህሣሥ ግርግር በኋላ በእርጅናና በግትርነት ለአሥራ ሦስት ዓመት የሕዝቡን ፍላጎት ችላ በማለትና በማን አለብኝነት፣ በግል ድሎትና በውዳሴ ከንቱ ጊዜ ማጥፋታቸው ለውድቀታቸው ዋና ምክንያት ኾነ። የተማረው ወጣት ሥራ አጥ ሆኖ፣ ሕዝቡ በድህነት እየተጉላላ፣ ደጋግሞ በሚመታው ድርቅ ባስከተለው የረሃብ አለንጋ እየተገረፈ፣ እሳቸው ግን በእርጅና ዘመናቸው እንኳን የሥልጣን ጥማቸውን ብቻ በማርካት ላይ እንዳሉ በመጨረሻ ላይ የመጣውን የሕዝብ እንቅስቃሴ ለማቆም ሳይችሉ ቀሩ።

ስለዚህ ያለምንም ማመንታት ለውድቀታቸው ምክንያት የሆነው የራሳቸው የተፈጥሮ ባህሪያቸው ነው ለማለት ይቻላል። አንደኛ ሞትን የማይቀበሉ ስለነበሩ የ80 ዓመት ልደት በዓላቸውን አክብረው ሥልጣን ላይ ንቁግ ስለነበሩ አልጋ ወራሻቸውን እንኳን ንጉሥ ብለው ለማለማመድ ቀርቶ ካቢኔያቸው ምን እንደሚሠራ እንኳን እንዲያውቁ አላደረጉም። ሁለተኛ በእሳቸው ዘመነ መንግሥት እንዲፈጸሙ ያልፈለጓቸው ሥር ነቀል ለውጦች የሆኑት የመሬት ይዞታን የሚያሻሽልና መሠረተ ልማት የሚያመጡ ታላላቅ ሥራዎች ማስፈጸም አልፈለጉም። ሦስተኛ ውዳሴ ከንቱ ስለሚያበዙ የሠላም አባት ተብለው የኖቤል ሽልማትን ለማግኘትና በዓለም ላይ ተደናቂ ለመሆን ሲሉ ለአገራቸው ታላላቅ ሥራ የሚሠሩበትን ጊዜና የሰው ኃይል አባከኑ። የከበቧቸው ሰዎች የተማሩትም ያልተማሩትም በንጉሠ ነገሥቱ የሚያመልኩና አገር ወዳድ ሆነው መጭውን መገመት የተሳናቸው ስለነበሩ ራሳቸውንም አገራቸውንም ጎዱ።

ተፈሪ ክፉ ነው ልቡም አይገኝ
ለሰው ይመስለዋል ይናገራል ቀኝ
ኋላ እንዲህ ሊዋረድ ፍጻሙን ሊያገኝ
ሼህ ሁሴን ጅብሪል





# ምዕራፍ ፵

## ተፈጥሮና የሰው ልጅ

ሰው በቀላሉ አይረዳውም እንጂ ተፈጥሮ ሰውን ያነጋግራል። ጥቂት ሰዎች አንዳንዴ እየገነገኑ የተፈጥሮን ቋንቋ ሊረዱ ይሞክራሉ።

ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሰው ከቤቱ ሲወጣ ባዶ እንስራ ከገጠመው ፍርድ ቤትም የሚሄድ ከኾነ እረታለሁ መንገድም የሚሄድ ከኾነ ለሚመጣው ሁሉ ይጠነቀቅና ምናልባትም አንድ አነስተኛ ችግር በመካከሉ ከገጠመው በዚሁ ይለፍልኝ ብሎ ለፈጣሪው ይማለዳል። ፈረንጅም ጥቁር ድመት ካቋረጠው ወይ ወደ ቤቱ ይመለሳል ወይም ጥንቃቄ ያደርጋል። በእንጻሩም በስኮትላንድ ለዘመን መለወጫ (New Year) አንድ ሰው ቤት የዓይኑ ብሌንና ፀጉሩ ጥቁር የሆነ እንግዳ በመጀመሪያ በር አንኳክቶ ቢመጣ ሀብታምና ጤነኛ እንደምንሆን ምልክት ነው ብለው ስለሚያምኑ ደስታቸው ወሰን አይኖረውም።

እግዚአብሔር ምድር ቢወርድና ሰውን ቢያነጋግር የእያንዳንዱን አገር ሕዝብ በየቋንቋው ያናግራል እንጂ በእንግሊዝኛ፣ በሃረማይክ፣ በኤስፔራንቶ፣ በአረብኛ፣ በግዕዝ ወይም በቻይንኛ ሊያነጋግር አይችልም። ተፈጥሮም ሲያነጋግረን በየራሳችን ባህልና ቋንቋ ወይም በሚገባን ዘዴ ነው። የሚገርመው ደግሞ እንዲገባን ካልፈለግን ሌላ እንዲገባን የሚያስችል መላ ይፈጥራል። እርግጥ ይህን ቋንቋ አንዳንዶች ሱፐርስቲሽን ነው ብለው አይቀበሉትም። አንዳንዶች ደግሞ በዚህ ቋንቋ ይመሰጡና የሚገጥማቸውን ሁሉ ትርጉም እየሰጡ ሲጨነቁ ይታያሉ። ሳይበዛ ግን በስፋት ሰው የሚመለከተውንና ትርጉም የሚሰጠውን ማጤን ክፋት የለውም።

ጣሊያን ሊገባ ሲል ብዙ ሰዎች ምልክቶችን ዓይተው ነገሩ በቅድሚያ የገባቸው ነበሩ። ዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ አካባቢ ያኔ ጋን ተራ ነበር

የሚባለው ልጆች ወገን ለይተው ነፍስ እስኪጠፋ ድረስ በኃይል ተደባደቡ። በአካባቢ የነበሩ ሽማግሌዎች የጦርነት ምልክት ነው ብለው ተረጎሙት። ደርግ ሥልጣን እንደያዘ የቻይና ቡድንና የቦንባርድ ቡድን ተባብለው እዚሁ አረዳ ላይ ብዙ ልጆች ተጎድተው የሞተው ሞቶ በፖሊስ ጣልቃ ገብነት ተበተኑ። ይህ የሽብር ጦርነት አመጣጥን አመላካች ነበር። በነገራችን ላይ ጦርነት ዓይነቱ ብዙ ነው። የነገር ጦርነት፣ የዲፕሎማሲ ጦርነት፣ የሚዲያ ጦርነት፣ የስም መጥፋት ጦርነት፣ የሽብር ጦርነት፣ የሽምቅ ውጊያ ጦርነት፣ የመሣሪያ ጦርነት ወዘተ.. ናቸው።

ለማይጨው ፍልሚያ የቀደመው ወታደር ሁሉ ማይጨው አካባቢ ሰፍሮና ሊላውም በጉዞ ላይ እንዳለ አንድ ቀን ፀሐይዋ በጣም ቀልታ ታየች። ይሄኔ ሽማግሌዎች “አይ ይህ ጦርነት እኛን አይቀናንም ድል አናደርግም” ብለው ተናገሩ። እንደሚባለው ራስ ካሣ ጦርነቱ ላይ ድል እንደማይኖረን ዐዋቂዎች የነገሯቸውን በማመናቸው ወደ ዘመቻ በሚሄዱበት ጊዜ አብሯቸው የዘመተው ጦር ይጓዝ የነበረው በዝግታ ነበር። በየሃያ አምስት ኪሎ ሜትር እንረፍ እያሉ ማይጨው ለመድረስ ብዙ ቀን ፈጅተዋል። ዕውነትም ጦሩ ተበትኖ ንጉሠ ነገሥቱም ወደ መናገሻ ከተማቸው ተመለሱ።

ጣሊያን አዲስ አበባ ገብቶ ከቆየ በኋላ አንድ ቀን አዲስ አበባ ላይ ፀሐይዋን ደስ የማይልና የመኪና ጭስ የመሰለ ነገር ከቧት አዩና “ምን ሊመጣብን ነው?” እያሉ ሲወያዩ ጥቂት ቀን አለፈና ግራዚያኒ ንግግር አደርጋለሁ ብሎ የከተማውን ነዋሪ በሰበሰበበት ወቅት በድንገት እነ አብርሐ ደቦጭ ቦንብ ወርውረው አቆሰሉት። በዚህን ጊዜ የጣሊያን ወታደር ብቀላ ለማድረግ ባገኘው መሣሪያ በአካፋና በዶማ ሳይቀር በየመንገዱ ያጋጠመውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሦስት ቀን ሙሉ ጨፈጨፈውና ወደ 30,000 ሰው አለቀ። በደርግ ዘመነ መንግሥት ልክ የዚያን ዓይነት ጭስ ፀሐይዋን ከቧት በመታየቱ የአዲስ አበባ ሰው ወሬ አበዛና የደርግን ባለሥልጣኖች አሳሰባቸው። በዚህን ጊዜ የታየውን መዋሸት ስለማይቻል ሳይንሳዊ ገለጻ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ሲያደርጉ ሰነበቱ። ግን ጥቂት ቀን ቆይቶ የነጭና የቀይ ሽብር በአዲስ አበባ ተከፈተና ብዙ ወጣት አለቀ።

ጃንሆይ ከስደት ሲመለሱ መጀመሪያ የረገጡት የኢትዮጵያ ምድር ኦሜድላ ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ሲያውለበልቡ ቀስተ ዳመና ሰማዩ ላይ



ታየና ሰው ሁሉ ደስ አለው። ጃንሆይም ይችን ደስታ በሆዳቸው ይዘው ኖረው አቡነ ባስልዮስ ሞተው በቀብር ሰዓት ደብረ ሊባኖስ ላይ ከንግግራቸው መሃከል አነሷት። የአሜሪካው ፕሬዚደንት ደብልዩ ቡሽ ሮማንያን በኅዳር ወር 1995 ዓ.ም በጎበኙበት ወቅት ንግግር ሲያደርጉ ቀስተ ዳመና ሰላዩ “ጥሩ ምልክት ነው ብለው” ራሳቸው ተናገሩ። በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም የኢሕአዴግ ጦር አዲስ አበባን ከቧት ፍጅት ይሆናል ተብሎ በአንዳንድ ሰዎች ሲገመት በሌሎች ደግሞ “ያው ኢትዮጵያውያን ናቸው ይግቡ ምን ያደርጉናል ብለህ ነው” እያለ ሲል በመካከሉ ሰዎች ተጨነቁ። ታዲያ ፀሐይዋን ሰንደቅ ዓላማ የመሰለ ነገር ከቧት በመታየቱ ሰው አማን ነው ብሎ ከሃሳብ ተገላገለ።

በተለምዶ ዛፍ የሚነቅል፣ ጣሪያ የሚገፍ፣ ኃይለኛ ንፋስ ከነፈሰ መንግሥት ይገለበጣል የሚል ትርጉም ይሰጠዋል። ታዲያ ኮሎኔል መንግሥቱ ሊሄዱ ሲሉ በጣም ነፈሰና ሕዝቡ ተጨንቆ እያለ በድንገት ርዕሰ ብሔሩ እንደሸሹ ተገለጸና የንፋሱ መልዕክት ምን እንደነበረ ሕዝቡ ተረዳ።

ብዙውን ጊዜ አገርን በማስተዳደር ላይ ያሉ አካላት ወደፊት ምን ሊሆን ይችላል የሚለውን ለማወቅ በተቻለ ጥረት ያደርጋሉ። ዓለምን ለመግዛት የጣመኘው ሂትለር እንኳን አንድ ይህንን የሚከታተል ቡድን ነበረው ይባላል። በአገራችን ንጉሥ ወደ ጦርነት ሲሄድ ታቦት ይዞ እንደሚሄድ እናውቃለን። አፄ ምኒልክ ዓድዋ ሲዘምቱ የአራዳውን ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት ይዘው እንደሄዱና ጣሊያኖች ከተሸነፉ በኋላ አሥመራ ላይ ስለጦርነቱ ሲያወሩ አንድ ሰው በነጭ ፈረስ ሆኖ ወጋን እንዳሉ ይወሳል። ጣሊያኖችም ለምይጨው ጦርነት ሲመጡ ጥቁር አሳማ ከታንካቸው ላይ አድርገው የመጡት “ፉርቱና” ብለው ነው።

ታዲያ መንግሥትም ለአንዳንድ ነገር መግለጫ ለሕዝቡ ባይሰጥም ከተፈጥሮ ቋንቋ አንዳንድ ነገሮችንም መረዳት ይቻላል። ስለዚህ የወደፊቱን እናውቃለን እያሉ የሚተነብዩ ሰዎች በየወቅቱ እየተነሱ መናገር ሲጀምሩ መጥፎ ነገር የደረሰባቸው ትንቢቱ ስለተነገረ የደረሰባቸው እየመሰላቸው ተናጋሪዎቹን ሟርተኛ እያሉ ስለሚጠሏቸው በፍርሃት የተነሳ የሚናገሩት ትንቢት ምስጢራዊና ስውር ኾኖ ይቀራል። ከ 500 ዓመት በፊት በፈረንሳይ አገር ኖስትረዳሞስ የሚባል ሰው የተናገረው አሁን ድረስ እየደረሰ መሆኑን ፀሐፊዎች ይጠቅሳሉ። እሱ የተናገረው በስውር ስለሆነና ከቀኑም ብዛት ቃላቶቹ ትርጉማቸው በቀን

ብዛት እየለወጠ መተርጎሙ እያዳገተ ሄዶ ብዙ ሰዎች አልገባ እያለቸው ነው። በአገራችንም በአፄ ዮሐንስና በአፄ ምኒልክ ዘመን ይኖሩ የነበሩትና በግጥም የተነበዩት በተለይ በተፈሪ ዘመነ መንግሥት የሚሆነው ቁልጭ ብሎ እንደታያቸው ያሳያል። ሼህ ሁሴን ጅብሪል በ1908 ዓ.ም. ከመሞታቸው በፊት የተናገሩት አብዛኛው ሲደርስ ወደፊት ደግሞ ይፈጸማል ተብሎ የሚጠበቅም እነሆ ከዚህ በታች ይታያል።

በመካ አንድ ንጉሥ ባረብ ሦስት ቲቀሩ
ሐበሻና ሶማል ታይገጥሙም አይቀሩ

ሼህ ሁሴን ይኸን ካሉ ወደፊት ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ትዋሃዳለች ማለታቸው ይሆን? ዘመኑስ ደርሶ የለም? ምክንያቱም አሁን ያሉት የአረብ ንጉሦች ሦስት ብቻ ሲሆኑ እነሱም የሞሮኮ፣ የዮርዳኖስና የሳውዲ አረብያ ናቸው። ይኸን ጉዳይ በተመለከተ ጋዜጦች በቅርቡ ማውሳት ጀምረዋል። ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ ሃበሻ ነን ብለው የሚያምኑት ኤርትራውያኖችን አስገንጥሎ ስለሶማሌ መዋሃድ ማውራት እምብዛም አልታየውም። ሆኖም ግን ቀኑ ደርሶ ትንቢቱ ዕውነተኛ ከኾነ በቅርብ ይታያል ማለት ነው።

በየትኛውም ዓለም የመንግሥትን ኃላፊነት ይዘው የሚኖሩ ሰዎች ጭንቅ ስላለባቸው የወደፊቱን እናውቃለን የሚሉ ሰዎችን ያዳምጣሉ። አጭበርባሪውም በዛው ልክ ስለኾነና ግራ ስለሚያጋባ ይኸንን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች ይመድባሉ። ጣሊያን ሊመጣ አካባቢ የውጭ አገር ሰላዮች በገንዘብ ሰዎችን እየገዙ አጉል ትንቢት እንዲበትኑ አድርገዋቸው "ነጭ ይመጣል እያሉ" ይናገሩ ነበር። ሂትለር ዓለምን ለመግዛት ሕልም ስለነበረውና የሙሴን ጽላት የያዘ ጦር ሁል ጊዜ አሸናፊ ነው የሚለውን ነገር ስለሰማ እሱን ለማስፈለግ ግብጽ አገር አንድ ቡድን ልኮ እንደነበረ ይነገራል። ይህንን መሠረት በማድረግ ነው የሆሊውድ ሰዎች "ዘ ሎስት አርክ" የሚለውን ፊልም የሠሩት።

በአገራችን በቤተ መንግሥት ውስጥ ሊቀ መባኔ የሚባል ሹመት ተሰጥቷቸው ይህንን ጉዳይ የሚከታተሉ ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ትንቢት የሚናገሩትን ሁሉ እያዳመጡ ነገሮችን እያበጠሩ ለንጉሦች ያቀርቡ ነበር። ጃንሆይ ከሥልጣን ሊወርዱ አካባቢ ብዙ ሰዎች መልዕክትም የላኩና ንጉሡም ዘንድ አድርሱን ብለው መልዕክታቸው



ሳይደርስ የቀሩ አሉ። እነዚህም ሰዎች ባሕታውያን፣ ሼሆች፣ አንዳንድ በዕድሜ የገፉ ሰዎች ናቸው።

እንደሊላው የመንግሥት ባለሥልጣን ሁሉ ለጃንሆይም ባህታውያኖች የሚልኩባቸው መልዕክት እንደነበረ ይነገራል። ከመናንያን ቀደም ብሎ በአዲስ አበባ የታወቁ አበ ጉኒና የሚባሉ መነኩሴ ግቢ ገብርኤል በርካታ ሰዎች የሚያውቋቸውና ትንቢት የሚናገሩ እንደ ነበሩ ይታወቃል። ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት በኋላ በደርግ ቤተ መንግሥትም የዚህን ጉዳይ የሚመሩና የሚከታተሉ ሰው እንደነበሩ ይነገራል። መጨረሻ ገደማ በደርግ መንግሥት ላይ እናውቃለን የሚሉ ሁሉ ብዙ የማይወደድ ነገር ማውራት ሲጀምሩ የማጥፋት ዘመቻ ተደርጎ ብዙዎች ተገድለዋል። ከነዚህም መካከል ቀኛዝማች ታየ (የአሩሲዋ እመቤት ልጅ) ከናዝሬት መኖሪያ ቤታቸው ተይዘው ታስረው ደብዛቸው ጠፍቷል። ደርግ የከፋው ኤቤዴ ጎዳ በጣም ታዋቂ የነበሩትን ከቦንጋ ወደ ጅማ አስመጥቶ ረሸናቸው ይባላል። ወልዮዎችንም ከወሎ፣ ሌሎችንም ከየቦታው ሰብስቦ ፈጅቷቸዋል።

አንዳንድ ሁኔታ ላይ ሕዝቡ የተደጋገመ ትንበያ ሲያደርግ ይሰማል። ለምሳሌ "አልጋ ወራሽ አይነግሡም" እያለ ማንም ሰው እንደዘበት ይናገር ነበር። ዕውነትም ሳይነግሡ ቀሩ። ወደፊት የሚሆነውን ደግሞ ሰዎች ሲናገሩ "ጥሩ ጊዜ ይመጣል" ይላሉ። አልፎ ተርፎም "አሁን ዲቪ. እየተባለ ወደ አሜሪካ እንደሚኬደው ወደፊት ዲቪ. ወደ ኢትዮጵያ ይሆናል" የሚሉም አልጠፉም። "አንድ ሸበቶ ባለከዘራ ኢትዮጵያን በሥርዓት ያስተዳድራታል፤ ከእሱ ዘመን ጀምሮ ኢትዮጵያዊ መሆን የማይገኝ ጸጋ ይሆናል" እያለ በሰፊው ሰው ይናገራል። ምን ታይቶት ይሆን ብሎ ከመጠበቅ ሌላ ሰው በምን መሠረት እንዲህ እንደሚል ለማወቅ ይቸግራል። ምናልባት ከበቁ መነኮሳትና ወልዮች እየሰማ ይሆን?

መጽሐፍ ቅዱስ ስለወደፊቱ በሰፊው እንደሚናገር የታወቀ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጣ ፍካሬ ኢየሱስ የሚባል የትንቢት መጽሐፍም አለ። በተጨማሪም የሰው ልጅ ስለወደፊቱ ለማወቅ የውስጥ እጅ ያያል፣ ከብት አርዶ ሞራውን ያነባል፣ ቡና ጠጥቶ ስኒውን ያጠነፍፍና ይመለከታል፣ ኮከብ ይቆጥራል፣ የበቁ ሰዎችን፣ መጽሐፍ ገላጮችንና አዋቂዎችን ይጠይቃል። ይህ ሁሉ ጥረት የነበረና የሚኖርም ነው።



# ምዕራፍ ፵፩

# ሪፑብሊክና ሞናርኪ

## የሥልጣን ኮርቻ

ዴሞክራሲ የሚባለውን ቃል ዘመናዊ ፖለቲከኞች እንደሚጠቀሙበት ሁሉ ቀደም ብሎ የነበሩት ነገሥታት ሃይማኖትንና የዘር ግንድን ለሥልጣን ኮርቻነት ይጠቀሙበት ነበር። ይህ የቋንቋና የዘዴ ልዩነት እንጂ ዓላማውና ግቡ አንድ ነው። ሕዝብ ቀድሞም ቢሆን አሁንም የሚፈልገው ከወገኑ አንድ ሰው መርጦ እንዲያስተዳድረውና ሥራውንም መሥራት ባቃተው ጊዜ ወይም በሞት ሲለይ በሌላ ለመተካት ነው። ሥልጣኑን የጨበጠው ሰው ግን ከያዘው ስፍራ ላለመነቃነቅ እንዲያውም ሲሞት ልጁን ለመተካትና የዘር ዘሩ በሥልጣን እርካብ ላይ እንደተፈናጠጠ እንዲቆይ በሚሸርበውና በሚሠራው ተንኮል ሕዝቡ ለመሪዎቹ መገልገያ መሣሪያ እየኾነ እንዲኖር ይገደዳል። አልፎ ተርፎም አንዳንድ ሸረኛ እበላባይ ምሁሮች ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች በምን ዘዴ ዘመናቸውን ማራዘም እንደሚችሉ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ብዙ መላ ያሳዩዋቸዋል።

በዚህ የታወቀው ጣሊያናዊው የቤተክህነት ሰው ማኪያቬሊ የሚባለው ፈላስፋ ነው። እሱም እሾማለሁ ብሎ በዘመኑ ለነበረው የጣሊያን ንጉሥ መሥፍኑ "The Prince" የሚል የሥልጣን ዕድሜውን ሊያራዝም የሚችልበትን የሚጠቁም መጽሐፍ ጽፎ ይሰጠዋል። መጽሐፉ ከፋፍለህ ግዛን የመሳሰሉ እርኩስ ሃሳቦችን የሚያስተምር ነበር። ንጉሡ መጽሐፉን አስቀርቶ የተመኘውን ሹመት ግን ሳይሰጠው ቀረ። ስሑል ሚካኤል 'ንጉሥ በስለት አይገደልም' ስለሚባል እንዴት እንደሚያደርግ ሲጨነቅ አንድ እበላባይ ጠጋ ብሎ ንጉሥን በሻሽ አንቆ መግደል የሚቻል መሆኑን ስለነገረው ይህንኑ ፈጽሟል።



እንግሊዞች በማኪያቬሊ ፍልስፍና የዓለምን ሕዝብ በያንዳንዱ አገር ላይ ጠንቅ እየጣሉ ሄደው ይኸው የደም ጎርፍ ብዙ ቦታ ይፈሳል። ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ እንደ ፓኪስታንና ባንግላዳሽ ያሉትን ከሕንድ ገንጥለው መንግሥት በማድረጋቸው አዲሶቹ መንግሥቶቸ አሁንም እንደተፋጠጡ ይኖራሉ። ሁለት የማይጣጣሙ ሕዝቦች የሚኖሩባትን ፓልስታይን የምትባለውን አገር ለአንዱ ብቻ ሰጥተው ሄደው ዘለዓለም ደም እየፈሰሰ ነው። ጆርዳን የሚባል መንግሥት ያለመኖሩ እየታወቀ እንግሊዞች የፍልስጥኤም ሕዝብ የሚኖርበትን መሬት ቆርጠው ከሳዑዲ ዓረቢያ ነገሥታት አምጥተው በፍልስጥኤም ሕዝቦች ላይ አዲስ መንግሥት ሾመው ሄዱ። ፍልስጥኤሞች እ.ኤ.አ. በ1969 ዓ.ም ጆርዳን ውስጥ የመንግሥት ግልበጣ ሞክረው ስላልተሳካ 185,000 ፍልስጥኤማውያን በሰይፍ ታርደዋል።

በኢትዮጵያ እንኳን አንዱ ጎሣ በሌላው ጎሣ ላይ ዕምነት እንዳይኖረው አቃቅረው የሄዱት እንግሊዞች ናቸው። ሶማሊዎች በመሠረቱ የኢትዮጵያ አንድ ጎሣ መሆናቸው እየታወቀ አንድ ትልቅ ኤምፓየር እንዲመሠርቱ ታላቋ ሶማሊያ ብለው ባንዲራቸው ላይ አምስት ኮከብ እንዲያደርጉ [illegible]ከሩዋቸው እንግሊዞች ናቸው። ኤርትራን ከመጀመሪያው ጀምሮ እስከመጨረሻው ድረስ ከኢትዮጵያ ጋር በአንድነት እንዳትኖር ያደረጉ እንግሊዞች ናቸው። እንዲያውም ለመጀመሪያ ጊዜ ኤርትራ ውስጥ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ሕዝቡ እርስ በርሱ ደም የተቃባው በእንግሊዞች ሤራ ነው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኤርትራ ውስጥ በየምክንያቱ ደም ይፈሳል።

ንጉሡ ወይም መሪው የአገሪቱ መሆን ሲገባቸው፣ በተቃራኒው ሕዝቡም አገሪቱም በጠቅላላ የንጉሦች ወይም መሪዎች ለልጆቻቸው የሚያወርሷቸው ሃብትና መገልገያ ለመሆን ተገደዋል። ከዚህ ዓይነት ማነቆ ሕዝቡን ለማውጣት ጥቂት በጥቂት ብልህ የሆኑ ሰዎች በሞከሩ ቁጥር በተናጠል ይመታሉ ወይም እንደ እርኩስ ይወገዛሉ። ሥልጣን ላይ ያሉ ሁሉ በጣም የሚጠሉት ነገር ቢኖር እንደዚህ ዓይነት ሙከራን ስለኾነ ለሰላዮች፣ ለልዩ ጠባቂዎቻቸውና ዝናቸውን ከፍ ለሚያደርግ ፕሮፓጋንዳ የሕዝቡን ሃብት ያባክናሉ። የሕዝቡን ልጆችም ለወታደርነት በመመልመል ብዙ ጥፋት ያደርሳሉ። ቀስ በቀስ በዓለም ውስጥ ንጉሦች ጠፍተው በሕዝብ በተመረጡ አስተዳዳሪዎች የሚተኩት ለዚህ ነው። ችግሩ ግን አዲሶቹም ተመራጮች ዘዴና የማዕረግ ስም ለውጠው

ሥርዓታቸው ከንጉሦቹ አልተለየም። ስለሆነም ይህች ዓለም ለሰው ልጅ ያማረ ኑሮ መኖርያ መሆን ሲገባት የፍዳና የመከራ ዓለም ሆና እስከ አሁን ቀጥላለች። ዴሞክራሲ የሚለው ቃል በአሁኑ ጊዜ ሰውን ውኸርንብር ውስጥ የከተተና ትርጉሙም እየተዛባ የሚገኝ ሆኗል።

## ሞናርኪ (ንጉሣዊ መንግሥት)

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ በንጉሥ አገዛዝ የሚያምን (ሞናርኪስት) የኾነ ሞዓ አንበሳ የሚባል ፓርቲ ተደራጅቶ ይገኛል። በመሠረቱ ማንኛውም ዓይነት ፍልስፍናን የሚከተል ፓርቲ መመሥረት፣ መደራጀት፣ ማኅበርተኛ ማብዛት፣ ፍልስፍናውን ማስተማርና በምርጫም የመሳተፍና ካሸነፈም በፍልስፍናው መሠረት አገሪቱን ማስተዳደር መብቱ ነው። ስለሆነም የሞዓ አንበሳ መኖርና መንቀሳቀስ ተገቢና የሚደገፍ ነው። ማኅበርተኛም ባይሆኑ ብዙ የንጉሣዊ አስተዳደርን የሚደግፉ ሰዎች አሉ። ይሁንና ፍጹማዊ የንጉሠ ነገሥታ መንግሥት (Absolute Monarchy) ይኑር ለማለት የሚደፍር ሰው በአሁኑ ወቅት ቢኖርም ቁጥሩ በጣም አነስተኛ ነው።

ለኢትዮጵያ የንጉሣዊ መንግሥት አስተዳደር ይሻላታል ብሎ መከራከርና መታገል ዓላማው ስለኾነ ሌሎች ፓርቲዎች እንደሚያደርጉት ሁሉ ሕዝብ ፊት እየቀረበ ውይይት ማድረግና ፍልስፍናውን ማሳመን ይኖርበታል። ዓላማው ቢሳካና በምርጫ ፓርቲው ቢያሸንፍ ንጉሥ እንደሚያነግሥ ዕሙን ነው። ነገር ግን ለንጉሠ ነገሥትነት የሚመረጠው ሰው መሠረቱ ታሪካዊ ቅርስነቱ ስለኾነ መንገሥ ያለበት ትክክለኛው ንጉሥ መሆኑ ተጣርቶ መቅረብ ያለበት በመጀመሪያ በፓርቲው አባሎች በድምጽ ብልጫ ነው። ቀጥሎም ንጉሥነቱ ለመላው ኢትዮጵያ ስለኾነ የኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ ተወያይቶበት፣ የታሪክ ተመራማሪዎች ተችተወበት በፓርላማ መጽደቅ ይገባዋል። እንዲያውም ይህ ፓርቲ ንጉሥ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል ብሎ ከሕዝብ ጋር መወያየት ዋናው ዓላማው መሆን አለበት እንጂ እንደሌሎች ፓርቲዎች የእኔ ፓርቲ አገሪቱን ያስተዳድር ብሎ መሳተፍ ዓላማው መሆን የለበትም። ምክንያቱም ፓርቲው አሸንፎ ሥልጣን ቢይዝ የሚሾመው ንጉሥ ፓርቲው በምርጫ ከሥልጣን የወረደ ዕለት ንጉሡም ይወርዳል ማለት ይሆናል። ስለሆነም ፓርቲው አሰባሳቢና አስረጅ ፓርቲ ስለሚሆን



ሕዝብ መካከል መግባትና የሌሎች ፓርቲ አባሎችንም ማስረዳትና ማሳመን ይኖርበታል። ሞናርኪን እቀበላለሁ ያለውን ፓርቲ በምርጫ ጊዜ የሞዓ አንበሳ አባሎች ድምጽ በመስጠት እንዲደግፉና አልቀበልም ያለውን ፓርቲ እንዳይደግፉ ዘመቻ ማድረግ ይችላል፣ ኃይሉም ይኸው ብቻ ይሆናል። አንድ ጊዜ ሕገ መንግሥት ውስጥ የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር ንጉሥ መሆን አለበት የሚል አንቀጽ ከገባ በኋላ ፓርቲው አሠራሩን ቀይሮ የቅርስ ወይም የባሕል ጠባቂ አካል መሆን ይኖርበታል።

የፓርቲው አሠራር ከላይ እንደተጠቀሰው መሆን ሲገባው ፓርቲው በአላስፈላጊ ሽኩቻ ጊዜ እያባከነ ይመስላል። አንድ ጊዜ የልዑል ማህለ ሥላሴ ልጅ ልዑል ኤርምያስ ቀጣይ ንጉሥ ይሁኑ የሚል ቡድንና የልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን ወገን የሆኑ ሲጨቃጨቁ በዘመኑ የፓርቲው ዋና ጸሐፊ የነበሩት አምባሳደር ዶክተር ጌታቸው መካሻ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን በሚገፋ ወንበር እየተንቀሳቀሱና መናገር ሲቸገሩ እየታየ "ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋው ወሰን በሙሉ ጤንነት ይገኛሉ" ብለው በይፋ ተናገሩ። በአሁኑ ሰዓት ደግሞ መንገሥ ያለበት የልዑል መኮንን ልጅ ልዑል በዕደ ማርያም ነው ብለው የሚከራከሩት ከልዑል ኤርሚያስ ደጋፊዎች ጋር በውዝግብ ላይ ናቸው ይባላል። የውስጥ ሹቅሹቅ የሌለው ቡድን ወይም ፓርቲ ያለመኖሩ ባይካድም ትችቱ የሚያተኩረው ግን ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን የሚያጠፉት ዓላማቸውን ግብ በሚያደርስ ጉዳይ ላይ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

በንጉሠ ነገሥቱ ዘመነ መንግሥት ስለሪፐብሊክ አገዛዝ ደፍረው የተናገሩት ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሃዋርያት ብቻ ነበሩ። ሌላው ይኸ ነገር ነሳበት 'ኧረ ዝም በል እንዲህ ዓይነት ነገር ኢትዮጵያ ውስጥ ሊኖ/ አይችልም' ይል ነበር። ዛሬ ደግሞ ስለንጉሥ መመለስ ሲነሳበት 'እዬ ከእንግዲህስ ወዲያ ሊሆን አይችልም' ይላል። እንዳይሆን የምንፈልገው ሥልጣን በአንድ ሰው እጅ ብቻ እንዳትገባ እንጂ ንጉሥም፣ ፕሬዚዳንትም፣ ጠቅላይ ሚኒስትርም ኾኑ ሥልጣኑ በአንድ ሰው እጅ እስከገባ ድረስ የዴሞክራሲ አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም። የሚሻለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍንና ሥልጣኑ በሕዝብ እጅ እንዲገባ ለማድረግ መጣጣር እንጂ አንድ ሰው በወኪልነት

ቢቃወጥ ተግባሩ ውሳኔን በተጠያቂነት መፈጸም ሲሆን የተቀረው ወግ ነው።

የንጉሣዊ ሥርዓት ለአገሪቷ የሚበጅበትን ሁኔታ ለሕዝብ ማሳወቅና ያለፈውን ስህተት እያረመ ለወደፊት የሚሻለውን አስተዳደር መቅረጽ እንደ አማራጭ ማቅረብ ነው። የንጉሦች አገዛዝ በይፋ እየተወገዘ ባለበት ወቅት ሞዓ አንበሳ በይፋ በፓርቲነት መሳተፍ ካልደፈረ እንደ እርምጃ ጎታች ቡድን ስለሚታይ በሕዝብ ዘንድ ይናቅና ፓርቲውም ፍልስፍናውም ቀስ በቀስ ይከስማሉ። ማንም ይንገሥ የፓርቲው ተቀዳሚ ዓላማ ግለሰቡ ሳይሆን ፍልስፍናውና ባህል መሆን ይኖርበታል። ቀደም ብሎ ንጉሡ ነገሥቱ የሠራው ጥፋት ካለ የሚቀጥለው ጥሩ የማይሠራበት ምክንያት የለም። ንጉሥ ሱስንዮስ ሃይማኖቱን ለውጠ ስምንት ዓመት ሙሉ ሕዝብ ካፋጀ በኋላ ልጁ ፋሲል ነግሦ ወደ ጥንቱ ሃይማኖት ተለውጠ ሠላም ስለወረደ ብዙ ሥራ መሥራት ችሏል። በመሠረቱ የአንድ ሰው ኃብቱ እንጂ ወንጀሉ አይወረስም።

ኢትዮጵያ ንጉሥ ቢኖራት ጥሩ የሚሆኑባቸው ምክንያቶችም ይኖራሉ። የሰው ልጅ እንደ ንብ ዓይነት የተፈጥሮ ጠባይ ስለአለው መሪውን ይወዳል፣ ይከተለዋል፣ በሱም መወከልን ይመርጣል። አንድ ሰው ፕሬዚደንት ተብሎ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከሚቀመጥ ባህልን መሠረት ያደረገ ብዙ ታሪካዊ ወጎችን የሚከተል ንጉሥ ቢኖረው መልካም ይሆናል። በዘመናችን ቅርስና የቱሪስት መስህብም ነው። አንድ ሰው ላይ የተጫነውንም የሥልጣን ኃላፊነት ሊጋራ ይችላል። ለምሳሌ በርዕሰ ብሔርነት አገሪቱን ከመወከል በተጨማሪ የፍትሕን ሥራና የምርጫ ኮሚሽንን ሃላፊነት ሊሸከም ይችላል። ለአገሪቱ አንድነት ከፕሬዚደንቱ የተሻለ አስተዋጽዖ ይኖረዋል። ብሪታኒያ፣ ኖርዌይ፣ ስዊድን፣ ኔዘርላንድና ስፔይን የተሰደዱትን ንጉሦቻቸውን መልሰው በቦታቸው አስቀምጠዋል። ጃፓን ንጉሥ ስላላት ትኮራበታለች እንጂ ሥልጣኔዋን አልገታውም። አፍሪካ መተባበርን ዓላማ እያደረገች ስለመጣች አንድ የጥቁር ንጉሥ ቢኖራት እንደ ክብር ስለምትቆጥረው በዚህም መስመር ነገሩን ተመልክቶ እንደ አማራጭ መዘጋጀት ጥሩ ይመስላል። የሴንትራል አፍሪካ ሬፑበሊክ መሪ ቦካሳ በነገሡበት ጊዜ የሰጡት ምክንያት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሲሞቱ የተካቸው ስለሌለና ለአፍሪካ ንጉሥ ስለሚያስፈልጋት እኔ መንገሥ አለብኝ የሚል ነበር።



ንጉሥ በሚነግሥበት ጊዜ በሃይማኖት ሥርዓት ይከናወን ስለነበረ ንጉሥ ይንገሥ ቢባል የሃይማኖት ጉዳይ መነሳቱ አይቀርም። እያንዳንዱ የሃይማኖት ቡድን የራሱን ሃይማኖት ብቻ የአገሪቱ ሃይማኖት ለማድረግ እንደሚፈልግ ደግሞ ግልጽ ነው። ስለሆነም ለጊዜው የሃይማኖት ጭቅጭቅ የንግሥና አፈጻጸም ላይ እንዳያውክና ሁሉም በኅብረት ንጉሡን ወኪላቸው፣ ጌጣቸውና ቅርሳቸው መሆኑን እንዲገነዘቡ ያስፈልጋል። የቀዳማዊ ምኒልክ ተወላጆች እስከ ኤዛና ድረስ በቤተ ክርስቲያን ወግ እንዳልነገሡ ይታወቃል። በአጠቃላይ ስለንጉሡ ሃይማኖት በአሁኑ ሰዓት ችግር መፍጠር ለንጉሡ ሹመት እንቅፋት ስለሚሆን ለጊዜው እንደበፊቱ አክናውኖ ምናልባት ስለዚህ ጉዳይ ወደፊት በተረጋጋ ምንፈስ በምክር ቤት መወያየትና ሁሉንም የሚያስደስት ሕግ በሕብረት ማውጣት ይቻላል። ኢትዮጵያ ከእንግዲህ ወዲህ የክርስቲያን፣ የእስላም፣ ወይም የቡድሃ ሃይማኖት አገር ነች ብሎ መመደብ አይቻልም። ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን አገር ነች ተብላ መጠራት ብቻ ነው ያለባት። ምክንያቱም ሃይማኖት የግል፣ አገር የጋራ ነውና።

ጃንሆይ በዘመናቸው አሻፈረኝ አሉ እንጂ ሕዝቡማ ይደረጋል ብሎ የጠበቀው ለሕገ መንግሥቱ የሚታዘዝ ንጉሠ ነገሥት እንዲኖርና አገሪቱ በሕዝብ በሚመረጥ ጠቅላይ ሚኒስትር እንድትተዳደር ነበር።

ይሁንና ሕዝቡ በሰፊው ተወያይቶ ንጉሥ አያስፈልግም ብሎ ከወሰነ ኢትዮጵያ ሬፓብሊክ መሆን ይኖርባታል። ምናልባት እንኳን በንጉሥ መተዳደር የሚመረጥ ከኾነ ንጉሡ ሥራ ስለሚሠራ ደሞዝ ቢቆረጥለትም የንጉሣዊ ቤተሰቦችን ልዩ ፍጡር አድርጎ መመልከትና ሳይሠሩ የክብር መጠበቂያ ደሞዝ መክፈል ተገቢ አይሆንም።

ተቴዎድሮስ አንስቶ ተፈሪ ድረስ
ዘመኑ ይበቃል የዘውድ ንጉሥ
ንጉሥ አለ ብለህ አትወሳወስ
በምርጫ ታልኾነ የለም የሚነግሥ
ግን ሕልቁን አየሁት ብዙውን ቲያለቅስ
ሺህ ሁሴን ጅብሪል



# ምዕራፍ ፵፪

## የምሁራን አስተዋጽዖ

ምሁሮች ኢትዮጵያን በፍጥነት እንደ ጃፓን ለማሠልጠን ያለሙት ገና ልጅ ኢያሱና ተፈሪ መንግሥት ለመያዝ በሚታገሉበት ዘመን ነበር። በወቅቱ የነበሩት ምሁሮች ቁጥራቸው በጣም ጥቂት ቢሆንም ስሚ የሚያገኙ መስሏቸው በዘመኑ በሚወጡት ጋዜጦች ያሰሳንሱር ይጽፉ ነበር። በራስ ተፈሪ አልጋወራሽነት ዘመን ማተሚያ ቤት ተስፋፍቶ መንግሥት ጋዜጣ ማውጣት ሲጀምር የነዚህ ሰዎች ጽሑፍ ከጋዜጣው እየጠፋ ሄደ። እነሱም የሚያደርጉት መፍጨርጨር ተገታና መኖራቸውም ተረሳ።

በኋላ ላይ የተማረው ሰው ቁጥር መጨመር ሲጀምር ጠላት አገሪቱን ይወርና የተሰደዱት ብቻ ሲቀሩ ጣሊያን እያሳደደ ፈጃቸው። ከስደት መልስ ከፍተኛ የመልሶ ማቋቋም ሥራ ስለነበረ የተረፉት በየመሥሪያ ቤቱ ተዋጡና ለነበረው እንቅስቃሴ ቁጥራቸው አነሰ። ከጊዜ ብዛት አዲስ ተማሪም ወደውጭ በብዛት እየሄደ ሲመለስ በአገርም ውስጥ ትምሕርቱን እየጨረሰ በየልዩ ልዩ ሙያ የተሰማራው በመንግሥቱ አሠራር ላይ ቅሬታውን በየምክንያቱ ማሳየት ጀመረ። ይህ የተማረው አዲስ ትውልድ የመሳፍንቱንም ልጆች ይጨምራል። እነ ልጅ ሚካኤል እምሩ ከየወጣቱ ጋር ስብሰባ ላይ የሚናገሩት ስላልተወደደላቸው ወደ መስኮብ አገር ተልከው እንዲርቁ ተደረገ። በነገራችን ላይ አንድ ሰው ለትምህርት ካልኾነ በቀር ወደውጭ አገር ሲላክ በዘመኑ መቀጣቱ ነበር።

በኋላ ግን የታወቁ ወጣት ተናጋሪዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ለምሳሌ ያህል ዶክተር እሸቱ ጮሌ በጣም የታወቀ ኤኮኖሚስትና ንግግር አዋቂ በዩኒቨርሲቲው አዳራሽ ንግግር ሊያደርግ ነው ተብሎ ሕዝብ ሲሰበሰብ መንግሥት ይከላከል ነበር። የጃንሆይ መንግሥት ተገልብጦ የደርግ መንግሥትም ቢመጣ ለዶክተር እሸቱ ጮሌ በመንግሥት ዜና ማሰራጫ



ድምጹን ሕዝብ እንዲሰማው ዕድል ተሰጥተቶት አያውቅም። አንድ ጊዜ ብቻ በስህተት በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ መናገሩ ይታወሳል።

ደርግ ንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን አውርዶ ምሁሮችን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ አስተያየት እንዲሰጡ ቢጠይቃቸው ድሮ አፄ ምኒልክ ተማሪ (ምሁር) ወላዋይ ነው እንዳሉት ሚናው ካልተለየ እንናገርም አሉ። እንዲም የፈሩት የተማሪው የኮሙኒስት ቡድን ኮሙኒዝምን የማይደግፍ ሰው ላይ ያደርሱት የነበረውን ደባ ነበር።

የኾነው ሆኖ የእነሱ ዝምታ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመጣበትን አደጋ አስቀድሞ እንዳያውቀው በፍርሃት አፋቸውን ዘግተው በነበረው ከፍተት የማወቅ ዕድሉን ነፈጉት። ምሁሩ በዚያን ጊዜ የኮምኒስትንና የሊላውንም ጥሩና መጥፎ ጎን ለያይተው እንደማስረዳት አፋቸውን ዘግተው የታሪክ ስህተት ሠሩ። ኮሙኒዝም ከታወጀ በኋላ ግን ጥሩነቱን ለመናገር ቀደም ቀደም ማለታችው ይታወሳል። አሁንም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ የጎሣዎችን የእኩልነት ትግል ፈሩን እያሳቱ ኢትዮጵያን ለመበታተኛ መሣሪያ ለማድረግ የሚጣደፉትን ማሳፈርና ሃቆቹንም ከሕዝቡ ጋር መወያየት ሲኖርባቸው አፋቸውን እንደተለመደው ለጉመው መቀመጥን የመረጡ ብዙ ምሁሮች አሉ።

በጠቅላላው ምሁሮች በፖለቲካ አመራር ላይ ፊትለፊት የመጋፈጥ ጠባይ የሌላቸው ሲሆኑ ሥልጣን የያዘን ለመተቸት ወይም ለእሱ ወግነው የአሠራሩን ጥሩነት ለሕዝብ ለማስተጋባት ግን ዝግጁ ናቸው። ዝም እንዳይሉ ብዙ ስለሚያውቁ ሕሊናቸው እንዲናገሩ ያስገድዳቸዋል፣ እንዳይገቡበት ተጠራጣሪ ስለሆኑ የመሪነቱን ቦታ መቀበሉ ያቅታቸዋል። የጋና ሕዝብ የምሁር መሪ መርጦ ቢያስቀምጥ የባሰ ግራ የተጋባ ስለሆነባቸው መልሰው ሽረውታል።

የብዙ አገር መሪዎችን በአትኩሮት ብንመለከት ለመሪነት የሚመርጡት የመሪ ጠባይ ያለውን እንጂ በዕውቀት ደረጃ ከፍተኛ ዝና ያላቸውን ሆኖ አናየውም። በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ዘመን የታወቁት የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ዊንሰተን ቸርችል የትምህርት ማሕደራቸው የሚያኩራራ አልነበረም። እጅግ በጣም ብዙ ዩኒቨርስቲዎች ባሉበት የአሜሪካ አገር ለፕሬዚደንትነት የሚመረጡት ፕሮፌሰሮች ሳይሆኑ በየፓርቲው ውስጥ ጥሩ እንደበት ያላቸው ፖለቲከኞች ናቸው። አንዳንዴ

መሪ ለመሆን ግርማ ሞገስና ችሎታ ያለው ተወዳዳሪ እየጠፋ ፓርቲዎች ሰው ለማቅረብ የሚቸገሩበትም ጊዜ አለ።

በሂንዱ ሃይማኖት ላይ ተንተርሶ ዶክተር ራቪ ባትራ የሚባል ኢኮኖሚስት "ዘ ግሬት ዲፕሬሽን ኦፍ 1990" በሚለው መጽሐፉ ሲተነትን የሰውን ልጅ በአራት ይከፈለዋል። እሱውም ጦረኛ፣ ገበሬ፣ ሠራተኛና ምሁር ናቸው ይላል። እንደ ፍልስፍናው ገበሬም፣ ሠራተኛም፣ ምሁርም፣ መሪ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ ይደመድማል። መሪነትን ለጦረኛ ወይም ለወታደር የሚከልለው እየተዋጋ የማስተዳድር ኃላፊነቱን የሥራ ክፍሉ አድርጎ ስለሚያየው ነው። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል የአገራችን ታሪክ ደጃች እገሌ የዚህ አገረ ገዥ በዚህ ጦርነት ድል መቱ ወይም ተሸነፉ በሚል የተሞላው። ስለሆነም ተማሪ ወይም በአሁኑ አጠራር ምሁር በጦረኛው ጥላ ስር ኃይሉን ያደራጅና የሚፈልገውን እያሳመነ ያስፈጽማል። ጦረኛውም ለምሁሩ ሳይስማማው የቀረ እንደ ኾነ ምሁሩ ጦረኛውን ገዝግዞ ይጥለዋል።





# ምዕራፍ ፴፫

## የተማሪ ንቅናቄ

ተማሪ ሕዝብ ሲበደል፣ አገር ሲጎዳ፣ ግፍ ሲሠራ፣ ዓይቶ ዝም ብሎ ማለፍ አይችልም። በተለይ ዘመናዊው ትምህርት በኢትዮጵያ መስፋፋት ከጀመረ አንስቶ ተማሪዎች ነገሮች አልጥም እያሉዋቸው በተለያዩ ጊዜዎች ተቃውሞዎች አድርገዋል። በ1923 ዓ.ም. በማኅበር ደረጃ ነገሮችን ለማስተካከል ተደራጁ። ደግነቱ ያኔ አትሰብሰቡ የሚል ሕግ ስላልነበረ ለመሰብሰብ የሚያስፈራ ነገር አልነበረም።

በ1928 ዓ.ም. ጠላት ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ ማኅበር ሊኖር ቀርቶ የተማረ ሰው ሁሉ እየታደነ ይፈጅ ስለነበረ ተማሪዎቹ ተበታተኑ። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ግን በውጭ አገር የኢትዮጵያ የተማሪዎች ማኅበር በነገርማሜ ንዋይ ተመልሶ አቆጥቁጦ ነበር። በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ውስጥ የንግግር ነፃነት ስለነበረ ተማሪዎች እንደልባቸው የፈለጉትን ቢናገሩ፣ ባለሥልጣንንም ይሁን ድርጅት ቢተቹ አይከሰሱም ነበር። በአንድ ወቅት ቀኃሥ ለአዲስ አበባ ኮሌጅ ክብረ በዓል መጥተው በነበረ ጊዜ የግጥም ውድድር አሸናፊዎች



ጥላሁን ግዛው

ግጥማቸው ሲነበብ አሽሙር በቀላቀለ ቋንቋ ተችተዋቸዋል። ንጉሡ ነገሥቱም ከዚህ ወቅት በኋላ በየዓመቱ ለክብረ በዓሉ መገኘቱን ተውት። ተማሪዎቹ የራሳቸውን የተማሪ መማክርትና ተወካዮች በመምርጥ ጉዳያቸውን መከታተልና ጋዜጦችም ማዘጋጀት ጀምረው ነበር። የተማሪ ንቅናቄ በስፋት የተጠናከረው ግን ከታኅሣሥ 1953 ዓ.ም ግርግር ጀምሮ ነው። የታህሣሥ 1953 ዓ.ም የመንግሥት ግልበጣ መሪ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ በግልበጣው ወቅት ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መካከል ተገኝተው "እኛ መስኮቱን ከፍተናል በሩን የምትከፍቱት እናንተ ናችሁ" በማለት ለተማሪው ንቅናቄ መቀጣጠል ልዩ አስተዋጽዖ ያበረከተ ንግግር አደረጉ።

ቀጥሎም ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ብቻ የተሰጣቸውን ነፃነት በመጠቀም ያላቸውን ቅሬታ ቢገልጹም ምንም ፋይዳ ስላልነበረው ሕዝቡን ለመቀስቀስ በየምክንያቱ ከተማ ውስጥ ሠላማዊ ሠልፍ ያደርጉ ጀመር። ሠላማዊ ሠልፍ ሲያደርጉ ፖሊስ ይታዘዝና ሲያግዳቸው ድንጋይ መወራወር ይጀመርና ከፖሊስ ጋር ግጭት ይፈጠራል። በተማሪና በፖሊስ መካከል በሚፈጠረው አምባጓሮ አንድ ወይም ሁለት ልጅ በተኩስ ይገደልና ነገሩ ሕዝብን ካስደነገጠ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ በራዲዮና በቴሌቪዥን ንግግር አድርገው እንደገና ትምሕርት ይጀመራል። ይህ ሁኔታ በተደጋጋሚ ለ**13** ዓመት ሳያቋርጥ ቀጥሏል።

ሌላው የተማሪዎችን የፖለቲካ ንቃተ ሕሊና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደረሰው ጉዳይ ለ**200** የአፍሪካ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የተሰጣቸው የነፃ ትምህርት ነው። የአፍሪካ ተማሪዎች የመጡት አፍሪካ ውስጥ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ መውጣት በተጀመረበት ወቅት ስለነበረና የተማሪ ንቅናቄ ልምድም ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ከእነሱ ብዙ ነገር ቀሰሙ። ምናልባት ጃንሆይ ለዝና ብለው ያደረጉት ችሮታ ተማሪውን አስገንግኖ የራሳቸው ጠላት እንዲሆን አፋጠነው ማለትም ይቻላል።

እነመንግሥቱ ንዋይ የመንግሥት ግልበጣ ሞክረው ከከሸፈ በኋላ ወጣቱ ትውልድ የንጉሠ ነገሥቱ ተቃዋሚ መሆኑ ስለታወቀ አንድ እበላባይ ጋዜጠኛ 'ገርማሜ ንዋይ ኪስ ውስጥ የተገኘ ወረቀት ከ40 ዓመት ዕድሜ በላይ የኾነ ሰው ሁሉ እንዲገደል ይላል' ብሎ በሬዲዮ አስነገረ። በዚህን ጊዜ ራሱ መንግሥቱ ንዋይ ዕድሜው 44 ዓመት ነበር። በዚህ ምክንያት



ዕድሜያቸው ከፍ ባሉ ሰዎችና በወጣቱ መካከል መቃቃር ተጀመረ። ይኸው አስተሳሰብ ቀጥሎ በደርግ ዘመነ መንግሥትም ቢሆን ወጣቱ በዕድሜ በገፉ ሰዎች በጥርጣሬ ዓይን ይታይ ስለነበረ በሚያካሂደው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ላይ የአዛውንቶችን ድጋፍ ተነፍጓል። ጋዜጠኛው ለትንሽ ሹመት ብሎ የረጨው መርዝ የአገሩን ሕዝብ መርሆ በአንድ ልብ እንዳይቆም አድርጓታል።

የኾነው ኾኖ የአገሪቷ በስልጣኔ ወደ ኋላ መቅረትና በኤኮኖሚ አለማንሰራራት በተማሪዎች አሳሳቢነት ሕዝቡን እያስገነገነ አኩራፊ እየበዛ ሄደ። የተማሪው ግብግብም ከመንግሥት ጋር እየጨመረ ሄደ። አስከትሎም የተማሪውን ኃይል ለማስደንገጥና የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ መንግሥት እርምጃዎችን ወሰደ። ከእርምጃዎቹም መካከል የልዑል መኮንን ባለቤት ታናሽ ወንድምና በወቅቱ የተማሪዎች ፕሬዚዳንት የነበረውን ጥላሁን ግዛውን የፀጥታ ኃይሎች አድብተው ማታ የሴት ጓደኛውን ከወንድሙ ከመኮንን ጋር ሊሸኝ ሲወጣ በጥይት ገደሉት። እንደሚባለውማ ልጅቷ ራሷ እሱ ሳያውቀው በፍቅር እንድታጠምደው የተላከችበት ወዳጁ እንደነበረች ነው። በጥይት እንደተመታ ደጃች ባልቻ ሆስፒታል ውሰዱኝ እያለ ሲል ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (የካቲት 12) ሆስፒታል ተወሰደ። ተከትሎት የሄደው ብዛት ያለው ተማሪ ቁስለኛው ከነበረበት አዳራሽ ተባሮ ያጣጥር የነበረው ልጅ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሕይወቱ ማለፉ ተነገረ። በዚህ ምክንያት በማግስቱ ዩኒቨርስቲው



ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም

ቅጥር ግቢ ውስጥ ታላቅ ብጥብጥ ተነስቶ በወታደሮች ተኩስ ብዙ ተማሪዎች ሲሞቱ የበለጠ ቁጥር ያለቸው ተማሪዎችም ቆሰሉ።

ተማሪዎቻቸውን ከጥቃት ለማዳን ይታገሉ የነበሩት የቀድሞው የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ልጅ ካሣ ወልደ ማርያም በዶክተር አክሊሉ ሃብቴ ተተክተው ስለነበረ አዲሱ ፕሬዚዳንት ግን ያሁሉ ተማሪ ጉዳት ሲደርስበት ባለመከላከላቸው ሕዝቡ አዝኖባቸዋል። ሆኖም የፊተኛው ፕሬዚዳንት የባላባት ልጅ የነበሩና

አዲሱ ግን የድሃ ልጅ ስለነበሩ ሞክረውም ቢሆን የሚስማቸው እንደማይገኝ ግልጽ ነበር።


ዶክተር አክሊሉ ግብቱ

በተማሪው ንቅናቄ መሃከል ዩንቨርስቲው ውስጥ ክሮኮዳየል በመባል የሚታወቅ የኮሚኒስት ቡድን ተደራጅቶ የተማሪውን እንቅስቃሴ መጨረሻ ላይ በድርጅታዊ አሠራር ለመቆጣጠር ቻለ። ድርጅታዊ አሠራርን ለቀጣዩ መንግሥት ያስተማረ የኸው ቡድን መሆኑ ይታወቃል። በዘመኑ የነበረው ተማሪና ወጣት ለውጥ ፈላጊ ብቻ እንጂ የምንም ርዕዮተ ዓለም አራማጅ ስላልነበረ በአገር ፍቅር ስሜት እየተገፋፋ የተሻለ አስተዳደር በለውጥ እንዲመጣ ሲመኝና ሲታገል ኮሚኒስቶቹ ላለሙት ግብ መሣሪያ አደረጉት። ለዴሞክራሲ እንዋጋለን የሚሉት የኮሚኒስት ቡድኖች ራሳቸው የተማሪውን የዴሞክራሲ መብት ነጥቀው እነሱን የተቃወመውን ሁሉ የሕዝብ ጠላት አስመስለው ማቅረብ ጀመሩ። ለውጡ ዕውን መሆን ሲጀምርና የንጉሡ ነገሥቱ ሥልጣን ወደ ወጣት መኮንኖች መዞር ሲጀምር የተማሪዎች ንቅናቄ ከአገር ውጭ መከፋፈል ጀመረ። ወታደሮቹ ሥልጣን ሲይዙ እነሱን እንደግፍ ወይስ አንደግፍ በሚለው ላይ ውዝግብ ተነስቶ አብዛኛው ተማሪ አንደግፍም በማለት በራሳቸው አገላለጽ "ምንም ቢሆን ወታደር ፋሽስት ነው" ብለው ሲስማሙ የድምጽ ብልጫ ያላገኙት ወገን ዘለው አዲስ አበባ በመግባት ከወታደሩ ጋር አብሮ ለመሥራት ተቀላቀሉ። ደጋፊዎቹ የኮሙኒስቱ ቡድን መኮንኖቹን የሚመጣው ችግር ሳይገባቸው ኮሙኒስት ነን ብለው እንዲያውጁ አደረጓቸው።

ሌላው ወገን ወታደሩ የያዘውን ሥልጣን በአብዛኛው ተማሪው እንዳይቀበለው ስላደረጉ መኮንኖቹ አጋር ሲያገኝ እሾክን በሾክ ነውና የጸጥታ ሠራተኞችን ለደጋፊዎቹ ረዳት ስላደረጉዋቸው እነዚህ ወዶ ገባ ተመሪዎች ዋና ጠላት አድርገው የያዙት የተማሪውን ንቅናቄ ስለኾነ በውጭ አገር አብዮቶች ላይ እንደተደረጉት ዓይነት ጥቃቶች በወጣቱና በተማሪው ላይ ዘረጉ። እነዚህም ጥቃቶች ሽብር፣ ፕሮፓጋንዳ፣ ስም



ማጥፋት፣ ሰልፍ፣ እስር፣ ግርፊያ፣ በከተማና በገጠር በየመንደሩ ውስጥ ያሉ ቦዘኔዎችን እየሰበሰቡና እያደራጁ መሣሪያ በማስታጠቅ ወጣቱን ማሰቃየት ተያያዙት። ወጣቱም ከስቃይ ብዛት የተነሳ ራሱን ለማዳን የከተማ ጦርነት (ነጭ ሽብር) አውጆ ደጋፊዎችን በተናጠል እያደነ መግደል ጀመረ። አብዮቱን ለማዳን በሚል ሽፋን በደጋፊዎች ላይ የተከፈተውን ጦርነት ለመቋቋምና መልሶ ለመምታት በማለት ሌላ (የቀይ ሽብር) ዘመቻ በመንግሥት ተፈቅዶ የሰው መግደል መብት ድረስ በአዋጅ ስለሰጡዋቸው በየመንደሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተፈጸመ የወንጀል ዓይነት አልነበረም። አብዛኛው ተቃዋሚ ተማሪ በጥቂት ደጋፊዎች ከመንግሥት እገዛ ጋር ሲመታ የተጎጂውን ብዛት መገመት ይቻላል። የሞተው ሞቶ በዙዎችም በአማራጭ ከአገር ውጭ መሰደድ ተገደዱ። ደጋፊዎቹም መጨረሻ ላይ ከመኮንኖቹ ጋር ስለተቃቃሩ በተራቸው እነሱም ተመቱ። አገሪቱ ስታስተምርና ስታሠለጥን የቆየችው የተማረ ወጣት ኃይል ከሁለቱም ወገን ከመፈጀቱም በላይ በስደት ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር መኮብለልን ተለማመዱት። ይኸንንም ክስተት የውጭ አገር ጸሐፊዎች 'እንደ የተፈጀ ትውልድ' (The Lost Generation) በማለት ገልጸውታል።

# ምዕራፍ ፵፬

## የሕዝብ እንቅስቃሴ

ንጉሠ ነገሥቱ ዝናን በጣም ይወዱ ስለነበረ የውጭ አገር ጉብኝት እያደረጉ ከአገሪቷ አቅም በላይ ወጭ ይወጣ ነበር። ከጉብኝቱም መልስ አገሪቱ የምታገኘው ጥቅም ዲፕሎማሲያዊና የሕዝብ ግንኙነት ብቻ እንጂ የኢኮኖሚ ጥቅም አይታይም ነበር። በመንግሥት የዜና ማሰራጫ በኩል ቢሆንም የንጉሠ ነገሥቱን ዝና ከፍ ከማድረግ ሌላ ለሕዝቡ ጠብ የሚልለት ነገርና ተስፋ ሊሰጠው የሚችል ሁኔታ ሊታይ አልቻለም። ሕብረተ ሰቡ ይኸ የንጉሠ ነገሥቱ የውዳሴ ከንቱ ሥራ ስላልጣመውና የባለሥልጣኖቹንም ሁኔታ እየታዘበ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥርዓቱን እያወገዘው ሄደ።

### መፈንቅለ መንግሥት

የክብር ዘበኛ መኮንኖች በጀኔራላቸው በመንግሥቱ ንዋይ የሚመራና በተማሩ ወጣት ሲቪሎች የታጀበ የመንግሥት ግልበጣ በታኅሣሥ ወር 1953 ዓ.ም ሞከሩ። ጃንሆይ ጉብኝት ላይ እያሉ ድንገት በሬዲዮ በአልጋ ወራሽ አስፋወሰን ድምፅ የጃንሆይ ከሥልጣን መውረድ ታወጀ። ነገር ግን የጦር ሠራዊት መኮንኖች እነ ጄኔራል መርዕድና ጄኔራል ከበደ ገብሬ ከነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ሃሳብ ጋር ስላልተስማሙ በሁለቱ ጦር መካከል አነስተኛ ግጭት ተደርጎ ግልበጣው ከሸፈ። መጨረሻ ላይ የክብር ዘበኛ ጦር ተፈረካክሶና የሞተው ሞቶ የመንግሥት ግልበጣው መሪዎች ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ከወንድሙ ከገርማሜና ከሻለቃ ባዬ ጥላሁን ጋር ሸሹ። ጎንደሬው ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁም እንደ ቴዎድሮስ ጥይቱን ጠጥቶ ሞተ። ጀኔራል ጽጌ ዲቡም ተገድለው ሬሳቸው አራተኛ ክፍለ ጦር ተዘርግቶ ታይቷል።

መፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፉን እንደተረዱ እነመንግሥቱ ንዋይ ተይዘው የነበሩትን ሚኒስትሮች፣ መኳንንቶችና የጦር አለቆች ረሸኑ። ከተረሸኑት መካከል የጦር ሚኒስትር የነበሩት ራስ አበበ አረጋይ፣



የቀኃሥ የግል በጅሮንድ አባ ሃና ጅማ፣ መኮንን ሃብተ ወልድና ሌሎችም ሚኒስትሮች ነበሩ። ከመካከላቸው የነበሩት ራስ ሥዩምን ጠርተው እርስዎ ወደ ቤትዎ ይሂዱ ቢሏቸው እነሱን ወንድሞቼን በተለይ ራስ አበበን ትቼ አልሄድም ስላሉ አብረው ተረሽነዋል።



ጄኔራል ፅጌ ዲቡ

በመሠረቱ ግልበጣውን እንዲከሽፍ ያደረገው አንደኛ በዘመኑ ንጉሥን መክዳት እንደ ትልቅ ኃጢያት በመታየቱና በፖለቲካው ረገድ የተራው ወታደር ንቃተ ሕሊና በጣም አነስተኛ ስለነበረም ጭምር ነው። ሁለተኛ ደግሞ የፖሊስ ፊጥኖ ደራሽ አዛዥ የነበሩት ሌተና ኮሎኔል ታደሰ ብሩ ክቡር ዘበኞችን በመክዳት ከጀርባ በማስተኮሳቸው ሲሆን ሦስተኛውና ዋናው ምክንያት ግልበጣውን የወጠኑት ሰዎች ስህተቶችን በመሥራታቸውም ጭምር ነው። በተጨማሪም የአሜሪካን አምባሳደርና ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሁለቱን ወገን ለማስታረቅ ከሞከሩ በኋላ ገልባጮቹን የሚያወግዝ ወረቀት አቡኑ በማስበተናቸው አስተዋጽዖ አድርገዋል። ብፁዕነታቸው ከማስታረቅ አልፈው አንዱን ወገን ማውገዛቸው ፖለቲካው ውስጥ አስገብቷቸዋል። ሆኖም በወቅቱ በዚህ ድርጊታቸው የተቻቸው አልነበረም።

ጃንሆይ የ25ኛ የዘውድ በዓላቸውን በ1948 ዓ.ም በሚያከብሩበት ወቅት በተዘጋጀው የዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ላይ በአሜሪካን አምባሳደር ሚስተር ሳይመንሰን የተዘጋጀውና ለሕዝብ ይታደል የነበረው የጃንሆይ ምስል ነበር። አንድ መንግሥት በሌላ አገር የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ለዚህ መሪ ትገዙ ብሎ የማስታወቂያ ሥራ

መሥራት ባልቃ ገብነት ነው። የአሜሪካ መንግሥት ከንጉሠ ነገሥቱ ዘመን ጀምሮ እጁን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ያስገባ ስለነበረ በታሕሣሥ ግርግር በአስታራቂነት በሁለቱ ጦር መሪዎች መካከል ይሯሯጥ ነበር። በወቅቱ የአሜሪካን አምባሳደር የነበሩት ሚስተር አርተር ሪቻርድስ የአስታራቂነቱን ቦታ ይዘው ጊዜ ያባክኑ ነበር። እኚሁ ሰው በቺሊ የአሌንዴን መንግሥት ማስገልበጥም ችለዋል። ደርግም ከሥልጣን በወረደ ጊዜ አንተ ግባ፣ አንተ ውጣ፣ የሚለው የአሜሪካ ባለሥልጣን ሚስተር ኮሄን ነበር። ይህም የሚያመለክተው ወደፊትም ቢሆን በአገራችን ጉዳይ አሜሪካኖች ባልቃ እየገቡ ማስቸገራቸው የማይቀር መሆኑን ነው። የዛምቢያ መሪ ኬኔት ካውንዳ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እየገቡ ይዘባርቁ እንደነበረ ብዙ ጊዜ ታይቷል። ጃንሆይን 'በመካከላችን እንደ ፀሐይ የሚያበሩ ንጉሥ' ባሉበት አፋቸው በኮሎኔል መንግሥቱ ጊዜ 'አንድ አገር ስል ኢትዮጵያ በሉ!' 'አንድ መሪ ስል መንግሥቱ በሉ!' ብለው ሕዝቡን ሲያስጨበጭቡ ነበር።

ሸሽተው የነበሩት እነ መንግሥቱ ንዋይ ከሳምንት በኋላ ተደርሶባቸው በተኩስ ልውውጥ ሲገደሉ ጄኔራል መንግሥቱ ግን ቆስለው ተያዙ። ከተያዙም በኋላ "እንዴት አርበኞችን ትገላላችሁ ተብለው ሲጠየቁ "እኛ የገደልነው የ 5 ዓመት አረበኛ የ 25 ዓመት ቀማኛን ነው" ብለው መለሱ። ከተረሸኑት ባለሥልጣኖች መካከል አንዳንዶቹ በብዙ ጉዳይ ላይ ቢወነጀሉም ከፊሎቹ ኋላ ቀር ስለነበሩ በገዛ እጃቸው ትዝብት ላይ የሚጥላቸው ብዙ የትምክህተኛ ስህተቶችም ፈጽመው ነበር። ለምሳሌ እንደሊላው ሕዝብ የመብራት፣ የውሃና የስልክ ፍጆታቸውን ለማስከፈል የሚመጣውን ገንዘብ ሰብሳቢ እንኳን ላለመክፈል ሲሉ "ባቀናነው አገር! ደግሞ ማነው የሚያስከፍለን!" በማለት ያባርሩ ነበር።

ከ1953 ዓ. ም. የታህሣሥ ግርግር አንስቶ በጃንሆይ መንግሥት ላይ በየዓመቱ የተማሪው ረብሻ ለ**13** ዓመት ባለማቋረጥ ይደረግ ስለነበረ በአዲስ አበባ ውስጥ የከተማው ሱቆች ዝርፊያ እየፈሩ በጊዜ መዝጋት ጀመሩ። የፖለቲካ ስሜት ያላቸው ሰዎች ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ስህተት በማጉላት ሲናገሩ ሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች ግን የጉዳዩ ክብደት ሊታያቸው አልቻለም። ንጉሠ ነገሥቱ ግን ነገሮችን ለማስተካከል ምንም እርምጃ ባይወስዱም ግንዛቤያቸው



የተሻለ ነበር። አንድ ቀን ተቆጥተው "ምንድነው ይኸ ነገር!" ብለው ሲጠይቁ "አይ ትንሽ ተማሪዎች ናቸው" ሲሏቸው "ተማሪም እኮ ሕዝብ ነው!" ብለው ተቆጡ ይባላል። ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ በ**1966** ዓ.ም ከእስር ተፈተው ቅዱስ ዮሴፍ ለቀብር ማርሴዲስ መኪናቸውን እየነዱ መጥተው አንድ ወዳጃቸው "ምነው ይህንን መኪና ለጊዜው ብታስቀምጠው፣ ዓይን አስገብቶሃል!" ብሎ ሊመክራቸው ቢሞክር "ምን እንዳይሆን ብለህ ነው! አይምሰልህ!" ብለው መለሱ። ከጥቂት ቀን በኋላ እንደገና ታሥረው የሚመኩበት መንግሥት ፈራረሰ።

የሕዝቡ እሮሮ በመብዛቱ ጊዜውን ጠብቆ እንቅስቃሴ ተነሥቶ መንግሥት እስከ ተገለበጠ ድረስ ሊገታ አልቻለም። በ**1966** ዓ.ም ጃንሆይ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሄደው በንግግራቸው ላይ ሁል ጊዜ 'የምንወደውና የሚወደን ሕዝባችን' የሚሉት ሕዝብ ቲማቲም ወረወረባቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ ጥር **12** ቀን 1966 ዓ.ም ለቃና ዘገሊላ የካ ሚካኤል ታቦቱ ሲገባ ከራሺያ ከመጡት ጳጳስ አቡነ ፒሜንን ጋር ሄደው ድንጋይ ተወረወረባቸው። ጥቂት ቆይቶ የቤንዚን ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ባለታክሲዎች ሥራ አቆሙ። አስተማሪዎች በዚያን ወቅት ሥራ አቁመው ስለነበረ ተማሪው ሁሉ መንገድ ላይ ነበር። በመሃሉ አውቶቡሶች ሕዝቡን እያመላለሱ ባለታክሲዎች ሥራ ፈተው በሚንገዋለሉበት ጊዜ አውቶብሶችን መስበርና ማስቆም ተጀመረ። ከአውቶብስ በኋላ የግል አሽከርካሪዎች ላይም ድንጋይ መወርወር ሲጀመር አንዳንድ ሰዎች ከአደጋ ራሳቸውን ለመከላከል እየተኮሱ የአዲስ አበባ ከተማ ተናወጠች። አስከትሎም ተሽከርካሪዎች ቆመው ሰው ሁሉ እግረኛ ሆነ።

በመሃሉ ነገሌ ቦረና ያለው ጦር በደል ስለነበረበት አመጸና የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩትን ጄኔራል ከበደ ገብሬን እንዲመጡ ቢጠራም በምትካቸው የምድር ጦር ዋና አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ተልከው ቢሄዱ አሠራቸው። ጄኔራል ድረሴ ዱባለ ያንኑ ቦታ ከዓመት በፊት ሲጎበኙ የነበረውን ሁኔታ ተመልክተውና ነገሮችን ለማስተካከል ቃል ገብተው ከተመለሱ በኋላ ምንም ሳያደርጉ ከርመው እንደገና ሲላኩ ሮጠው የሄዱት ትዕዛዝ ለመፈጸም እንጂ ራሳቸውም ከመጀመሪያው ምንም እንደማይፈይዱ ያውቁት ነበር።

ጄኔራል ድረሴን ለማስፈታት የተላኩት የአየር ኃይሉ አዛዥ ጄኔራል አበራ ወልደ ማርያም ጠሩን አግባብተው እስረኛውን ጄኔራል አስፈትተው ተመለሱ። ነገሩ ተቀጣጥሎ በየቦታው ያሉት ወታደሮች በሙሉ መገናኘት ጀምረው አቤቱታቸውን በአሥመራ ሬዲዮ በኩል በይፋ ዘረዘሩ። አስከትሎም ወኪሎቻቸውን ወደ አዲስ አበባ ልከው ሳለ የአክሊሉ ካቢኔ በድንገት መውረዱ ተገለጸና አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ተሾሙ። ወታደሮች የተሻሩትን ሚኒስትሮች ልቅምቅም አድርገው አስረው ንጉሠ ነገሥቱን ሠላምታ እየሰጡ ታማኝ መሆናቸውን አሳወቁ።

አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ልጅ እንዳልካቸው መኮንን አዲስ ካቢኔ አቋቋሙ። የወታደሮቹም ኮሚቴ ፈርሶ በሌላ ኮሚቴ ሲተካ መጨረሻ ላይ ያለው ኮሚቴ እራሱን ደርግ ብሎ አንድነቱን ከሁሉም የጦር ኃይሎችና ፖሊስ ሠራዊት ጋር አጠናክሮ ለጃንሆይ መንግሥት ታማኝ መሆኑን እያስታወቀ ባለሥልጣኖችን ማሾምና ማሻር ጀመረ። በመሃሉ ተፈተው የነበሩትን ሚኒስትሮችም እንደገና መልሶ አሰረ። ይህ ሁሉ ሲሆን ጃንሆይ ከወታደሩ ጋር እንደገና በአዲስ መልክ አገሩን አስተዳድረዋለሁ በሚል ሃሳብ ወይም እኔ እስካለሁ ድረስ ለመግዛት ልሞክር ካልሆነልኝም ከእኔ ወዲያ ሰርዶ አይብቀል በሚል ከወታደሮቹ ጋር እየተስማሙ እስከ መጨረሻው ቆዩ።

አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ልጅ እንዳልካቸው መኮንንን ተማሪ አስቀድሞም ቢሆን አይወዳቸውም ነበረና ገና ሲሾሙ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም" ብሎ ተቃወማቸው። ከዚህ በኋላ እሳቸውም ፋታ ስጡኝ እያሉ ቢወተውቱም ከየድርጅቱ የሚቀርበው አቤቱታ ከልክ በላይ ሆነና ሰላማዊ ሠልፍንም ጋበዘ። በተለይ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ባዘጋጁት ሰላማዊ ሠልፍ ላይ ክርስቲያኑም ስለተደመረበት በጣም ብዙ ሰው ተሠልፎ ባለሥልጣኑን ሁሉ አናወጠው። በመጨረሻም ደርግ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳልካቸው መኮንንን እንደሌሎቹ ባለሥልጣኖች ወደ ማረፊያ ቤት ወሰዳቸው። ሚኒስትሮችና የጦር ባለሥልጣኖች ከየሠፈራቸው ሲለቀሙ ሕዝቡ እየተሰበሰበ ደስታውን ይገልጽ ነበር።

ቀጥሎም ልጅ ሚካኤል እምሩን ደርግ ጠቅላይ ሚኒስትር አስኝቶ በንጉሡ አሾመ። ራሱ ደርግ ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ ሕዝቡን እያነሳሳ መሠረቱን አጠናከረ። የወሎ ድርቅ ተደብቋል ብሎ መንግሥትን አሳጣ። የኮንጎ ዘማቾች የተባበሩት መንግሥታት የሰጠን ገንዘብ በባለሥልጣኖች ተመዝብሯል ብለው አቤት ስላሉ ጃንሆይ ዘንድ ቀርበው ሲነጋገሩ ንጉሡን



"ሊባ!" ብለው ደፈሩ። ጃንሆይ ወታደሩ የማይነካቸው መስሏቸው ከርመው ወደ መጨረሻ ላይ ነገሩ እየገባቸው ሲሄድ አልጋ ወራሻቸው በጠና ታምው ለህክምና ውጪ አገር ስለነበሩ ቀኃሥ ሐምሌ 16 ቀን 1966 ዓ.ም የልደት በዓላቸውን ባከበሩ ቀን የአልጋ ወራሹን ወንድ ልጅ ልዑል ዘርዓ ያዕቆብን ምክትል አልጋ ወራሽ ብለው ሾሙ። በዚህን ጊዜ ሕዝቡ ተስፋ ቆርጦ የሚወያየው ስለሕዝባዊ መንግሥት ስለነበረ በአዲሱ ሹመት ሳቀ እንጂ እንደ ቁምነገር አልቆጠረውም። አዋጁ የተነገረ ዕለት ማታ አዲስ አበባ የታወቀው ጅማ ባር አጠገብ አንድ ወፈፌ "በአንደ አገር ሁለት አልጋ ወራሽ!" እያለ በመሳለቅ በለወ አእምሮ የነበረውን አንጸባረቀ ።

ከቀን ወደ ቀን ባጠገባቸው ያለው መኳንንት ሁሉ እየታሠረ ብቻቸውን እየቀሩ ሲሄዱ በቅርባቸው የተገኙት ራስ እምሩና ደጃዝማች ከበደ ብቻ ነበሩ። ሌሎቹ ልጃቸው ልዕልት ተናኘ ወርቅና በአገር የቀሩት የልዑል መኮንን ልጆች ነበሩ።

መስከረም 1 ቀን 1967 ዓ.ም የእንቁጣጣሽ ዕለት ማታ የኢትዮጵያ ሕዝብና ራሳቸው ጃንሆይም ተጋብዘው በቴሌቪዥን ጆናታን ድምብልቢይ የሚባል የእንግሊዝ ጋዜጠኛ በድብቅ ያነሳው የወሎ ረሃብ ፊልም በቴሌቪዥን ለሕዝብ ተላለፈ። የተላለፈበትም ምክንያት ሆን ተብሎ ንጉሠ ነገሥቱ በሕዝቡ እንዲጠሉ የተደረገ የፕሮፓጋንዳ እርምጃ ነበር።

በማግስቱ ጠዋት መስከረም 2 ቀን1967 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሬዲዮ የንጉሠ ነገሥቱን ከሥልጣን መውረድና በጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መተካት ደጋግሞ አወጀ። የሥራ ቀን ስለነበር ሁሉም ሰው ወደየመሥሪያ ቤቱ ሲሄድ ተማሪዎች ወታደር ሥልጣን መውሰዱን በመቃወም አንዳንድ

ቦታ ላይ ሠልፍ ለማድረግ ሲሞክሩ ፖሊሶች አሁንም ያባርሯቸው ጀመር። ማታ ግን በርቀት የተነሳውን የሠልፉን ፊልም ተማሪዎች የደርግ ሥልጣን መያዝን እንደ ደገፉት ተድርጎ በቴሌቪዥን ተላለፈ። ይህ ዜና ምናልባትም በደርግ ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያው የሃሰት ዜና ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል።

በኋላ የተለማው ወሬ ግን የደርግ አባሎች ቤተ መንግሥት ሄደው ራስ እምሩ በተገኙበት ንጉሡን አስቀምጠው ከሥልጣን መውረዳቸውን የሚያስረዳ ጽሑፍ ከደርግ አባሎች በአንዱ በሻለቃ ደበላ ዲንሳ ለንጉሡ እንደተነበበና ቀጥሎም በሾፌራቸው በጄኔራል ሉሉ የግል ቮልክስዋገን ቢትልስ መኪና ወደ ማረፊያ ቤት እንደተወሰዱ ነው። በዚያን ጊዜ ትናንሽ ልጆች ቤተ መንግሥቱ አጠገብ ወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ "ተፈሪ ሌባ" እያሉ ይጮሁ ነበር። ንጉሡም አንገታቸውን ጠጋ አድርገው ልጆቹ የሚናገሩትን ለመስማት ቢሞክሩ ስላቃታቸው "ምንድነው የሚሉት" ብለው ቢጠይቁ "ሌባ! ሌባ! ነው የሚሉት" ብለው ቢነግሯቸው "እውነታቸውን ነው ንጉሣቸውን ሠርቃችሁ ስትሄዱ" ብለው ተናገሩ ይባላል።



ወሎ በራብ አልቆ ሞት የበዛ እንደሆን
ተፈሪ የዛን ቀን ምን ይውጠው ይሆን
የጃን ነው የሚያገኝ የዛን ቀን ሰው አይሆን

ሼህ ሁሴን ጅብሪል





# ምዕራፍ ፵፰

# የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መጨረሻ

አንድ የዝቋላ ባሕታዊ የታያቸውን በጽሑፍ ለጃንሆይ በአንድ የቤተ መንግሥት ሰው በኩል ይልካሉ፤ መልዕክቱም እንዲህ ይላል። "እንግዲህ ያንተ መንግሥት አብቅቶለታል፣ ምንም የሚደረግ ነገር የለም፣ መጸለይ ብቻ ነው። ከምሥራቅ የሚመጣ ጥቁር ሻለቃ መንግሥትህን ይወስደዋል። ከሥልጣኑ ለማውረድ ብዙ ሰዎች ይሞክራሉ፣ ግን ለጥፋት የመጣ ስለኾነ ምንም አይሳካላቸውም።ጊዜው ሲደርስ እዚህ ገባ ሳይባል ይጠፋል። ዕድሜው እንዲያጥር መጾም መጸለይ ብቻ ነው"[21]።

መቼም ንጉሥ ዘንድ አዋቂ ነኝ የሚል ሁሉ ለመሸለምና ለመታወቅ ሲል የታየውን ትንቢት ዕውነቱንም፣ ውሸቱንም፣ እንደሚያስተላልፍ የታወቀ ቢሆንም ንጉሡ ለዚህ መልዕክት የተለየ ግንዛቤ የሰጡት አይመስልም። አሁን ስናየው ግን ትንቢቱ እንደ ደረሰ እንገነዘባለን።

ንጉሠ ነገሥቱ ከመንግሥቱ ንዋይ ያልተሳካ የመንግሥት ግልበጣ በኋላ ንግግራቸው ላይ "...እኛን የመረጠ እግዚአብሔር ብድር መላሽነቱንና ውለተኛነቱን ስለምናምን ሕይወታችን እስከፈቀደ ድረስ ሕዝባችንን እናገለግለዋለን" እንዳሉት ሥልጣናቸውን ለማስተላለፍ ፈቃደኛ አልሆኑም። የሚቀርቧቸው ራስ እምሩና ሌሎችም ያስፈጁናል፣ ሥልጣንዎን በጊዜ ይልቀቁ ሲሉዋቸው እየተቆጡ እምቢ ይሉ ነበር። ሌተና ጄኔራል ዓቢይ አበበ ይህንኑ ፍርሃታቸውን ቀደም ብለው 'አውቀን እንታረም' በሚል መጽሐፍ ቢናገሩም ሰሚ አልተገኘም። ቢትወደድ

[21] አምባሳደር ብርሃኑ ድንቄ አዲስ መጽሐፍ ለማስተዋወቅ በበተኑት ወረቀት ላይ የተጻፈ.

ዘውዴ ገብረ ሕይወት የአገር ግዛት ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት ስለዚሁ ጉዳይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሲወያዩበት ተገኝተው ከሚኒስትርነት ሥልጣናቸው ተሽረው ወደ ሲዳሞ ጠቅላይ ግዛት በአስተዳዳሪነት ተዛውረዋል። በ1955 ዓ.ም ሌተና ጄኔራል ዓቢይ አበበ፣ ሌተና ጄኔራል መርዕድ መንገሻ፣ ልዑል ራስ ዓሥራተ ካሣ፣ ሌተና ኮሎኔል ታምራት ይገዙና ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሃዋርያት በአንድነት "ግርማዊነትዎ ጊዜን እንዲሽቀዳደሙ" በሚል ማሳሰቢያ በጽሑፍ ቢያቀርቡም ከነበሩበት ቦታ ተሻሩበት እንጂ ምክሩ ተቀባይነት አላገኘም። ልዕልት የሻሽ ወርቅ ይልማ ጃንሆይን "ሰው ያጉረመርማል! በተለይ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እየረበሹ ነው! ተከታዩን ንጉሥ አንግሠው እርስዎ ቦታ ይልቀቁ! አይሆንም!.." በማለታቸው ምክሩን ጃንሆይ ስላልተቀበሉትና ስለተናደዱባቸው ፈርተው ወደ ስዊዘርላንድ ሄዱ። ከዚያም በውጭ ሲኖሩ ቆይተው በአስታራቂ አማካይነት ተመልሰው መጡ። እንደፈሩትም ደርግ ሥልጣን እንደያዘ በ1967 ዓ.ም አሥሯቸው አሥራ አምስት ዓመት ቆይተው እንደተፈቱ ሞቱ።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሐምሌ 16 ቀን 1964 ዓ.ም በጣም ከፍ ባለ ሥነ ሥርዓት የ 80 ዓመት ልደታቸውን ሲያከብሩ አዲስ አበባ በተለያዩ ቀለማት መብራቶች ተሽቆጥቁጣ በዓሉ በድምቀት ተከብሮ አለፈ። ቀጥሎም ሥልጣናቸውን አስረክበው በክብር የሚቀረውን ዕድሜያቸውን እንዲያሳልፉ ሕዝቡ ሁሉ ተመኘ። አንዳንዶች የመንግሥት ሥልጣናቸውን ልጃቸው ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን ተረክበው እሳቸው አፄ ተብለው ለክብር በንጉሠ ነገሥትነታቸው ያለ ሥልጣን እንዲኖሩ አማራጭ ሲያቀርብ ሌሎች ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ሕዝብ መርጦ ንጉሠ ነገሥቱ በዘመናችን እንዳሉ ንጉሣዊ አገሮች ያለሥልጣን ለክብርና ለታሪክ ብቻ ይኑሩ እያሉ አማራጭ ሃሳብ ማቅረብ ጀመሩ።

ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ሰው ሲያረጅ በአብዛኛው መንኩሶ ወደ ጾምና ጸሎት ያደላና ያለበትን ኃላፊነት ለተወላጆቹ ያስተላልፋል። ከንጉሦችም መካከል መንኩሰው ገዳም የገቡ ብዙ ናቸው። ይኸ ባልሆነበት ሁኔታ ግን መሳፍንቶችና መኳንንቶች ተሰብስበው ይመክሩና ለቀጣዩ ዘመን የሚበጅ ውሳኔ ላይ ይደርሳሉ።

በዕድሜያቸው መግፋት ምክንያት ንጉሠ ነገሥቱ ወደ መጃጀቱ ደረጃ ደርሰው ነበር። ታዲያ በተለያዩ የመንግሥት ሥልጣን ላይ የነበሩ



ሰዎች ለአገርና ለራሳቸውም የሚያስቡ ቢሆኑ ኖሮ ሥልጣኑን ለሌላ ሰው አዛውረው ንጉሠ ነገሥቱን ለስም ብቻ የማስቀመጥ ኃላፊነት ነበረባቸው። ባለ ሥልጣኖቹም እርስ በእርስ በመፈራራትና ለንጉሠ ነገሥቱ የሚሰጡት ከበሬታ ከፍ ከማለቱ የተነሳ ሰው መሆናቸውንም እስከመዘንጋት ስላደረሳቸው ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ ባለመውሰዳቸው ብዙ ደም እንዲፈስና ከነጭራሹ የመንግሥቱ ሥርዓት ከመሠረቱ እንዲገረሰስ አድርገዋል።

ግንቦት 6 ቀን 1965 ዓ.ም ጃንሆይ የሶማሌውን ስይድ ባሬ ወረራ ለመቋቋም በማሰብ መሣሪያ ለመግዛት ፕሬዚዴንት ኒክሰን ዘንድ ሄደው ሰተወሰነ ጊዜ ንግግር እንዲያደርጉ ሲጠበቁ የሄዱበትን ፍሬ ነገር ትተው የማይመለከታቸውንና የተንዛዛ ንግግር አደረጉ። አስተርጓሚው ዶክተር ምናሴ ኃይሌ ግራ በመጋባት ነገሮችን ለማረም ብለው ንጉሠ ነገሥቱ የሚናገሩትን ትተው ፍሬ ነገሩን ብቻ መናገር ሲጀምሩ ጃንሆይ ንግግራቸውን አቋርጠው መቆጣት ጀመሩ። የዚህን ጊዜ ፕሬዚዴንት ኒክሰን ጊዜ ስላጠራቸው ይቅርታ ጠይቀው ወደሌላ ጉዳያቸው ሄዱ። ጥቅምት 23 ቀን 1966 ዓ.ም የዘውድ በዓል ላይ የተዘጋጀውን የፓርላማ መክፈቻ ዙፋናዊ ንግግር ጽሑፍ እልፍኝ አስከልካዩ ጄኔራል አሰፋ ደምሴ እቤታቸው ረስተው መጥተው ነበርና ቢጠየቁ ደንግጠው እቤት ሄደው ግማሽ ሰዓት ያህል ቆይተው አመጡት። በዚህን ጊዜ ጃንሆይ እንደበፊቱ ይቆጣሉ ተብለው ሲጠበቁ የተፈጠረውን ችግር ከጉዳይ ሳይጥፉት በመቅረታቸው ሰው ሁሉ መጃጃታቸውን እያወቀ ሄደ። በማግስቱ የአገሪቱ እንግዳ የነበሩትን አቡነ መቃርዮስ የቆጵሮስ (ሳይፕረስ) ፕሬዚዳንት መሆናቸውን ጃንሆይ ዘንግተው አለባበሳቸውን ብቻ በመመልከት ስለዴር ሡልጣን ገዳም ማነጋገር ሲጀምሩ ሰውዬው ግራ ተጋቡ።

በተጨማሪም ለብዙ ዓመት የካቢኔ አባል የነበሩት ክቡር አቶ ግላሀ ሂኒት የፖስታና ቴ.ቴ. ሚኒስትር እንደተለመደው ከሌሎች ሚኒስትሮች ጋር ቤተ መንግሥት ሄደው እጅ ሲነሱ ወፈር ያሉ፣ ፀጉረ ሉጫና ረጅም ስለነበሩ ጃንሆይ ጠቅላይ ሚኒስትር ፀሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሃብተ ወልድን "ይኼ ደግሞ ማነው?" ብለው ጠየቁ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ "ክቡር አቶ ግላሀ ሂኒት የፖስታ ቴ.ቴ. ሚኒስትር ናቸው" ብለው መለሱ። ጃንሆይም መልሰው "የማን ፖስታ ቴ.ቴ.

ሚኒስትር?" ብለው ሲጠይቁ ለመመለስ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ። ለአስቸኳይ የመንግሥት ሥራ ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጃንሆይን ለማነጋገር በዚሁ በ1966 ዓ.ም. መገባደጃ ላይ እቢሯቸው ሲገቡ ከፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ ጋር የግል ጭውውት ያደርጉ ነበርና መለስ ብለው "አንተን ብቻ ነው እንዴ ሁል ጊዜ የምናነጋግረው!" ብለው አሳፍረው መለሷቸው። በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች የጃንሆይ እርጅና የመንግሥቱን ሥራ ለማቀላጠፍ ከማስቸገሩ በላይ የተተኪ ጉዳይ ግልጽ ያልሆነበት ወቅት ተፈጥሮ እያለ በሥልጣን ላይ የነበሩት ሰዎች እርምጃ አለመውሰዳቸው ራሳቸውንም አገሪቱንም ጎዳ።

በ1966 ዓ.ም በሕዝባዊ አመጽ የተቀሰቀሰው አብዮት እየገነፈለ ሲመጣ ለልጆቻቸው፣ ለተከታዮቻቸው ሚኒስትሮችና መኳንንቶች ደህንነት እንኳን ሳይቀር ፈጽሞ ባለማሰብ ሁኔታውን በዘዴ ለማሳለፍና በጥንቱ አገዛዛቸው ለመቀጠል ስላቀዱ አልፈው ተርፈው ሚኒስትሮቻቸው በደርግ ሲታሰሩ ተባባሪ ሆኑ። አንዳንድ የጦር መኮንኖችም የመጣውን ችግር በኃይል እናጨናግፈው ይፍቀዱልን ቢሏቸውም እየተቆጡ ተከላከሉ። በተለይ የክብር ዘበኛ አዛዥ የነበሩት ጄኔራል አበበ ገመዳ ደጋግመው ቢጠይቁ ፈቃድ አጡ። ከተከላከሉት ሰዎች መካከል ደጃች ከበደ ተሰማም እንደነበሩበት ታምተዋል።

ሆኖም መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከሥልጣን ወርደው ታሰሩ። ጥቂት ወራት ከቆዩ በኋላ የደርግ ጽሕፈት ቤትም ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ተዛውሮ ስለነበረ ንጉሠ ነገሥቱም ወደእዚያው ተወስደው በእስር ተቀመጡ። በመሃሉ የፕሮስቴት ህመም ስለ አስቸገራቸው የታወቁት ሃኪም ፕሮፌሰር አሥራት ወልደ የስ የቀዶ ጥገና ህክምና አድርገውላቸው ተሻላቸው።

የመንግሥቱ ለውጥ ባስገኘው ዕድል ሥልጣን የጨበጡት የደርግ አባሎች ከተደበቁበት ብቅ እያሉ መታወቅ ቢጀምሩም ውስጥ ውስጡን ልባቸው ይፈራ ስለነበረና ተቃውሞም እየበረታባቸው ስለሄደ ተጠራጥረው ከንጉሡ ባለሥልጣኖችና መኳንንቶች የሚፈሯቸውን ራሳቸው በድምጽ ብልጫ ወስነው ያለፍርድ ፈጇቸው።

ምንም እንኳን የተማረው ክፍል የለውጥ ደጋፊ መሆኑ ቢታወቅም ከዚሁ ክፍል ጥቂቶች ብቻ የእነሱ ደጋፊ ሲሆኑ አብዛኛው ተቀዋሚያቸው



መሆናቸውን ተረዱ። በዚህም የተነሳ ሶሽያሊዝም መርሃቸው መሆኑን አስታውቀው "ዕድገት በኅብረት" የሚል ዘመቻ አውጀው በዚህ ሽፋን ተማሪውን ከከተማ አስወጥተው በየአውራጃውና በየወረዳው በተኗቸው። እዚህ ላይ "ዕድገት በኅብረት" የሚለው ስም ታዋቂው የስፖርት ጋዜጠኛ ሰሎሞን ተሰማና ጓደኞቹ አቋቁመውት ለነበረው የመረዳጃ ማኅበር የሰጡት ስም እንጂ ደርግ ያወጀውን የዘመቻ ተግባር አይገልጽም።

ከመቶ አሥር በላይ የሆኑት (በስህተት መቶ ሃያ ነን ብለው የተናገሩት) የደርግ አባሎች መካከልም የማይመስሏቸውን ወደ መጡበት ክፍለ ጦር መልሰው በሌላ በሚታዘዛቸው ሲተኩ አንዳንዶችም እየከዱ መጥፋት ጀመሩ። በተፈጠረው የሥልጣን ሽሚያ ቤተ መንግሥት ውስጥም የተጋደሉ ነበሩ።

የንጉሠ ነገሥቱ በሕይወት መኖር የእነ ኮሎኔል መንግሥቱን ሕሊና አላሳርፍ ስላለና በወቅቱ ሽፍተው ጫካ የገቡትን ተስፋ ለማስቆረጥ ጃንሆይን በትራስ አፍነው ከገደሉ በኋላ ለማሳሳት ባዶ ሳጥን ባዕታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን በር ላይ አስቀምጠው ጉድጓድ ሲያስቆፍሩና መሞታቸውንና መቀበራቸውን ሲያስወሩ ዋሉ።



ጃንሆይ በማረፊያ ቤት

በሌላው መልኩ ሻለቃ ጌታቸው የሮም 'የለውጡ ረመጥ የታሪክ ማስታወሻ' በሚለው መጽሐፋቸው ላይ ደርጎች የጃንሆይ አስከሬን ላይ መርዝ (Synide) አፍስሰው ወህኒ ቤት ወስደው በማይለይ ቦታ እንደቀበሩዋቸው ጠቅሰዋል።

ኢሕአዴግ ሥልጣን እንደያዘ መቃብሮችን እያስቆፈረ የብዙ ሰዎችን አስከሬን ለቤተሰቦቻቸው እየሰጠ እንደገና በክብር እንዲቀብሩ አድርጓል። የጃንሆይ አስከሬን ከመንግሥቱ ኃይለ ማርያም

ቢሮ ሥር 16 ዓመት ተቀብሮ ከቆየ በኋላ በውስጥ አዋቂ ጥቆማ ተቆፍሮ ወጣ ተባለ። የተገኘው አስከሬን በቁሙ እርቃኑን የተቀበረ ሲሆን በቀብሩ ሰዓት ዘፍ እንዳይል አንገቱ በሽቦ እንደታሰረ ተገኘ ተብሎም ተወርቷል። አስከሬን መርማሪዎች ከውጭ አገር መጥተው የጃንሆይ መሆኑን ባያረጋግጡም አስከሬኑ ታች ግቢ ውስጥ በምትገኘው ባዕታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ለጊዜው እንዲያርፍ ተደረገ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ስለቀብሩ ሥነ ሥርዓት አፈጻጸም ጉዳይ ኮሚቴ ተቋቁሞ ለረጅም ጊዜ ብዙ ውዝግብ ካስነሳ በኋላ በመጨረሻ በ1992 ዓ.ም በነቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወትና በሌሎች የኮሚቴ አባላት ብርታት ልዑላን ቤተሰቦቻቸውና ብዙ ሕዝብ በተገኘበት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን በሕይወት ዘመናቸው ባሠሩት መቃብር ውስጥ አስከሬናቸው እንዲያርፍ ተደርጓል። ይሁንና አሁንም ቀብሩ ይፋ በዓል ባለመሆኑና በተጨማሪም ብዙ ወዳጆቻቸው ከውጭም አገር ሳይቀር መጥተው ባልተገኙበት የቀብር ሥነ ሥርዓታቸው መከናወኑ በሰዎች ዘንድ ቅሬታን ፈጥሯል። ይህም የሆነበት ምክንያት መንግሥት ለውጪ እንግዶች ደህንነት ዋስትና ባለመስጠቱና ይፋ መሆኑንም ስላላስታወቀ ነው።

ንጉሥ ዳዊት የሰው ልጅ ዕድሜ ሰባ ዓመት ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው እንዳለው ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለራሳቸውና ለኢትዮጵያ ክብር ብለው ሰማንያ ዓመታቸውን አክብረው ከሥልጣን ዘወር ብለው ቢቆዩና ሞትም ሲመጣ በይፋ የኢትዮጵያ ሕዝብ እያለቀሰ በቀበራቸው ኖሮ ምንኛ ታሪክ ያምር ነበር። እንደ ተወለደ ከእናቱ ዘንድ በድብቅ ተወስዶ ያደገው ጨቅላ በ83 ዓመታቸውም ከሚወዷቸውና ከሚያከብሯቸው ቤተሰቦቻቸውና ባለሟሎቻቸው መካከል ተወስደው ታስረውና በመጨረሻም ተገድለው አስከሬናቸው በድብቅ ተቀበረ።

ተፈሪ መኮንን በ13 ዓመታቸው ደጃዝማች ሆነው በመንግሥት ሥልጣን ወጥተው በ83 ዓመታቸው ከንጉሠ ነገሥትነት እስከ ተሻሩ ድረስ፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ለ70 ዓመት በኢትዮጵያ የመንግሥት ሥልጣን ላይ የቆዩ ነበሩ። በዚህ ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ ከፊውዳል ሥርዓት ወጥታ፣ በዘመናዊ አስተዳደር ለመተዳደር የሞከረችበት ዘመን ሲሆን፣ በመሃሉ ያልለመደችው በውጭ ኃይል መሸነፍ፣ የሃይማኖት ነፃነትና የምዕራባውያን ጥበብ የታየበት ዘመን ነበረ። እንደዚሁ ሁሉ



በምዕራባውያን ተንኮልና ሤራ የኢትዮጵያ ባለሥልጣን የተሻረበትና የተሾመበት፣ የተገደለበትና የእነሱን ክፋት የኢትዮጵያ ሕዝብም መንግሥትም መማር የጀመረበት ዘመን ነበር። ምንም እንኳን ጃንሆይ ከቀደሙት ነገሥታት በተለየ ዕድለኛ ቢሆኑም በጥቅሉ ሲታይ ዘመነ መንግሥታቸው ለረጅም ጊዜ የሠላም ዘመን ሆኖ እያለ አገሪቷ የኤኮኖሚ እመርታ ልታገኝ ስትችል አልተሳካላትም። ከጃንሆይ ዘመነ መንግሥት አስከትሎ አገሪቱ ለአደጋ እንድትጋለጥና በኮሙኒስት ሥርዓት እንድትዘፈቅ መንገድ የተጠረገበት ዘመንም ነበር።

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደስ የሚሉ ንጉሥ ስለነበሩና የሚወዳቸው ሰው ብዙ እንደመሆኑ መጠን ውስጥ ውስጡን የማይወዱዋቸውም ሰዎች ስለነበሩ ‘የጁን ነው ያገኘው’ እያሉ ይናገሩ ነበር። ስለቀብራቸው ሲነሳም እሳቸው እንዳደረጉት ከኾነ ይሄም ይበዛባቸዋል የሚሉም አሉ። እንደ ጌታቸው ኃረደው ዓይነት የንጉሠ ነገሥቱ ተቃዋሚ በሰጡት አስተያየት “የንጉሠ ነገሥቱ አፅም በክብር ከመቀበሩ በፊት ንጉሡ ያስገደሏቸው ሰዎች አፅም ከየተጣለበት ተሰብስቦ በክብር መቀበር ቅድሚያ ማግኘት ይገባዋል። ስማቸው የማይታወቀውን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩትን በዝርዝር ለመጥቀስ ባይቻልም የታህሣሥ 5 ቀን 1953 ዓ.ም ንቅናቄ መሪ ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይን ሞት አስፈርደውበት ከሰቀሉት በኋላ አስከሬኑን ጥለውታል። የእሱ ጓደኞች ኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ሻምበል ባዬ ጥላሁን፣ አቶ ገርማሜ ንዋይ ራሳቸውን ከገደሉ በኋላ አስከሬናቸው አደባባይ ተሰቅሎ ውሎ እንደውሻ ሬሳ የትም ወድቆ ቀርቷል። ጄኔራል ጽጌ ዲቡን ያህል የፖሊስ ጄኔራል ተገሎ አስከሬኑን ወታደሮች ሲጫወቱበት ከዋሉ በኋላ በፅዳት መኪና ተጭኖ አልታወቀ ስፍራ ተጥሏል” ሲሉ አትተዋል። በበኩሌ መርምሬ ለመድረስ እንደቻልኩት የጄኔራል ጽጌ ዲቡ መቃብር እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ኮለኔል ወርቅነህና ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ እንደ በላይ ዘለቀ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በሌሊት የተቀበሩ መሆናቸውን ነው።

ኢትዮጵያን የመሰለ አንድ ባለታሪክ አገር 58 ዓመት ያስተዳደረውን መሪ ሲሆን እስከ ዕለተ ሞቱ ታሪክ ይፍረደው ብሎ በክብር ማስቀመጥ፣ አለበለዚያም ፍርድ ላይ አቅርቦ ተገቢውን ፍትሕ መስጠት በተገባ ነበር። ሲሞትም በክብር መቅበር እንጂ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ላይ የተደረገው ድርጊት ግን በሙሉ ውርደቱ ለቀሪው ባለታሪክ ሕዝብ ነው። ስለሆነም የተሳሳቱትና ሕዝቡንም ያሳሳቱት አመራሩን የያዙት የሥልጣን

ዘራፊ ባለሥልጣኖች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ጺሚና ጸላይ ነው እየተባለ ይገለጻል። ነገር ግን በክፉ ቀን የአረመኔ ሥራ ሲሠራ አገሪቷን ያልሠለጠነች አድርጎ ያስገምታታል። ይህ ዓይነት ሁኔታ በአገራችን ታሪክ የተደጋገመ ነው።

ኢትዮጵያ የንጉሡ ነገሥቱን 58 ዓመት የሥልጣን ዘመን አልፎ ራዕይ የሌለው ጨለማ ውስጥ ገብታ፣ ልጆቿ እየተሰደዱ፣ እርስ በርስ እየተዋጉ፣ እየደኸዩ፣ ሸረኞች በነዝባቸውና በተፈጥሮ መቅሠፍት እያለቁ፣ የባሕር በራቸው ተዘግቶ፣ በውጭ አገርም ኾነ በአገራቸው ባይተዋር ሆነውና ግራ ገብቷቸው፣ ለፈጣሪያቸው እየጸለዩ፣ እግዚአብሔርን መከታ አድርገው ተቀምጠው ይገኛሉ።

ሃበሻ ተፈሪን ይዘው ተቀበሩ
አሥመራ በሙሉ ይታጠራል በሩ
መቸም ላስተዋለው ብዙ ነው ነገሩ
እኔ አልናገርም አያል ነው ምሥጢሩ
ሼህ ሁሴን ጅብሪ

# ዋቢ መጽሐፍት


| | | |
|---|---|---|
| 1 | መጽሐፍ ቅዱስ | |
| 2 | የአፄ ኃይለ ሥላሴ ታሪክ | በበሪሁን ከበደ |
| 3 | የምክር ቤታችን ዕድል | በከበደ አንግዳ ሰው |
| 4 | የሕይወቴ ውጣ ውረድ | በበ.. ዘውዱ ገ/ሕይወት |
| 5 | የታሪክ ማስታወሻ | በደጃዝማች ከበደ ተሰማ |
| 6 | ከአፄ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ | በተክለጻድቅ መኩሪያ |
| 7 | የሰውጡ ረመጥ | በሻለቃ ጌታቸው የሮም |
| 8 | ጥርስ የነበች አገር | በጆን ስፔንሰር |
| 9 | የኦሮሞ ሕዝብ ታሪክ | በብርሃኑ ለሚሳና ታቦር ዋሚ |
| 10 | ጣይቱ ብጡል | በቀኛዝማች ታደሰ ዘወልዴ |
| 11 | የኢትዮጵያና የኢጣሊያን ጦርነት | በጳውሎስ ኞኞ |
| 12 | የአቶ መኮንን ሃብተወልደ ታሪክ | በአገር ፍቅረ ማኅበር ፕሬስ |
| 13 | ኤድስ ሳይንሳዊ መቅሰፍት ወይስ የፈጣሪ ቁጣ | በዶክተር ሊዮናርድ ሆርዊዝ |
| 14 | የአደዋ ድልና የኢትዮጵያ ጀግኖች ውለታ | በአበበ ኃይለ መስከት |
| 15 | ያቺ ቀን ተረሳች | በሕይወት ኅዳሩ |
| 16 | ቀይ አንበሳ | በኮሎኔል አልሸንድሮ ዴል ባዬ |
| 17 | ንጉሠ ነገሥቱ | በጌታቸው መኮንን ሃሰን |
| 18 | ደድረስ ሰባስታሪክ | በተስፋዬ መኮንን |
| 19 | ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀኃሥ 1936 ዓ ም | በተክለ ጻድቅ መኩሪያ |
| 20 | ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀኃሥ 1949 ዓ ም | በተክለ ጻድቅ መኩሪያ |
| 21 | የኤርትራ ታሪክ | በዘውዴ ረታ |
| 22 | ከንቲባ ገብሩ ደስታ | በኮሎኔል ዳዊት ገብሩ |
| 23 | የኢት ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን | በአባ ጎርጎሪዮስ |
| 24 | አይመስል | በተስፋ ገብረየስ |
| 25 | የኢትዮጵያ ታሪክ | በፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ |
| 26 | ኢትዮጵያ ሀገሬና ትዝታዬ | በበላይ ግደይ |
| 27 | የኢትዮጵያ ታሪክ | በአባ ጋስፓሪኒ |
| 28 | ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ | በቀኃሥ |
| 29 | Ethiopia A New Political History | Richard Greenfield |
| 30 | Ethiopia its people its society its culture | George A. Lipsky |
| 31 | Ethiopia Photographed | Richard Pankhrst |
| 32 | Lion by tha Tail | Thomas M. Coffey |
| 33 | Ethiopia The Modernization of Autocracy | Robert L. Hess |
| 34 | Beyond tha Utmost Purple Rim | E. Alexander Powell |
| 35 | Abyssinia on the Eve | Ladislas Farago |



# አቶ ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ

አቶ ጥላሁን ብርሃነ ሥላሴ ቤተ ጥቅምት ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፪ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። ከባህላዊ ትምህርት በኋላ በአርበኞች ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ፲፱፻፵፬ ዓ.ም አጠናቅቀው በንግድ ሥራ ትምህርት ቤት ከ፲፱፻፵፭ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም በመማር በሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሙያ በዲፕሎማ ተመርቀዋል። አርበኞች ትምህርት ቤት ሲማሩ በክርስትና ስማቸው ተክለ ገብርኤል በመባል ይታወቁ ነበር።

ትምህርቱን እንደጨረሱ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሂሳብ ክፍል ለሦስት ዓመት ሠርተዋል። ከዚያም በልዑል በዕደ ማርያም ላቦራቶሪ ትምህርት ቤት አስተማሪ ሆነው ሲያገለግሉ በቢዝነስ ኮሌጅ የቀን ተማሪ ሆነው መማር ጀምረው እያለ በጥላሁን ግዛው ሞት ምክንያት ዩኒቨርስቲው ለረጅም ጊዜ ስለተዘጋ ትምህርቱን ትተው አዲስ በተከፈተው የሒልተን ሆቴል በሂሳብ ሠራተኛነት ተቀጠሩ።

በአ.አ. ሒልተን ሆቴል አሥር ዓመት እንደሠሩ በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም ሊሶቶ ሒልተን ማሴሩ በዝውውር ሄደው አምስት ዓመት ተኩል ከሠሩ በኋላ በቆጵሮስና በካርቱም ለስድስት ወር ያህል ቆይተው ወደ ማዳጋስካር ሒልተን ታናናሪቭ ተዛወሩ። ማዳጋስካር ሁለት ዓመት ቆይተው እንደገና በዝውውር የናይጄሪያ አዲሱ ዋና ከተማ አቡጃ በናይከን ኖጋ ሒልተን ሆቴል የፋይናንስ ኃላፊ ሆነው ለሰባት ዓመት ተኩል ያህል እንደሠሩ በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም የግል ሥራቸውን ለመሥራት ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

በትርፍ ጊዜያቸው ማንበብ ስለሚወዱ የተሸፋፈኑ የታሪክ ሃቆችን ፈልቅቀው በማውጣትና የአንባቢን አእምሮ የሚኮረኩሩ ታሪኮችን በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተው ለተደራሲያን እነሆ አቅርበዋል። የሚቀጥሉትን የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ታሪክም አከታትለው ለመጻፍ በውጥን ላይ ናቸው። አምላክ ፈቃዱ ሆኖ እንዲሳካላቸው አመኛለሁ።

ጎሩይ በላይነህ አጋጅየለው